
የአንድ መነኩሴ ታሪክ ሰምተን ነበር ፤ ይህ መነኩሴ ከሌሎች መነኮሳት ጋር ሲነጋገር ቆይቶ ወደ በዓቱ ከሔደ በኋላ እጅግ በተደጋጋሚ በአቱን ሲዞር አንድ መነኩሴ ተመለከተውና ምን እያደረገ እንደሆነ ጠየቀው ፤ እርሱም መለሰ «ስናወራቸው የነበርናቸውን ዓለማዊ ወሬዎች እያስወገድኩ ነው ፤ ወደ በአቴ ይገቡ መግባት አልፈልግም»

ለሰዓታት በስልክ ማውራትን ያስቀረው አዲሱ ምትክ ደግሞ መልእክት መጻጻፍ ነው፡፡ በኢንተርኔት ምልልስ ማድረግ ሆኗል ነገሩ፡፡ ሌላው ቀርቶ አገልግሎቱን በስልክ ለማግኘት ስለሚቻል ኮምፒውተር መጠቀምም አይጠይቅም፡፡ የሚያገርመው ነገር በኢንተርኔት ለረዥም ሰዓታት ምልልስ ሲያደርጉ ከቆዩ በኋላ ከዚያው ሰው ጋር ለመነጋገር ስልካቸውን ማንሣታቸው ነው፡፡

ሦስት መነኮሳት አንድ ነገር ተገልጦላቸው የተገለጠው ነገር ከእግዚአብሔር ነው ወይንስ ከዲያቢሎስ እያሉ ይከራከሩ ነበር፡፡ በመጨረሻም ወደ ቅዱስ እንጦንስ ሔደው ሊጠይቁት ወሰኑ፡፡ ወደ ቅዱስ እንጦንስ ሲሔዱ በመንገድ ላይ ይዘውት ሲሔዱ የነበረ አህያ ሞተባቸው፡፡ መንገዳቸውን ቀጥለው ወደ ቅዱስ እንጦንስ ሲደርሱ «አህያችሁ መሞቱ በጣም ያሳዝናል!» አላቸው፡፡ እነርሱም «ስለ አህያው እንዴት ልታውቅ ቻልህ?» ሲሉ ጠየቁት፡፡ እርሱም «ሰይጣን ነገረኝ!» አላቸው፡፡ እነርሱም «ሳንጠይቅህ ጥያቄያችንን መለስህልን!» አሉት፡፡



አቡነ አትናስዮስ እስክንድር በማርች 9,1938 እ.ኤ.አ. በግብፅ ሹብራ አውራጃ ተወለዱ፡፡ በዐሥራ አምስት ዓመታቸው በኤይን ሻምስ ዩኒቨርሲቲ የሕክምና ትምህርት ቤት ገቡ፡፡ በ1962 በሕክምና ዶክተርነት ተመርቀው እስከ 1968 ድረስ በግብፅና በምሥራቅ አፍሪካ የሠሩ ሲሆን በዲቁናም አገልግለዋል፡፡ በ1970 ዓ.ም. በካናዳ ጋብቻ የመሠረቱ ሲሆን በካናዳ የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችላቸውን ፈቃድም አግኝተዋል፡፡ በ1981 ዓ.ም. በዚያው በካናዳ ላሉ ምእመናን አባት ይሆኑ ዘንድ ቅስና ተቀብለዋል፡፡


«Practical Sprituality» ከሚለው ከዚህ መጽሐፋቸው ሌላ «Understanding Liturgy» ፣ «The Abomination of Desolation» የሚባሉ መጻሕፍትንና በርካታ ጽሑፎችን ለንባብ አብቅተዋል፡፡ ይህንን መጽሐፍ ወደ አማርኛ እንዲተረጎም ሙሉ ፈቃደኛ የሆኑ ሲሆን በካናዳ ያሉ ኢትዮጵያውያን እንዲያነብቡትም በቤተ ክርስቲያኒቱ ድረ ገጽ ላይ የአማርኛውን ትርጉም ኮፒ እንዲለቀቅ ፈቅደዋል፡፡

## ቀደም ሲል በተርጓሚው የቀረቡ መጻሕፍት

- ክብረ ክህነት
- ቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላእክት
- ታቦት በሐዲስ ኪዳን
- ሊቀ ዲያቆናት ሐቢብ ጊዮርጊስና ሥራዎቹ

ተግባራዊ ክርስትና

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ



# ተግባራዊ ክርስትና

አቡነ አትናስዮስ እስክንድር እንደጻፉት

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ እንደተረጎመው

ኅዳር/፳፻፬

# ተግባራዊ ክርስትና

አቡነ አትናስዮስ እስክንድር እንደጻፉት

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ እንደተረጎመው

፳፻፬ ዓ.ም

FATHER ATHANASIUS ISKANDER

**SAINT MARY'S COPTIC ORTHODOX CHURCH**
**KITCHENER, ONTARIO, CANADA**
**www.stmarycoptorthodox.org**

# ተግባራዊ ክርስትና

፳፻፩ ዓ.ም.

የመጀመሪያ ኅትም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው!!

© All Rights Reserved.

__አድራሻ__ ፡- 251 091 2 08 18 29

✉ 24467 / 1000 አዲስ አበባ Email : **henok_tshafi@yahoo.com**

የሽፋን ዲዛይን ፡- ፍጹም ዓለማየሁ

# መታሰቢያነቱ

በፍጹም ትጋትና ትሕትና ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሲያገለግል ለነበረውና ለሌሎች የመኖርን ‹ተግባራዊ ክርስትና› በሕይወቱ ላሳየን ፤ በተያየን በአንድ ሌሊት ልዩነት ወደ እግዚአብሔር ለተወሰደው ለወንድማችን **ለዲያቆን ስመኝህ በላይ** ይሁንልኝ!

***‹‹ጌታ ለቤተሰቦቹ ምሕረትን (መጽናናትን) ይስጥ... በዚያ ቀን ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው!››*** ፪ጢሞ. ፩÷፲፮

# ምስጋና

ምስጋና የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ ኃይሉን በድካማችን የሚገልጥ ለልዑል ባሕርይ እግዚአብሔር ለስም አጠራሩ ክብር ይግባው! ፤ አክሊለ ርእስየ ለሆነች ቅድስት ድንግል ማርያምና ለቅዱሳን ሁሉ ምስጋና ይሁን!

ቀና ትብብር ላደረጉልኝ ለአቡነ አትናስዮስ እስክንድር ፣ ሙሉ ረቂቁን በመመልከት ገንቢ አስተያየት ለሰጠኝ ለወንድሜ ለዲያቆን ኀብረት የሺጥላ እንዲሁም በየደረስሁበት ገጽ ታግሠው ለተመለከቱልኝና ቀና ትብብራቸው ላልተለየኝ ለዲያቆን ማስደ ዋሲሁን ፣ ለዲያቆን ታደሰ ፈንታው ፣ለዲያቆን እሸቱ ማሬ አስበ መምህራንን ያድልልኝ!

‹‹ለቅኖች ምስጋና ይገባል!›› መዝ. ፴፫÷፩

## ማውጫ

መቅድም ........................................................... 5-6

መግቢያ ........................................................... 7-17

ምዕራፍ አንድ

**ትምህርት ስለ አእምሮ** ................................................ 18-30

ምዕራፍ ሁለት

**ትምህርት ስለ ፈቃድ** ................................................ 31-40

ምዕራፍ ሦስት

**የስሜት ሕዋሳትን መቆጣጠር** ...................................... 41-65

ምዕራፍ አራት

**ስለ ትውስታዎችና የፈጠራ ሐሳቦች** ................................ 66-76

ምዕራፍ አምስት

**የድፍረት ኃጢአቶች** ................................................ 77-91

ምዕራፍ ስድስት

**ጽድቅን መከተል** .................................................... 92-103

ምዕራፍ ሰባት

**የዋህነት** ............................................................ 104-113

ምዕራፍ ስምንት

**ንጽሕና** .............................................................. 114-133

ምዕራፍ ዘጠኝ

**መስዮት** ............................................................. 134-148

## መቅድም

ውድ አንባቢያን! ከዚህ ቀደም ‹ክብረ ክህነት› ፣ ‹ቅዱስ ገብርኤል ሊቀ መላእክት› ፣ ‹ታቦት በሐዲስ ኪዳን› የሚሉ መጻሕፍትንና ‹ሊቀ ዲያቆናት ሀቢብ ጊዮርጊስና ሥራዎቹ› የተሰኘ የትርጉም ሥራ ይገባላችሁ መቅረቤ ይታወሳል፡፡ አሁን ደግሞ ጸሎታችሁ ደግፋኝ ይህንን ‹ተግባራዊ ክርስትና› የሚል መጽሐፍ በእግዚአብሔር ቸርነት ተርጉሜአለሁ፡፡

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከተሰጣቸው ሁለት ዲናር (ብሉይ ኪዳንና ሐዲስ ኪዳን) በላይ አትርፈው በርካታ መጻሕፍትን የጻፉ ቅዱሳንን የያዘች ስትሆን በየዘመናቱ ለሚነሣው ትውልድ ጥያቄ ምላሽ ስትሰጥ ኖራለች፡፡ እነዚህ መሠረታዊ መጻሕፍትም በየዘመኑ ከሚኖረው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ መጠቀም እጅግ ወሳኝ ነገር ነው፡፡ የተጻፉት የሚበቁ ቢሆኑም በዚህ ዘመን ደግሞ ላለው ትውልድ በሚረዳው መንገድ ማስተማር የቤተ ክርስቲያን የዘወትር ተልዕኮዋ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ከተጻፉት እየተቀዳ እየተብራራ በየዘመናቱ መጽሐፍ ይጻፋል፡፡

አንዳንድ ጊዜ እንደ መጽሐፈ መነኮሳት ፣ ተግሣፃት የመሳሰሉ መጻሕፍት በዚህ ዘመን ላለው ትውልድ ላለው ሰውም ሆነ በዚህ ዓለም ለሚኖሩ የሚጠቅም የማይመስላቸው የዋሃን አሉ፡፡ እንዲሁም ጥልቅ ስለሆነ መንፈሳዊነት ከቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ተጠቅሶ ሲነገር ካለመሠልጠንና ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ኋላቀርነት ጋር ተያይዞ የመጣ አቋም መስሎ የሚታያቸውም አሉ፡፡ ይህ ‹ተግባራዊ ክርስትና› በሚል ስያሜ የተረጎምሁት መጽሐፍ ግን እንዲህ ዓይነት አቋም ያላቸውን ወገኖች ልብ የሚከፍል ነው ብዬ ተስፋ

አደርጋለሁ፡፡ ይህ መጽሐፍ በቀደምት መጻሕፍት የተጻፉልንን የአባቶቻችንን ታሪኮች በምን መልኩ በሕይወታችን ልንጠቀምባቸው እንደምንችል የሚያሳይና ጥልቅ መንፈሳዊነት በሥልጣኔ የትም ቢደረስ እንኳን ልናስተባብለው የማይገባ አቋም መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡

የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ አቡነ አትናስዮስ እስክንድር ይህን መጽሐፋቸውን ወደ አማርኛ እንድተረጉመው ፣ ‹መንፈሳዊነት› የሚል ርእስ ያላቸው ብዙ መጻሕፍት በመኖራቸው የመጽሐፉን ርእስ በቀጥታ ተግባራዊ መንፈሳዊነት (Practical sprituality) ብሎ በመተርጎም ፈንታ ተግባራዊ ክርስትና (Practical Christianity) ብዬ እንድተረጉመው በመፍቀድ ፣ ፎቶአቸውንና የመጽሐፉን አዲስ ኅትም በመላክ ቀና ትብብር ስላደረጉልኝ አመሰግናቸዋለሁ፡፡ በዚህ የአማርኛ ትርጉም ላይ ለኢትዮጵያውያን ምእመናን ልጆቻቸው መልእክት እንዲጽፉ ስጠይቃቸውም [1]‹‹እኔ ካህን ሆኜ ሳለ በኢትዮጵያ ላሉ እኅቶቼ እና ወንድሞቼ መጻፍን እንደ ድፍረት እቆጥረዋለሁ፡፡ በእኔ ፈቃድ የታተመ መሆኑ ከገለጽህ ይበቃል፡፡›› ብለዋል፡፡ ይህም ሌላ ተግባራዊ ክርስትና ስለሆነ በፈቃዳቸው ይህንን ሐሳብም አካትቼዋለሁ፡፡ ጸሎታችሁ ብትረዳኝ ጌታ ቢፈቅድ ብኖርም

መልካም ንባብ!

ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌ

[1] I consider it presumptuous for me to write to my brothers and sisters in Ethiopia since I am only a priest. It is enough that you say that it is being translated with my permission.

## መግቢያ

ኦሪት ዘፍጥረት ሰው በእግዚአብሔር መልክ እንደተፈጠረ ይነግረናል፡፡ በዚህም ምክንያት የሰው ልጅ በተፈጥሮው በእርሱ መልክ የፈጠረውን እግዚአብሔርን የመፈለግ ዝንባሌ አለው፡፡

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር ምሳሌም ነው፡፡ ይህም ማለት (ከሌሎች ትርጉሞቹ ጋር) የእግዚአብሔርን በመልካምነት መምሰል ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ሰው የተፈጠረው መልካምና የመልካምነት ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን ከመምሰልና ጥሩ ከመሆን ዝንባሌ ጋር ነው፡፡ ይህ ተፈጥሮአዊ ሥጦታ የሰውን ልጅ ጥሩ ወደ መሆን የሚመራው ሲሆን ሕገ ልቡና ብለን የምንጠራው ነው፡፡ (‹‹ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እንኳ ራሳቸው ሕግ ናቸውና ፤ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው አሳባቸውም እርስ በእርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ፡፡ ›› ሮሜ. ፪÷፲፬ )

አዳምና ሔዋን ሲወድቁ የሰው ልጅ ባሕርይም የወደቀ ሆነ፡፡ ይህ ጊዜም ሰው ልጅ ባሕርይ ከኃጢአት ጋር ተዋወቀ፡፡ ኃጢአትም በሰው ልጅ ፈቃድና እውቀት (ኅሊና) ላይ ትርጉም ያለው (አሉታዊ) ለውጥን አመጣ፡፡ እግዚአብሔርን ከመፈለግ ዝንባሌ ጋር የተፈጠረው የሰው ልጅም ፈቃዱ ተበላሸ፡፡ ነፃ ፈቃድ የነበረው የሰው ልጅ በኃጢአት በኩል ራስን መውደድንና ፍትወትን ተዋወቀ፡፡ ይህም የሰው ልጅን አንደኛው ክቡር የሆነ ሌላኛው

ደግሞ የተዋረደ ስሆኑ ሁለት ፈቃዶች (ለፈቃድ ምንታዌ) ዳረገው። የከበረው ፈቃድ የመጀመሪያው እግዚአብሔርን የመሻት ፈቃድ ሲሆን የተዋረደው ፈቃድ ደግሞ የራስን እርካታና ደስታ ብቻ የመሻት ፈቃድ ነው።

እንዲሁም ኃጢአት የሰው ልጅን ኅሊና በርዞ ተፈጥሮአዊውን የመልካምነት ሕግ የሚያፈርስ የክፋትን ሕግ አስተዋውቆታል። (ሮሜ. ፯፥፳፫) ይህም ቅዱስ ጳውሎስ ጥሩ አድርጎ ለገለጸው የመሳቀቅ ሁኔታ ዳርጎታል። ‹‹በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና ፈቃድ አለኝ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም። የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።››

ጌታችን ሰው በሆነ ጊዜ ፣ ሥጋችንንም ባከበረው ጊዜ ደካማ ሥጋችንን ከአምላክነቱ ጋር በማዋሐዱ የወደቀውን የሰው ባሕርይ ወደ ቀደመው በእርሱ መልክና ምሳሌ የሆነ አኗኗሩ መለሰው ፤ በመስቀል ላይ በሞተም ጊዜ ኃጢአት በባሕርያችን ላይ የነበረውን የበላይነት አስወገደ። በቅድስቲቱ ጥምቀት ደግሞ በኃጢአትና በሞት ላይ ከፈጸመው ድል ጋር በመሳተፍ የመጀመሪያውን ባሕርያችንን ዳግም ለማግኘት እንድንጋደል ዕድል ሰጠን።

በጥምቀት ዳግም ስንወለድ በእኛ የሚኖርና በእኛ (ከእኛም ጋር) የሚሠራ መንፈስ ቅዱስን እንቀበላለን። ቅዱስ መንፈሱም እግዚአብሔርን የሚመስል ባሕርያችንን ዳግም እስከምናገኝ ድረስ በምናደርገው የሕይወት ዘመን ትግል በጸጋውና በረዳትነቱ ይደግፈናል።

‹‹የሰማይ አባታችሁ ፍጹም እንደሆነ እናንተም ፍጹማን ሁኑ›› ብሎ ጌታችን ነግሮናል፡፡ (ማቴ. ፭፥፵፰) ጌታችን በጥምቀት ካደሰንና በቅዱስ መንፈሱ ከቀደሰን በኋላ ፍጹምነትን እንድንሻ ሌላው ቀርቶ የሰማይ አባታችንን ፍጹምነትን እንኳን እንድንሻ ያበረታታናል፡፡ ‹የእግዚአብሔር መልክ› ነታችንን ዳግመኛ የማግኘት እውነተኛ ትርጉምና ባሕርያችንን ዳግም የማምጣት የመጨረሻ ግብ ክርስቲያናዊ ፍጹምነት ነው፡፡ የዚህም ሽልማቱ እግዚአብሔርን የሚመስል ፍጹምነታችንን ባጣን ጊዜ ወደ ወጣንበት ወደ ገነት መመለስ ነው፡፡

ወደዚህ ፍጹምነት ለመድረስ ስለሚያስፈልጉን ነገሮች መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብዙ በሆኑ ቃላት ይነግረናል፡፡ ‹‹የዘላለም ሕይወትን አገኝ ዘንድ ምን ላድርግ?›› (ማቴ. ፲፱፥፲፮)

ጌታችንም መለሰለት ፡- ‹‹ትእዛዛትን ጠብቅ ፤ አትግደል ፣ አታመንዝር ፣ አትስረቅ ፣ በሐሰት አትመስክር ፣ አባትህንና እናትህን አክብር ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው፡፡›› (ማቴ. ፲፱፥፲፯-፲፱) ያም ሰው እነዚህን ሁሉ እንደጠበቀ በነገረው ጊዜ ‹‹ፍጹም ልትሆን ብትወድድ ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥ መዝገብም በሰማይ ታገኛለህ ፤ መጥተህም ተከተለኝ አለው›› (ማቴ. ፲፱፥፳፩) በዚህም ጌታችን ለዚህ ጎልማሳ እንዳስረዳው ሕግን መፈጸም (ፈሪሳውያን የሙሴን ሕግ ጠብቀናል ብለው እንደሚያስቡት ማሰብ) አምላክ ወደ ክርስቲያናዊው ፍጹምነት ለደረሱት ለመስጠት ቃል ወደ ገባት ወደ ሰማያዊቷ መንግሥት

አያደርስም፡፡ ይህም ጎልማሳ ወደዚህ ፍጹምነት ለመድረስ ፈቃደኛ አልነበረም፡፡

ምንም እንኳን ወደ ፍጹምነት ለመድረስ (የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት) ምን እንደሚያስፈልገን ቢነግረንም እንዴት ወደ ፍጹምነት እንደምንደርስ ግን በዝርዝር አይነግረንም፡፡ ለእያንዳንዳችን ትቶታል፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ የነገረን ‹‹የራሳችሁን መዳን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ፈጽሙ›› ብሎ ነው ፡፡ (ፊል. ፪÷፲፪)

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አሳብ በጎ ምግባር በመዳን ሂደት ውስጥ አስፈላጊው ክፍል ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ ሥራ ላይ ብቻችንን አይደለንም፡፡ በእኛ አድሮ በሚኖርና በእኛ በሚሠራው በመንፈስ ቅዱስ በኩል በእኛ የሚሠራ የእግዚአብሔር ጸጋ ጠንካራው ደጋፊያችን ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያን የመጀመሪያዎቹ ዘመናት ክርስቲያኖች መዳናቸውን ለመፈጸም በነበራቸው መሻት የመጨረሻውን መሥዋዕትነት ይኸውም ሰማዕትነትን እስከመቀበል ድረስ ምግባርን ይፈጽሙ ነበር፡፡ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ክፍለ ዘመናት ዐሥርቱ ዋና ዋና የሥቃይ ጊዜያት በሚልዮን ለሚቆጠሩ ክርስቲያኖች ወደ ፍጹምነት ለሚያደርጉት ጥረት እንደ ዕድል ሆኖላቸው ነበር፡፡ ስለ ክርስቶስ ደምን ማፍሰስም የራስን መዳን ለመፈጸም ተስማሚ ነበር፡፡

ቆስጠንጢኖስ ንጉሥ በሆነበትና ለክርስትና ዳግም ሰላም የሚሠጥን አዋጅ ባወጀበት ጊዜ (፫፻፲፫) ክርስቲያኖች መዳናቸውን ይፈጽሙ ዘንድ ሌላ መንገድ መፈለግ ነበረባቸው፡፡ ብዙዎች

ለድኅነታቸው ሲሉ ወደ ምድረ በዳ ሔዱ ፤ ስለ ክርስቶስ ሲሉ ደማቸውን ማፍሰስ ባይችሉ እንኳን ሰውነታቸው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ፣ ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርገው ሊያቀርቡ ፈለጉ። (ሮሜ. ፲፪፥፩) ‹‹የክርስቶስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።›› (ገላ.፭፥፳፬) ‹‹ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላየተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አስገዛዋለሁ።›› (፩ቆሮ. ፱፥፳፯) የሚሉት ኃይለ ቃላት መነሻዎቻቸው ነበሩ። ሌሎች ኃይለ ቃላት ደግሞ ይህንን የፍጹምነት መንገድ እንደ ሩጫ ውድድር አድርገውታል፦ ‹‹በእሽቅድድም ስፍራ የሚሮጡት ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን እንግዲያውስ ታገኙ ዘንድ ሩጡ።›› እና ‹‹በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ›› (፩ቆሮ. ፱፥፳፬ ፤ ዕብ.፲፪፥፩)

ሌሎች ጥቅሶች ደግሞ ይህንኑ የፍጹምነት ጉዞ ጦርነት ይሉታል። ‹‹ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም›› (ዕብ. ፲፪፥፬) ‹‹አብረኸኝ እንደ ክርስቶስ ወታደር ሆነህ መከራን ተቀበል ፤ የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም።›› (፪ጢሞ. ፪፥፫-፬) ሌሎች አገላለጾች ደግሞ ከአራዊት ጋር ከሚደረግ ትግል ጋር ያመሳስሉታል። ‹ባላጋራችሁ ዲያቢሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሳ አንበሳ በዙሪያችሁ ይዞራልና›› (፩ጴጥ. ፭፥፰)

በምናባቸውም ይመላለስና ያሳስባቸው የነበረው ከአጋንንት ጋር የሚያደርጉት ውጊያ ነው። ‹‹መጋደላችን ከሥጋና ከደም ጋር አይደለም ፤ ነገር ግን ከአለቆች ጋር ፣ ከኃይላት ጋር ከዚህ ዓለም ከጨለማ ገዥ ጋር በሰማያዊውም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው።›› (ኤፌ. ፮፥፲፪)

እነዚያ የክርስቶስ ሯጮች ክርስቲያናዊውን ፍጹምነት ለማግኘት ከአጋንንት ጋር ይዋጉ ዘንድ ወደ ምድረ በዳ ሔዱ። ከጥቂት ጊዜያትም በኋላ ምንኩስና ፍጹምነትን ለማግኘት ምቹ በመሆን ሰማዕትነትን የተካ ሆነ።

የራሳቸውን መዳን ለመፈጸም በሚሞክሩበት ወቅት እነዚህ የክርስቶስ ሯጮች ለእኛ ደግሞ ታላቅ ውለታን ዋሉልን። ክርስቲያናዊውን ፍጹምነት ላይ እንዴት መድረስ እንደሚቻል የሚስረዳ ሰፊ የጽሑፍ ቅርስ አስተላለፉልን። የግብጽ በረሃም ፍጹምነትን ፍለጋ ምርምር የሚካሔድበት ዩኒቨርሲቲ ሆነ። የበረሃው አባቶችም ከፍጹምነት ፍለጋ ውስጥ ዛሬ መንፈሳዊነት ብለን የምንጠራውን ሳይንስ (ፍልስፍና) ፈጠሩ። በዚህ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ምርምሮች ተደርገዋል ፣ በውድቀትም በስኬትም የተጠናቀቁ ሙከራዎችም ተካሒደዋል። የእነዚህ ሙከራዎች ውጤቶችም የበረሃ አበውን ጥበብ ፈልገው በሚመጡ ሰዎች አማካኝነት ገሃድ ወጥተዋል። አባቶች ተገድደው በሚሆንበት ጊዜ ብቻ እንጂ ራሳቸው የራሳቸውን አባባል አይጽፉም ፣ ስለ ልምዶቻቸውም አይናገሩም።

የበረሃ አባቶች ኃጢአቶችን ዘርዝረው አስቀምጠዋቸዋል ፣ ለኃጢአት ስለሚያጋልጡ ነገሮችም እንዲሁ። በተጨማሪም እንዴት ከኃጢአቶች ጋር መዋጋት እንደሚቻል በዝርዝር ተናግረዋል።

ልዩ ልዩ ጸጋዎችንም ለይተው አስቀምጠዋል ፣ በየምድቡም አስቀምጠዋቸዋል ፤ እነዚህ ጸጋዎችም ላይ ለመድረስ የሚቻልባቸውን መንገዶችም እንዲሁ አስረድተዋል።

በበረሃውያን አባቶችን አባባል በተመለከተ አስደናቂው ነገር ስምምነታቸው ነው። አንዳንዶቹ በምሥራቅ በረሃ ሲኖሩ ሌሎቹ በምዕራብ በረሃ ይኖራሉ ፤ ሌሎቹ ደግሞ በላዕላይ ግብጽ ፤ ይህ ሆኖ ሳለ ግን የሁሉም የሐሳብ ድምዳሜ ግን አንድ አይነት ነው። ይህ የሐሳብ አንድነትም ነው አባባሎቻቸውን ልብ የሚነኩ የሚያደርጋቸው። ልዩነታቸው በአገላለጽ ስልት ብቻ ነው።

የበረሃውያን አባቶች መንፈሳዊነት ሁለቱ በጣም ጠቃሚ ባሕርያት የሚከተሉት ናቸው ፦ የመጀመሪያው በደቀመዝሙርነት (ተማሪነት) ላይ ያላቸው ጥብቅነት ነው። የመንፈሳዊነትን ጥበብ ለመማር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ራሱን ከመምህሩ ጋር ማጣበቅ ይኖርበታል። መምህራኑ ለአርድእቶቻቸው ልዩ ልዩ (ለክብር) የሚያበቁ ጥብቅ ፈተናዎችን ስለሚፈትኗቸው ይህ ጉዳይ ቀላል አልነበረም። ቅዱስ ጳኩሚስ ረድእ ለመሆን ተቀባይነት ከማግኘቱ በፊት በቅዱስ አባ ጵላሞን በአት ደጃፍ ለሦስት ቀናት እንዲለምን ተትቶ ነበር።

ይህንን የመንፈሳዊነት ሳይንስ የመሠረቱና የመንፈሳዊነት ጥናትን ዩኒቨርሲቲ ያቋቋሙ በእርግጥም እንደ አባ ጳውሊና እንደ ቅዱስ እንጦንስ እንደ ቅዱስ መቃርስ ያሉ ፋና ወጊዎች ነበሩ።

ሁለተኛው ጠቃሚ መመሪያ ደግሞ በራስ መተማመንን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ነው። አንድ ረድእ እርሱን ለማለማመድ ሙሉ ሓላፊነትን ለሚወስደው ለመምህሩ በጭፍን (ያለ አንዳች ጥያቄ) መታዘዝ ይኖርበታል። መምህራኑ የአርድእቶቻቸውን ታዛዥነት ለመፈተን ለእኛ ለመረዳት የሚያዳግቱንን ልዩ ልዩ መንገዶች ይጠቀማሉ። ልክ ለረድአቸው ደረቅ በትር ሠጥተው ይህንን አጠጥተህ አለምልም እንዳሉት አባት ያለ ፈተና ማለት ነው። ይህ ታዛዥነትም ለከንቱ አልነበረም ፤ ከሦስት ዓመታት በኋላ ዱላው መብቀልና ፍሬን መስጠት ጀምሮ ነበር። ሌላው ረድእ ደግሞ በአቅራቢያው ጅብ እንዳለ ለመምህሩ ቢነግራቸው ‹‹ይዘኸው ና›› ብለው አዝዘውት ነበር። ዓይኖቹን በእምነት ጋርዶ (በጭፍን እምነት) ወደ መምህሩ ጅቡን ይዞ ቢመጣ መምህሩ ‹‹መልሰው ጅብ ይዘህ ና አልኩህ እንጂ መች ውሻ አምጣ አልኩህ?›› ብለውታል።

እነዚህን መመሪያዎች በእምነት መከተል የቻሉ ልምምዳቸውን ፈጽመው እነርሱም መምህራን ይሆናሉ ፤ ከመምህራኖቻቸው የተማሩትንም መልሰው ያስተምራሉ። በተለመደው ሥርዓት በበረሃውያን አበው አባባሎች ‹‹አባ እንዲህ ብለው ነበር›› ‹‹ብፁዕ አባታችን እንዳሉት›› የሚሉ አነጋገሮች የተለመዱ ናቸው ፤ ደቀ መዝሙሩ ለሌሎች የሚናገረው የመምህሩን አባባሎች እንጂ የራሱን አይደለም። በኋላም የእርሱ

ደቀ መዛሙርትም የሚናገሩት የእርሱን አባባሎች ይሆናል እንዲህ እያለም ይቀጥላል፡፡

ምንም እንኳን አስደናቂዎች ቢሆኑም የበረሃውያን አበው አባባሎች ለሁሉም ሰው የሚሆኑ አይደሉም፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ምእመናን በመልእክቱ እንዲህ ሲል ተናግሯቸዋል ፡- ‹‹ገና ጽኑ መብልን ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተትን ጋትኋችሁ ፤ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም፡፡›› ፩ቆሮ. ፫፥፪

በበረሃውያን አባቶች አባባሎች ላይ ተመርኩዘው ስለ መንፈሳዊነት በርካታ መጻሕፍት ተጽፈዋል፡፡ የ‹ጆን ክሊማከስ› ‹ዘ ላደር ኦፍ ዲቫይን አሴንት› /**“The Ladder of Divine Ascent”**/ እና የ ‹ጆን ካሲያንስ› ሁለት መጻሕፍት ‹ዘ ኢንስቲቲውትስ› እና ‹ዘ ኮንፍረንስስ› /**“The Institutes” and “The Conferences”**/ ለእዚህ ዓይነቶቹ መጻሕፍት ምሳሌዎች ናቸው፡፡

የስድስተኛው ክፍለ ዘመን የሩስያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባት ቴዎፋን ባሕታዊ የበረሃ አባቶችን አባባሎችን በመሰብሰብና እንዴትም ሥራ ላይ ማዋል እንደሚቻል የራሱን አስተያየቶች በማከል ለመንፈሳዊነት ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ይህ መጽሐፍ በመነኮስ ለመነኮሳት የተጻፈ መጽሐፍ ነበር፡፡

‹የብሕትውና መንገዶች› የተሰኘው መጽሐፍ ደግሞ ከላይ ካሉት የተለየ ነው፡፡ የተጻፈው በሃያኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ በአውሮፓ (ፊንላንድ) ይኖር በነበረ ኦርቶዶክሳዊ ክርስቲያን የተጻፈ ነበር፡፡ መጽሐፉ የበረሃውያንን አበው መንገዶች

በዓለም በሚኖረው ተራ ሰው ዘንድ እንዴት መተግበር እንደሚችሉ የሚያስረዳ መጽሐፍ ነው። ይህን መጽሐፍ የራሱን መዳን ለመፈጸም ለሚተጋ ሰው ሁሉ ያነብበው ዘንድ የምመክረው ነው።

ይሁንና ሁሉም እንደሚያውቀው በሃያኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የነበረው ሕይወት በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ካለው ሕይወት እጅግ የተለየ ነው። በወቅቱ የነበረው ግብረ ገብና ፈተናዎቹ የተለዩ ናቸው። በየዕለቱ ዓለም በአሉታዊ መንገድ እየተለወጠች ነው።

የበረሃውያን አባቶችን መንገዶችና አካሔዶችን ልንዋስ እና በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በሚኖሩ ወጣት ኦርቶዶክሳዊያን በሚያጋጥማቸው ፈተና ላይ እንደ መፍትሔ ልናውለው ግን እንችላለን።

ከዚህ በታች የምንመለከታቸው ልዩ ልዩ ጽሑፎችም ለዚሁ ዓላማ የሚደረጉ ሙከራዎች ናቸው። ጽሑፎቹ በ፳፻፩ዓ.ም. ዐቢይ ጾም ላይ በኪችነር ኦንታሪዮ ለቤተ ክርስቲያናችን ወጣቶች በሰጠኋቸው ስብከቶች ላይ የተመረኮዙ ናቸው።

*ለአንባቢዎቻችን የተሰጠ ማሳሰቢያ* ፡- እነዚህ ጽሑፎች እንዲህ እንዲህ አድርጉ የሚል መልእክት ያላቸው ማዘዣዎች አይደሉም። በጽሑፎቹ ላይ የምታነብቧቸውን ነገሮች ለመተግበር ከመነሣታችሁ በፊት እባካችሁ የንስሐ አባታችሁን አማክሩ! አንዳንዶቹ መንፈሳዊ ልምምዶች ለእናንተ የሚመጥኑ ላይሆኑ ይችላሉ ፤ በዚህ ጉዳይ ሊያማክሯችሁ የሚችሉት የንስሐ አባቶቻችሁ ብቻ ናቸው።

በተከታታዩ የክርስቲያናዊ ፍጹምነት ሒደት የመጀመሪያው ደረጃ ፈቃድንና ኅሊናን ዳግም አንድ አድርጎ እግዚአብሔርን በመልክና በምሳሌ ወደ መምሰል መመለስ ነው። ምእራፍ አንድና ሁለት የሰው ልጅ ሕሊናና ፈቃድ ምን መምሰል እንዳለበት ያብራራሉ።

ቀጣዮቹ ሦስት ምእራፋት በግብረ ገብ ሥርዓት እና ከኃጢአት ጋር በመዋጋት ላይ ያተኩራሉ። የስሜትና የአሳብ ኃጢአቶችም በዚህ ላይ ይዳሰሳሉ። ቀጥሎ ያለው ምእራፍ ደግሞ ስለ ድፍረት ኃጢአቶችና ስለተሠወሩ ኃጢአቶች ያትታል። የመጽሐፉ መጨረሻ ክፍል ደግሞ ወደ መንፈሳዊ ፍጹምነት ለመድረስ የሚደረገውን ጉዞ ለመጀመር አስፈላጊ የሆኑ ባሕርያትን ይዘረዝራል።

እግዚአብሔር እነዚህን ጽሑፎች ለስሙ ክብር ያድርጋቸው!

አባ አትናስዮስ እስክንድር

፳፻፩ በዓለ ዕርገት

ምእራፍ አንድ

# ትምህርት ስለ አእምሮ

፩. ሕሊናን ከጎጂና ጥቅም አልባ እውቀት ጠብቅ

፪. በሕሊናህ ውስጥ መንፈሳዊ እውቀትን ትከል

## ጥቅም አልባ እውቀት

ክርስቲያናዊ ፍጹምነትን ለማግኘት የምትፈልግ ከሆነ ሕሊናህን ለነፍስህ ከማይጠቅም ወሬ መጠበቅ አለብህ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዘመኑ የመረጃና የመረጃ ጥበብ ዘመን ነው። ዓለም በቲቪ ፣ በመጻሕፍት ፣ በጋዜጦች ብቻ ሳይሆን በመረጃ መረብ ጭምር የሚያጥለቀልቅ መረጃን ከምንጊዜው በላይ እያቀረበችልን ነው። ነገር ግን ይህ ጥቅም የለሽ መረጃ እኔ የአእምሮ ብክለት ብዬ ለምጠራው ችግር ይዳርጋል። በዚህ ዘመን ለሥራቸው ውጤታማነት ቢጠቅምም ባይጠቅምም መረጃን በመረጃነቱ ብቻ የሚፈልጉ የመረጃ ሱሰኞች አሉ።

ቅዱስ ጳውሎስ በ፩ቆሮ.፪÷፪ ላይ እንዲህ ይለናል፦ ‹‹በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር ላላውቅ ቆርጬ ነበር›› ቅዱስ ጳውሎስን የሚያሳስበው እውቀት ኢየሱስና ሕይወትን የሚሰጠው መሥዋዕትነቱ ነው።

መክ. ፩÷፲፰ ላይ ደግሞ ፡- ‹‹በጥበብ መብዛት ትካዜ ይበዛልና እውቀትንም የሚጨምር ኀዘንን ይጨምራልና›› ይላል፡፡

ለጥቅም አልባ እውቀት የመጀመሪያው ምሳሌ ዜናን ከመጠን በላይ መመልከት ነው፡፡ በዙሪያችን ባለው ዓለም ላይ ምን እየሆነ እንዳለ ማወቅ መልካም ነው ፤ ይሁንና ክርስቲያናዊውን ፍጹምነት የምትፈልጉ ከሆነ በየቦታው በእያንዳንዱ ደቂቃ የሚሆነውን እያንዳንዱን ነገር ስለማወቅ መጨነቅ ትርፍ ያለው ነገር አይደለም፡፡ ሰዎች ዜናን ለመስማት ካላቸው የማይረካ ጉጉትና ጥማት የተነሣ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች የሃያ አራት ሰዓት ዜና ሥርጭትን ሊጀምሩ ችለዋል ፣ የሬድዮ ጣቢያዎችም ቀጥለውበታል፡፡

ይህን ምሳሌ ውሰዱ የኦ ጄ ሲምትሰን ተከታታይ የፍርድ ሒደት በዓለም ዙሪያ የነበሩ እጅግ ብዙ ሰዎች ከማንኛውም ክስተት በላይ ተመልክተውታል፡፡ የገና ጨዋታንስ ይሁን እረዳለሁ ረዥም የፍርድ ሒደትን መከታተል ግን ምን ሊባል ይችላል? ከዚህ ምን ላገኝ እችላለሁ? ለነፍሴም ለሥጋዬም ለሕሊናዬም ምንም አላገኝም!

በዐቢይ ጾም ወቅት የማደርገውን ልንገራችሁ ፤ በሬድዮ ዜናን ከመስማት ፣ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን ከማንበብ እከለከላለሁ፡፡ (እንደምታውቁት ቲቪ በዐቢይ ጾም ወቅት እንዳንጠቀም ተስማምተናል፡፡) እመኑኝ! ምንም ነገር አያመልጠኝም ፤ አይጎድልብኝም ፤ ይልቁንስ ሕሊናዬ ከመረጃ ብክለት ነፃ ይሆናል ፤ ስለዚህ በትክክል እንደሚሠራ አምናለሁ፡፡

የአንድ መነኩሴ ታሪክ ሰምተን ነበር ፤ ይህ መነኩሴ ከሌሎች መነኮሳት ጋር ሲነጋገር ቆይቶ ወደ በዓቱ ከሔደ በኋላ እጅግ በተደጋጋሚ በአቱን ሲዞር አንድ መነኩሴ ተመለከተውና ምን እያደረገ እንደሆነ ጠየቀው ፤ እርሱም መለሰ ‹‹ስናወራቸው የነበርናቸውን ዓለማዊ ወሬዎች እያስወገድኩ ነው ፤ ወደ በአቴ ይገቡ መግባት አልፈልግም››

ሁለተኛው የማይጠቅም እውቀት ምሳሌ ደግሞ ከንቱ የማወቅ ፍላጎት ነው፡፡ አዋቂ ለመሆን ብቻ ሲባል ስለ ብዙ ነገሮች የማወቅ ጥማት፡፡ ይህ እንዴት ሊጎዳኝ ይችላል? መልካም አበው እንዳሉት ይህ በጠቅላላ እውቀት መሞላት (መጠቅጠቅ) ከሌሎች የተሻለ አዋቂ እንደሆንኩ ወደማሰብና ወደ ኩራትና ትዕቢት ይመራኛል፡፡ እውቀቴንም በሌሎች ፊት ማሳየት ስለምፈልግ ወሬኛ እሆናለሁ፡፡ ባሕታዊው ቴዎፋን እንዳለው ከሆነ በመጨረሻ አእምሮአችን ራሱ የምናመልከው ጣዖት ይሆንብናል፡፡ ሃሳበ ግትር እንሆናለን ፤ ሁሉን እስካወቅን ድረስም ሌሎችን ለማማከርም ሆነ ምክርን ለመቀበል ፈቃደኞች አንሆንም፡፡ ይህም በመንፈሳዊ ጉዳዮችም ጭምር በራስ ወደ መደገፍ የሚመራን የሕሊና ትዕቢት ሲሆን እጅግ አደገኛ ነው፡፡

ክርስቲያናዊውን ፍጹምነት መከተል ከፈለጋችሁ ሕሊናችሁን ከዚህ ዓይነቱ የእውቀት ሱስ ማላቀቅ አለባችሁ፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ በ፩ቆሮ.፫÷፲፰–፲፱ ላይ ፡- ‹‹ማንም በዚህች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን፡፡ የዚህች ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነውና፡፡›› መንፈሳዊ ጥበብና

ዓለማዊ ጥበብ እጅ ለእጅ ተያይዘው ሊሔዱ አይችሉም፡፡ የዚህን ዓለም ጥበብ እጅግ የሚሹ ሰዎች ብዙ ጊዜ በእግዚአብሔር የማያምኑ ይሆናሉ፡፡ በትዕቢተኛ አእምሮአቸው ተወጥረው አእምሮአቸውን የፈጠረውን እግዚአብሔርን ይክዳሉ፡፡ በዚህ የተነሣም ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ጢሞቴዎስ ሆይ በውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ ፤ ይህ እውቀት አለን ብለው አንዳንዶች ከእምነት ስተዋልና ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን አሜን!›› ፩ጢሞ. ፮÷፳–፳፩

በመዝ. ፸፪÷፳፪–፳፬ ላይ ነቢዩ ዳዊት እንዲህ አለ ፡- ‹‹እኔ የተናቅሁ ነኝ አላወቅሁምም ፤ በአንተ ዘንድም እንደ እንስሳ ሆንሁ፡፡ እኔ ግን ዘወትር ከአንተ ጋር ነኝ ቀኝ እጄንም ያዝኸኝ፡፡ በአንተ ምክር መራኸኝ ፤ ከክብር ጋር ተቀበልኸኝ፡፡›› ጠቢብ ለመሆን ሲባል ሞኝ የመሆን ትርጉም ይህ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነትህን ከገለጥህ ቀኝ እጅህን ይይዝሃል ፣ በእርሱም ምክር ይመራሃል ፤ ከክብርም ጋር ይቀበልሃል፡፡

የማወቅ ፍላጎት የሎጥን ሚስት ለጥፋት ዳርጎአታል፡፡ እንዲሁም ጌታችን በሐሳዊው መሲሕ ጊዜ ስለማወቅ ጉጉት በተመሳሳይ ምሳሌ አስጠንቅቆናል፡፡ ‹‹እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ስፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሽሹ፥በሰገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ፥በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ፡፡››

ይህም ማለት ሐሳዊውን መሲህ ከማግኘት ወይም ከማየት ወይም ከመስማት አሻፈረኝ ማለትና መሸሽ ማለት ነው፡፡ በጠንካራ የማወቅ ፍላጎት ለማየት የሚሞክሩ ሰዎች ግን እንደ ሎጥ ሚስት ይጠፋሉ፡፡ ሉቃ. ፲፯÷፴፩ ተመሳሳይ አሳብ የሚነግረን ሲሆን በሎጥ ሚስት ስኅተት ዳግም እንዳንወድቅ ያሳስበናል፡፡ በዚያን ዕለት ‹‹በዚያም ቀን በሰገነት ያለ በቤቱ ያለውን ዕቃ ሊወስድ አይውረድ፥ እንዲሁም በእርሻ ያለ ወደ ኋላው አይመለስ፡፡የሎጥን ሚስት አስቡአት፡፡››

በእነዚያ ዕለታት ሰው ቲቪ ለማየት ወይም ሬድዮ ለመስማት ወይም የቅስቀሳ ስብሰባዎቹን ወይም ስለእርሱ ማንኛውንም ነገር ከማወቅ ራስን መግታት አለበት፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ ያስጠነቅቀናል፡፡ ‹‹‹ሂዱ ግን አትመኑበት› አላለንም ፡፡ ነገር ግን አትሒዱ ከእርሱም ተለዩ አለን እንጂ ፤ ምክንያቱም በዚያን ጊዜ ድንቅ ነገሮች እና ታላላቅ ተአምራት ይደረጋሉና ነው፡፡›› ይህንን ማስጠንቀቂያ ወደ ጎን ትተህ የራስህን የማወቅ ፍላጎት ከተከተልህ ትጠፋለህ፡፡

በዐቢይ ጾም ወቅት ቴሌቪዥን ከመመልከት መከልከል መልካም የሆነው ለዚህ ነው፡፡ ራሳችንን መግታት ከለመድን ደግሞ ሐሳዊው መሲህ ቢመጣም ከማየት መከልከልና ወደ እርሱ ይሰበስበን ዘንድ በደመና የሚመጣውን ጌታ በመጠባበቅ ዓይናችንን ወደ ሰማይ ማቅናት ይቻለናል፡፡

ሌላው የከፋ የማወቅ ፍላጎት ደግሞ ስለ አስማት ፣ ጥንቆላና ስለመሳሰሉት የማወቅ ፍላጎት ነው፡፡ ይህም በአጋንንት

ወደ መያዝ ራስን ወደ ማጥፋትና ሰዎችን ወደ መግደል የሚያደርስ ነው፡፡

እስከ አሁን ጥቅም ስለሌለው እውቀት ተነጋገርን ፤ አሁን ደግሞ እስቲ ስለ ጎጂ እውቀት እናውራ፡፡ ይህም ስለሌሎች ሰዎች የማወቅ ፍላጎት ሲሆን መጽሐፍ ቅዱስ ‹በነገር የሚገባ› የሚለው ነው፡፡ ፩ጴጥ. ፬÷፲፭ እንዲህ ይላል ፡- ‹‹ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል››

ስለሌሎች ሰዎች ጉዳይ የማወቅ ሱስ የአሉባልታና የሐሜት ሥር ነው፡፡ ዲያቢሎስ የሰውን ጉዳይ ለማወቅ የምትፈልጉት ልትረዷቸው ስለምትችሉ ነው ብሎ ሊያሳምናችሁ ይችላል፡፡ ነገር ግን በምን ዓይነት በሽታ እንደታመመ ሳላውቅ ለታመመ ሰው ልጸልይ እችላለሁ፡፡ አንድን ሰው ቤቱን በስንት እንደገዛው ሳላውቅ ወደ አዲስ ቤቱ ሲዘዋወር ላግዘው እችላለሁ፡፡ አንድን ሰው ምን ያህል ደመወዝ እንደሚከፈለው ሳላውቅ ስላገኘው አዲስ ሥራ እንኳን ደስ ያለህ ልለው እችላለሁ፡፡

ከሌሎች በተለየ ወጣቶች የጓደኞቻቸውን ምሥጢሮች የማወቅ ሱስ አለባቸው፡፡ ‹ምሥጢርህን ካልነገርከኝ ጓደኛዬ አይደለህም› ‹ምሥጢሬን ልነግርህ የምችለው የአንተን ከነገርከኝ ብቻ ነው› ይባባላሉ፡፡ ይህ ግን ጎጂ እውቀት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ‹በነገር መግባትን› ነፍሰ ገዳይ የመሆንና የመስረቅ ያህል ክፉ መሆኑን ይገልጻል፡፡

ብዙ ሰዎች ስለእነርሱ ማወቅ ስለሚፈልጉ ወዳጆቻቸው ተማርረው ይነግሩኛል፡፡ አንዳንድ ሰዎች እንደውም ‹‹ሰዎች የግል ጉዳዮቼን እንዲያውቁብኝ ስለማልፈልግ ለመዋሸት እገደዳለሁ›› ብለውኛል፡፡ ለዚህ የምሰጠው መልስ ግን ‹‹አትዋሹ! ጉዳዩ የግል ጉዳይ መሆኑን ብቻ ንገሯቸው›› የሚል ነው፡፡ ከተቆጡና ሊያናግሯችሁ ካልወደዱ አትጨነቁ ፤ እውነተኛ ጓደኞቻችሁ አይደሉም ማለት ነው፡፡ እውነተኛ ጓደኞች ምሥጢርን ለማውጣጣት ከመገፋፋት ይልቅ የጓደኞቻቸውን የግል ጉዳዮች ያከብራሉ፡፡

## መንፈሳዊ እውቀት

ሁላችንም መጽሐፍ ቅዱስን አንብበናል ጥቅሶችንም እናስታውሳለን ፤ ይህ ሆኖ ሳለ ግን በእርግጥ ጥቅሶቹ የያዟቸውን መንፈሳዊ ጽንሰ ሃሳቦች በአእምሮአችን ውስጥ ተክለናቸዋል?

በዘዳ. ፮÷፮-፱ ላይ ተነግሮናል ፡- ‹‹እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ፡፡ለልጆችህም አስተምረው፥ በቤትህም ስትቀመጥ፥ በመንገድም ስትሄድ፥ ስትተኛም፥ ስትነሣም ተጫወተው፡፡ በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው በዓይኖችህም መካከል እንደክታብ ይሁንልህ፡፡ በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው፡፡››

ይህም ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያነበብነው ነገር በሚገባ ቀስመን የአስተሳሰባችን ሒደት አካል እስከሚሆኑ ድረስ በልባችንና በአእምሮአችን ላይ ማተም አለብን ማለት ነው፡፡ እነዚህን ምሳሌዎች እዩ፡-

መጽሐፍ ቅዱስ በሉቃስ ፮÷፳፮ ላይ እንዲህ ሲል ነግሮናል ‹‹ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ፤ አባቶቻቸው

ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ ያደርጉላቸው ነበርና፡፡›› እንዲሁም በድጋሚ በሉቃስ ፮÷፳፪–፳፫ ላይ ‹‹ሰዎች ስለ ሰው ልጅ ሲጠሉአችሁ ሲለዩአችሁም ሲነቅፉአችሁም ስማችሁንም እንደ ክፉ ሲያወጡ፥ ብፁዓን ናችሁ፡፡እነሆ፥ ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ ዝለሉም፤ አባቶቻቸው ነቢያትን እንዲህ ያደርጉባቸው ነበርና፡፡›› ይላል፡፡

በዚህም መሠረት ከመመስገን ይልቅ መነቀፍ የበለጠ ብፅዕና ነው፡፡ ሰዎች ሲያመሰግኑኝ ለእኔ መንፈሳዊነት አደገኛ እንደሆነና ሰዎች ሲነቅፉኝና በሐሰት ክፉ ሲናገሩብኝ ማመስገንን በአእምሮዬ ውስጥ ተክዬዋለሁ? የማይቻል ነገር ነው ልትሉ ትችላላችሁ ግን መሆን ያለበት ነው፡፡

አቡነ ዮሐንስ የተባሉ አባት በየሳምንቱ ሐሙስ ሐሙስ በአቅራቢያቸው ወዳለ አንድ መንደር ለማስተማር ይሔዱ ነበር፡፡ በግብፅ እንደተለመደው ወደዚያች መንደር ለመሔድ ሲሳፈሩ ከአንድ ሌላ ሰው ጋር መዳበል ነበረባቸው፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ አክራሪ ሙስሊም ሁልጊዜ በተመሳሳይ ሰዓት አብሯቸው ይሳፈር ነበር፡፡ ሊሳፈሩ ሲገቡ ታዲያ ፊቱን ዞር ያደርግና ይተፋ ነበር! ይህን አስነዋሪ ድርጊት ለዓመታት ይፈጽም ነበር፡፡ አንድ ቀን ጳጳሱ ሊሳፈሩ ሲመጡ ያ ሰው አልነበረም፡፡

አቡነ ዮሐንስ ከልባቸው አዝነው እግዚአብሔርን መጠየቅ ጀመሩ ‹‹ጌታዬ ይህንን በረከት ለምን አስቀረህብኝ? ይህንን በረከት ከዚህ በላይ እቀበል ዘንድ እንደማልገባ የወሰንከው በኃጢአቶቼ መብዛት ይሆን?››

ሌላው የተቀደሰ ትውስታ ባለቤት ደግሞ የማይታክቱት የእግዚአብሔር ሠራተኛ ጳጳሱ አቡነ ሳሙኤል ነበሩ፡፡ እኚህ አባት እንደተለመደው ብዙ ጠላቶች ነበሯቸው ፤ እጅግ አስጸያፊ መልእክቶችን እየጻፉ በደብዳቤ መልክ ይልኩላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም እነዚህን አስጸያፊ ስድቦች በመሳቢያቸው ውስጥ ያስቀምጡአቸው ነበር፡፡ በሚከፋቸውና በሚተክዙ ጊዜ ማኅደራቸውን ከፍተው እነዚህን ደብዳቤዎች ያነብቡ ነበር ፤ ከዚህ በኋላ የመታደስ ስሜት ይሰማቸዋል ምክንያቱም ነቀፋዎቹን ሲያነብቡ በእያንዳንዱ ስድብ ውስጥ በረከት እንዳለ ስለሚያዩ ነበር፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የምናነብበውን በልባችን ውስጥ መትከል የምንለው እንግዲህ ይህንን ነው፡፡

አባቶቻችን ስድብን የመቀበልና ምስጋናን ያለመቀበል ሥልጠናን በተገቢው መንገድ ወስደዋል፡፡ ‹ፓራዳይዝ ኦፍ ፋዘርስ› የተባለው መጽሐፍ አእምሮን ስለመግዛት ሁለት አስደናቂ ታሪኮችን ይነግረናል፡፡

አንድ አባት ወጣኒ ደቀመዝሙሩን አለው ‹ሒድና ሙታንን ተሳደብ› ፤ ወደ መቃብር ሔዶ ቀኑን ሙሉ ሙታንን ሲሳደብ ዋለ፡፡ በቀጣዩ ቀን ደቀ መዝሙሩን አለው ‹ሒድና ሙታንን አመስግን!› ወደ መቃብር ሔዶ ምስጋናውን ሲያወርድ ዋለ፡፡ ማታ ሲመለስ መምህሩ ጠየቀው ‹‹በሰደብካቸው ጊዜ ሙታኑ ተሰማቸው?›› ‹‹የለም አልተሰማቸውም›› አለና መለሰ ፤ ደግሞ ጠየቀው ‹‹ስታመሰግናቸውስ?›› አለው ፤ ‹‹የለም አልተሰማቸውም›› አለው፡፡ አረጋዊውም ‹‹ሒድ አንተም እንዲህ ሁን!›› ብሎ ነገረው፡፡

ሌላው ታሪክ ደግሞ መነኩሴ ይሆን ዘንድ ወደ ገዳም ስለሔደ የሀብታም ቤተሰብ ልጅ ስለሆነ ወጣት ነው፡፡ መምህሩ ‹‹ስድብን በደስታ ለመቀበል ራስህን አስለምድ›› ብለው ነገሩት፡፡ ዙሪያውን ቢፈልግ በገዳሙ ውስጥ እርሱን የሚሰድበው የለም፡፡ ስለዚህ ወደ መንደር ሔዶ ወደ ገዳም መጥቶ ስድብን በደስታ መቀበልን እስከሚለምድ ድረስ እንዲሰድበው አንድ ሰው ቀጠረ፡፡

አንድ ቀን ከሌሎች መነኮሳት ጋር ወደ ከተማ ተልኮ ሳለ አንድ ቁጡ ሰው የስድብ ናዳ ሲያወርድበት በደስታ መሳቅ ጀመረ፡፡ ሌሎቹ መነኮሳት ለምን እንደሚስቅ ቢጠይቁት ‹‹ለዚህ (ለመሰደብ) ስከፍል ነበር ፤ አሁን ግን በነፃ አገኘሁት!›› አላቸው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ በ፩ዮሐ. ፪÷፲፭ ላይ እንዲህ ይለናል ፡- ‹‹ዓለምን ወይም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፤ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም፡፡›› እንዲሁም በያዕቆብ ፬÷፬፡- ‹‹ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል፡፡›› ይላል፡፡

ይህንንስ በአእምሮአችን ውስጥ ተክለነው ይሆን? የፍጹምነት መንገድ ዓለምንና በዓለም ያሉትን ነገሮች ሁሉ መናቅ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ከሁሉ ይልቅ ስለሚበልጥ ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ስለ ጌታዬ እውቀት ነገር ሁሉ ጉዳት እንዲሆን እቈጥራለሁ፤ ስለ እርሱ ሁሉን ተጐዳሁ፥በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጕድፍ እቈጥራለሁ›› ብሏል፡፡ ፊል. ፫÷፲፰

ቅዱስ ጳውሎስ በዓለም ያለውን ነገር ሁሉ እንደ ጉድፍ ቆጥሮ የክርስቶስን እውቀት ያገኝ ዘንድ ሁሉን አጣለሁ አለ፡፡ የቆሻሻ ገንዳ! በልባችሁ ውስጥ ይህች ዓለም ትልቅ የቆሻሻ ገንዳ እንደሆነችና በውስጧም ያሉት ሁሉ ቆሻሻና ጉድፍ መጣያ እንደሆኑ ታስባላችሁ? አሁንም መኪና ባየሁ ጊዜ የምመሰጥና በአድናቆት የማከብረው ከሆነ ይህ መኪና የማመልከው ጣዖት አልሆነብኝም ትላላችሁ?

አስታውሳለሁ አንድ ቀን ወጣቶችን አሳፍሬ ከሚሲሳውጋ ወደ ኪችነር እያመጣኋቸው ነበር፡፡ ሁሉም የሚያወሩት ስለ መኪኖች ነበር፡፡ የመኪኖች የተጨራመተ አካል በጭነት መኪኖች ላይ ተጭኖ አይታችሁ ታውቃላችሁ? ወይም ዝጎ የወደቀ የተጣለ መኪና አላያችሁም? ለዓይን ያስቀይማል፡፡ ሁልጊዜ መኪና ስትመኙ አስቀያሚ የብረት ቁርጥራጭ እንደሚሆን አስቡ፡፡ አእምሮአችሁን ዓለማዊ (ምድራዊ ነገሮችን) እንዲንቅና መንፈሳዊውን ፍጹምነት እንዲመኝ አለማምዱት፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል ፡- ‹‹ትዕግሥተኛ ሰው ከኃያል ሰው ይሻላል፥ በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስዱ ይበልጣል፡፡›› ምሳ. ፲፮÷፴፪

ቁጣን መቆጣጠር ጥንካሬ እንጂ ደካማነት አለመሆኑን በአእምሮዬ ውስጥ ቀርጬዋለሁ? የቁጣን ቃላት በቁጣ ቃላት ወይም ክፋን በክፉ መመለስ ቀላል ነው ፤ ቀላሉና የደካሞች መንገድ ይህ ነው፡፡ ንዴትን መቆጣጠርና እንደ ክፉ አመጣጥ አለመመለስ ግን ጥንካሬና ታላቅነት ነው፡፡ አንዴ ሲመቱ ሌላን

ጉንጭ መስጠትስ ፈሪነት ሳይሆን ጀግንነት እንደሆነ በአእምሮአችሁ ውስጥ ተተክሏል? እንደማይቻል ትነግሩኛላችሁ እኔ ግን ይቻላል እላችኋለሁ፡፡

በዘጠናዎቹ ውስጥ የተፈጸመ እውነተኛ ታሪክ እነሆ፡፡ አንድ መነኩሴ የገዳሙን አስፈላጊ ዕቃዎች ለማሳደስ ተልኮ ወደ ካይሮ መኪና እየነዳ ይሔዳል፡፡ ከካይሮ ጠባብ ጎዳናዎች በአንዱ እየነዳው የነበረው መኪና አንድ የቆመ መኪናን ጭሮት ያልፋል፡፡ መነኩሴው የመኪናውን ባለቤት አጠያይቆ ያገኘውና ይቅርታ ጠይቆ ለማሳደሻ ልክፈል ይለዋል፡፡ የመኪናው ባለቤት ግን አክራሪ ነበር ፤ በክርስቲያኖች ላይ ያለውን ጥላቻ ለመወጣት ጥሩ አጋጣሚ ሆነለት፡፡ ስለዚህም መነኩሴውን መሳደብ ጀመረ ፣ አልፎም በጥፊ መታው፡፡ መነኩሴው ምንም ሳይል ሌላኛውን ጉንጩን ሰጠው፡፡ በዚህን ጊዜ ሰውዬው ልቡ ተነክቶ ፣ አልቅሶም መነኩሴውን ይቅርታ ጠየቀ ፤ እንዲህም አለው ፡- ‹‹መጥፎዎች እንደሆናችሁ ይነግሩናል ፤ ነገር ግን ከእኛ ትሻላላችሁ!›› ወደ ካይሮ ለምን እንደመጣም ጠየቀው፡፡ ዕቃ ለማሳደስ እንደመጣ ሲነግረው እርሱም እንዲህ ዓይነቶቹ ዕቃዎች የሚሠሩበትና የሚታደሱበት የሥራ መስክ ላይ እንደተሠማራ ነገረው፡፡ ከዚህ በኋላ ዕቃዎችን በነፃ ከማደስ አልፎ ሁልጊዜ ለእድሳት ሲመጣ ወደሌላ ቦታ እንዳይሔድ ቃል አስገባው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በፊል. ፩÷፳፫ ላይ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፥ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና›› እንዲሁም በፊል.

፩፥፳፩ ላይ ‹‹ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና›› በእርግጥ ሞት ጥቅም እንጂ ጉዳት አለመሆኑ በአእምሮአችሁ ውስጥ ተተክሎአል? መሔድ ከክርስቶስ ጋር መኖር ከሁሉ ይልቅ የሚሻል መሆኑስ? ዓይን ያላያትን ጆሮ ያልሰማትን በሰው ልብ ያልታሰበችውን የእግዚአብሔርን መንግሥት መመኘትንስ አእምሮአችሁ ለምዷል? የሞትና የሕይወት እውነተኛ ትርጉምንስ በተገቢው መንፈሳዊ አረዳድ ተረድታችሁታል?

ምእራፍ ሁለት

# ትምህርት ስለ ፈቃድ

ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ።›› ሲል ነግሮናል። ሮሜ. ፯፥፳፪–፳፫

አባቶች ይህንን ሲያብራሩ በእኛ ዘንድ ሁለት ፈቃዶች እንዳሉ ያስረዳሉ። ታላቅ የሆነውና የከበረው ፈቃዳችን ‹‹ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን የሚሻ›› የውስጣዊው ሰውነታችን ፈቃድ ነው። (ቆላ.፫፥፩) የተዋረደውና ታናሽ የሆነው ፈቃዳችን ደግሞ እርካታን ብቻ የሚሻው ፈቃዳችን ወይም ‹የኃጢአት ሕግ› ሲሆን ዓለምንና የሥጋ አምሮቱን ብቻ የሚከተል ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው እነዚህ ሁለት ፈቃዳት በውጊያ ላይ ናቸው። (ሮሜ. ፯፥፳፫)

በሚያሳዝን ሁኔታ ብዙውን ጊዜ ታላቅ የሆነውን ፈቃዳችንን የሚያሸንፈው የተዋረደውና ታናሽ የሆነው ፈቃዳችን ነው። ስለዚህ የኃጢአት ሕግ ወይም የተዋረደው ፈቃድ ወይም የራስን እርካታ ብቻ የሚሻው ፈቃዳችን የሚመራው በቀንደኛው ጠላታችን በዲያቢሎስ ነው እንዲሁም በልዕልና ያለው ፈቃዳችን በጸጋው ይመራል ልንል ማለትም አያስፈልግም።

የክርስቲያናዊ ፍጹምነት ዓላማ ሁኔታዎችን ማለዋወጥና ሥጋዊ ፈቃዳችንን ለመንፈሳዊው ፈቃዳችን ማስማረክ ነው። ይህ

ግብ እጅግ ፈታኝ ነው ፤ ቅዱስ ጳውሎስ ራሱ እንዲህ ሲል ኀዘኑን ገልጧል ፡- ‹‹እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?›› (ሮሜ.፯÷፳፬)

ዲያቢሎስ እጅግ ተንኮለኛ ነው ፤ ሥጋዊ ፈቃዳችንን ለመንፈሳዊው ፈቃድ ለማስገዛት ብንችል እንኳን ስልቱን ይቀይራል። መንፈሳዊውን ፈቃዳችን ከጸጋ እግዚአብሔር የተለየ እንዲሆን አድርጎ ያበላሸዋል። ምንም እንኳን እያደረግን ያለነው ነገር መልካም ቢሆንም ፤ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ በሆነና እግዚአብሔርን ደስ በማያሰኝ መንገድ ካደረግነው ዋጋ አይኖረውም።

ይህ ባይሳካለት እንኳን ሌላ ስልት ይሞክራል። በልባችን ውስጥ የኩራትና የጻድቅነት ስሜት እንዲያድርብን ያደርግና በጽድቃችን ልናገኘው የሚገባንን ዋጋ ያሳጣናል።

በዚህ ውጊያው ምን ያህል የተወሳሰበ እንደሆነ የተረዳን ይመስለኛል! እናም እስከ መጨረሻይቱ እስትንፋስ ድረስ መዋጋት ይጠበቅብናል። ቅዱስ ጳውሎስ በዕብ. ፲፪÷፬ ላይ ያስጠነቅቀናል ፡- ‹‹ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም›› በኤፌሶን መልእክቱም እንዲህ ሲል ያሳስበናል ፡- ‹‹መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።›› ኤፌ. ፮÷፲፪–፲፫

ቅዱስ ጴጥሮስም ‹‹በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ አንበሳ ይዞራልና›› ብሎ መክሮናል። (፩ጴጥ. ፭÷፰)

ይህ እንድንዋጋና እንድናሸንፍ የምንጠበቅበት ብዙ ትግል የሚጠይቅ ጦርነት ነው። እጅግ ፈታኝ ነው ትሉ ይሆናል ፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም መቶ በመቶ ይስማማበታል። ‹‹ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥ መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው›› (ማቴ. ፯÷፲፬)

አስደሳቹ ዜና ባላጋራችን ዲያቢሎስ ፣ የሚያገሣው አንበሳ ነፃ ፈቃዳችንን መንካትና ማስገደድ ግን አይችልም። የሚችለው ዕቃዎቹን እንደሚሸጥ ጥሩ ነጋዴ መሆን ብቻ ነው። የቀረበውን ዕቃ ወድዶ መግዛት ወይም አለመቀበል የእኛ ሙሉ መብት ነው።

ወደ ካናዳ ለመጀመሪያ ጊዜ ስንመጣ ቶሎ ከጥቅም ውጪ ሊሆኑ የሚችሉ ዕቃዎችን በሚሸጡ ብልጣ ብልጥ ነጋዴዎች በተደጋጋሚ ተሞኝተን ነበር። አሁን ግን ነጋዴዎች የሚነግሩንን ሁሉ ማመን እንደማይገባን ተምረናል። ብዙዎቹ እየደወሉ በማይሆን ተስፋ ሊሞሉንና ሊደልሉን ይሞክራሉ ፤ እንዴት ጠንቃቃ መሆን እንዳለብን ስለተማርን ሌላ ድርድር ውስጥ ሳንገባ በአጭሩ እንገታዋለን። አንዳንዴም ከውትወታቸው ለመላቀቅ ስትሉ ቆጣ ልትሉ ትችላላችሁ።

እንዲህ ዓይነቶቹ ልጣብልጦች በወጥመዳቸው ውስጥ እንድትገቡ ለማሳመን ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ይህንን ጣቢያ መቼም ሁላችሁም ታስታውሱታላችሁ ‹‹እንኳን ደስ አላችሁ

ወደ ጃማይካ ለመሔድ የነፃ ትኬት አሸናፊ ሆናችኋል!!›› ወይም የቴሌቪዥን ተሸላሚ ሆናችኋል የሚሉ! ብልሆች ከሆናችሁ ሽንገላቸውን ከንቱ ልታደርጉት ትችላላችሁ! እኔ በግሌ በነፃ መውሰድን ሃይማኖቴ አይፈቅድም ብዬ አሳፈራቸዋለሁ!

የዲያቢሎስም እንዲሁ ተመሳሳይ ነው ፤ ማታለያዎችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ እናንተ ካልፈለጋችሁ ግን ምንም ማድረግ አይችልም፡፡ ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው በመጠን የምትኖሩ ንቁዎች ከሆናችሁ ማታለያዎቹን ቢቀያይር እንኳን ድሉ የእናንተ ይሆናል፡፡ ዲያቢሎስ ወደ እኛ የሚልካቸውን መደለያዎች እንዴት ልንቋቋም እንችላለን? የመጀመሪያው ነገር ጸሎት ነው፡፡ ደካማነታችሁን ወደ ጌታችን አምጡት በአጋፔ ጸሎታችን እንደምንለው ‹‹ጻድቅ በጭንቅ የሚድን ከሆነ እኔ ኃጥኡ የት ልቆም እችላለሁ? በድካሜና በተሰባሪነቴ የቀኑን ሸክምና ቃጠሎ መታገሥ አልቻልሁም፡፡›› ብላችሁ ለምኑ፡፡ ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ‹‹ለዚህ ለሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?›› ብላችሁ አልቅሱ! ከመዝሙረኛው ጋርም ‹‹ድውይ ነኝና አቤቱ፥ ማረኝ ›› (መዝ. ፮÷፪) በእግዚአብሔር ፊት ደካማነቱን የሚገልጽን ሰው ዲያብሎስ ሊያጠቃው አይችልም፡፡

ሁለተኛው ነገር ኃጢአትን መጥላትና የኃጢአት ነጋዴ የሆነውን ዲያቢሎስን እንዴት መጥላት እንደሚቻል ራስን ማስተማር ነው፡፡ ከራት ላይ የሚያስነሷችሁን ነጋዴዎች መቋቋምን እንደምትለምዱ ሁሉ ኃጢአትንና ዲያቢሎስን መጥላትን ተማሩ፡፡ ሁላችንም በመጨረሻ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት እንደምንቆምና የኃጢአት ደመወዝ ሞት እንደሆነ አትርሱ፡፡ የአጋፔ (ጸሎትን)

ቃላት አስታውሱ ‹‹እነሆ በጌታ የፍርድ ወንበር ፊት የምቆም ነኝ ፤ በኃጢአቴ አፍራለሁ ፣ እጨነቅማለሁ!!››

ጸሎትና የፍርድ ቀንን ማሰብ የመከላከያ መንገዶቻችሁ ናቸው። ነገር ግን ጠላት ሲያጠቃኝስ ምን ማድረግ እችላለሁ? አንድ ምሳሌ እንውሰድ ፡-

ለምሳሌ አንድ ሰው ሰደበህ እንበል። ወዲያው የኃጢአት አቅራቢው (ዲያቢሎስ) ወደ አንተ ቀርቦ ለክብርህ እንድትቆምና በዚያ ሰው ፊት ፈሪ መስለህ መታየት እንደሌለብህ ይመክርሃል። ነገሩን የጀመርከውም አንተ አለመሆንህንና ምንም ብታደርግ ራስህን ለመከላከል ያደረግኸው እንደሆነ ይነግርሃል። ይህ ሹክሹክታ ይደጋማል። የአንተ ምላሽ ግን ይህ ሹክሹክታ የሰይጣን መሆኑን ማስታወስ ነው። ለራስህ ‹‹እስቲ ቆይ! በዚህ ምክር ነጋዴው ዲያቢሎስ የቁጣና የበቀልን ኃጢአቶች ሊሸጥልኝ እያግባባኝ ነው።›› በል። የተሸጠልህ ኃጢአት ምን እንደሆነ ለይ ፤ ከዚያም ወደ ልብህ ሳይደርስና ስሜትህን ሳይገዛ በፊት በቁጥጥር ሥር አውለው። ከዚያም ‹‹ከኊላዬ ሒድ አንተ ሰይጣን›› ብለህ አባርረው። ዲያቢሎስ ይህንን ሰምቶ ከኊላዬ ይሔዳል ብለህ አትገምት። እዚህ ጋር ከዚህ በፊት ያየናቸው ራስን የመጠበቂያ መንገዶች ሥራ ላይ ሊውሉ ነው። እንዲህ ያሉትን የዲያብሎስ ምክሮችን ለመጥላትና እንደ ጠላቶችህ ለመቁጠር ራስህን አስለምድ። ከመዝሙረኛው ጋር ‹‹አንቺ ወራዳ የባቢሎን ልጅ ሆይ ስለ ተበቀልሽን የሚበቀልሽ የተመሰገነ ነው። ሕፃናቶችሽን ይዞ በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው

የተመሰገነ ነው፡፡›› (መዝ.፻፴፮÷፰–፱) የባቢሎን ልጅ የተባሉት የሚጎዱን ክፉ ሐሳቦቻችን እንደሆኑ አበው ይናገራሉ፡፡

የበረሃ አባቶች በተጨማሪም እነዚህን ሐሳቦች ለመቃወም የሚያዘወትሯቸውን ጸሎቶችንም ያስተምሩናል፡፡ ይህም ጸሎት ከዲያቢሎስና ከሚያቀርብልን ክፉ ሐሳቦች ለመገላገል የምንጠቀምበት ምሥጢራዊ መሣሪያ ነው፡፡ ይህ ጸሎት ‹‹አቤቱ እኔን ለማዳን ተመልከት ፤ አቤቱ እኔን ለመርዳት ፍጠን፡፡›› በሚለው የዳዊት መዝሙር ነው፡፡ (መዝ.፷፱÷፩) ‹The Conferences› (ጉባኤያቱ) በተሰኘው የ‹John Cassian› መጽሐፍም አንድ ምእራፉ ይህንን ምሥጢራዊ የጸሎት መሣሪያ የያዘ ነው፡፡ ይህንን ጸሎት ሰላም እስከምታገኝ ድረስ በኅሊናህ ደጋግመህ ጸልየው፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ይህንን ጸሎት እያማተብህ የበለጠ ውጤታማ ትሆናለህ ብሎአል፡፡

ይህንን ክፉ ሃሳብ ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ከፈለግህ ዲያቢሎስ እንድታደርገው ሹክ የሚልህን ነገር ተቃራኒውን ፈጽም ፤ በክፉ ፈንታ መልካምን! ፍጹምነትን መፈለግ ማለት ከኃጢአት መገላገል ብቻ አይደለም፡፡ መዝሙሩም የሚለው ይህንን ነው ፡- ‹‹ከክፉ ሽሽ መልካምንም አድርግ ለሰላምን እሻ ተከተላትም፡፡›› (መዝ. ፴፫÷፲፬) ጌታችንም ይህንን የመሰለ ቃል ተናግሯል፡- ‹‹ነገር ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤ ምንም ተስፋ ሳታደርጉም አበድሩ፥ ዋጋችሁም ታላቅ ይሆናል፥ የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ፥ እርሱ ለማያመሰግኑ ለክፉዎችም ቸር ነውና፡፡›› (ሉቃ. ፮÷፴፭)

ፈቃድን ለእግዚአብሔር ማስገዛትን ስለመለማመድ ከመናገር በፊት ባለፈው ምእራፍ ያየነውን ሕሊናን ማስገዛትን መልመድ ይቀድማል፡፡ ‹‹ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ፤›› ‹‹ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ፡፡›› ብሎ ጌታችን እንደነገረን በመጀመሪያ ሕሊናህ በእግዚአብሔር ታምኖ ስድብን መታገሥ መልመድ ይኖርበታል፡፡

ይህም ሁሉ ሆኖ ጦርነቱ የማያቋርጥ ሊሆን ይችላል ፤ ክፉ ሐሳቦችም እንደ ባሕር ወጀብ በላይ በላይ ሊመጡብን ይችላሉ፡፡ የአጸፋ ውጊያ ለማድረግ እንድትችል እንደ ቀረርቶ (battle cry) ዜማ የሚጠቅምህን ኃይለ ቃል አስታውስ፡፡

ለምሳሌ ከመዝሙረኛው ጋር እንዲህ በል ‹‹እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፡፡ የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው የሚያስደነግጠኝ ማን ነው? ክፉዎች፥ አስጨናቂዎቼ ጠላቶቼም፥ ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ በቀረቡ ጊዜ፥ እነርሱ ተሰናከሉና ወደቁ፡፡ ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ ልቤ አይፈራም ሰልፍም ቢነሣብኝ በዚህ እተማመናለሁ፡፡›› (መዝ. ፳፮፥፩–፫)

የእመቤታችን ድንግል ማርያምንም ረዳትነቷን ፈልግ፡፡ በአጋፔ ጸሎታችን የምንላትን በል ‹‹ንጽሕት ድንግል ሆይ የከለላነትሽን ጥላ በእኔ ላይ ዘርጊ ፤ የክፉ ሃሳቦችን ማእበልም ከእኔ አርቂ›› እነዚህ የአጋፔ ጸሎታት በፈቃዶቻችን (በሥጋና በነፍስ) መካከል በሚደረገው ውጊያ እንዲረዱን በአባቶች የተቀመጡ ናቸው፡፡

ክፉ ሃሳቦች ሲያጠቁህ ሁልጊዜ ከእኛ ጋር ያሉት ከሚቃወሙን ይልቅ እንደሚበልጡ አስታውስ፡፡

አንድ ቀን ክፉ ንጉሥ በነቢዩ ኤልሳዕ ላይ ሙሉ ሠራዊት አዘመተበት፡፡ የኤልሳዕ ባሪያ የከበቧቸውን ሰረገላዎችና መሣሪያዎች ባየ ጊዜ እጅግ ፈራ፡፡ ነቢዩ ኤልሳዕ ግን ‹‹አትፍራ ከእኛ ጋር ያሉት ከእነርሱ ጋር ካሉት ይበልጣሉ›› አለው ፤ ኤልሳዕም ‹የዚህን ሰው ዓይኖች ክፈት› ብሎ ጸለየ ፤ የሎሌውም ዓይኑ በተከፈተ ጊዜ ተራራው በእሳት ሰረገላዎችና ፈረሶች ተከብቦ አየ፡፡ (፪ነገሥ. ፮፥፲፮–፲፯)

ተመሳሳይ ነገር በቅዱስ ሙሴ ጸሊምም ላይ ደርሷል፡፡ ይህን አባት የሃሳብ ኃጢአቶች ያጠቁት ነበር፡፡ ሁልጊዜም ስለ እነዚህ ሐሳቦች ሊያማክረው ወደ ንስሐ አባቱ ወደ ቅዱስ ኤስድሮስ ይሔድ ነበር፡፡ ለዐሥራ አራት ጊዜያት ከተመላለሰ በኋላ ቅዱስ ኤስድሮስ ከበአቱ በላይ ይዞት ወጣና ‹‹ወደ ምዕራብ ተመልከትና ያየኸውን ንገረኝ›› አለው፡፡ ‹‹አጋንንት ወደ መነኮሳት የእሳት ጦሮችን ሲወረውሩ አየሁ›› አለው፡፡ ቀጥሎም ‹‹ወደ ምሥራቅ ተመልከት ፤ ምን ይታይሃል?›› አለው፡፡ ሙሴ ጸሊምም ‹‹መላእክት ጦሮቹን እየመከቱ ለመነኮሳቱ ሲከላከሉ አየሁ›› አለ፡፡ ‹‹እንግዲያውስ ማናቸው ይበልጣሉ ፤ የሚያጠቁን ወይስ የሚጠብቁን?›› ቅዱስ ሙሴ መለሰ ‹‹የሚጠብቁን!›› ወዲያውኑ ክፉ ሃሳቦች እርሱን መዋጋት አቆሙ፡፡

ጠላታችን በእኛ ውስጥ የሚተክለውን ክፉ ሃሳብ መቃወም ዋጋን የማያስገኝ አይደለም፡፡ የሚከተለው የአበው ታሪክ እንደሚያስረዳን ፡-

ከመንፈሳዊ አባቱ ጋር አብሮ የሚኖር ወጣት መነኩሴ ነበር ፤ ይህ መነኩሴ ሳይሰግድና የአባቱን ቡራኬ ሳይቀበል እንቅልፍ አይተኛም ነበር፡፡ አንድ ምሽት ከሰገደ በኋላ ‹‹አባቴ ይባርኩኝ!›› ሲል አባ ከእርሱ በፊት እንቅልፍ ጥሎአቸው ነበር፡፡ ይነቁ ይሆናል በሚል ተስፋ እርሳቸው ሳይባርኩት ላለመተኛት ከአጠገባቸው ሊቆይ ወሰነ ሆኖም አባ ሙሉ ሌሊቱን ተኙ፡፡ ይህ ወጣኒ መነኩሴ በዚያውም እንቅልፍ አሸለበው፡፡ አባ ሲባንኑ ሰባት መላእክት ሰባት በዚህ ደቀ መዝሙር ራስ ላይ አክሊላትን ሲያደርጉ ተመለከቱ፡፡ እኚህ አባት በጠዋት ‹‹ማታ ምን ተፈጥሮ ነበር?›› ብለው ጠየቁት፡፡ ‹‹ይቅር ይበሉኝ አባቴ! ማታ የእርስዎን ቡራኬ ሳልቀበል ወደ አልጋዬ እንድሔድ የሚገፋፋ ሃሳብ ሰባት ጊዜ መጥቶብኝ ነበር ፤ ይህንን ሃሳብ ተቃወሜው ቆየሁ›› አላቸው፡፡ እኚህ አባት ሰባቱ አክሊላት ክፉ ሃሳቦቹን በመቃወሙ ያገኛቸው መሆናቸውም አወቁ፡፡ ይህንን ታሪክ ለሌሎች መነኮሳት ነገሯቸው፡፡ በትዕቢት እንዳይወድቅ ሲሉ ግን ለዚህ ወጣት ደቀ መዝሙራቸው አልነገሩትም፡፡

ዲያቢሎስ በእኛ ውስጥ በሚተክላቸው ክፉ አሳቦች ፈንታ በጎ ሃሳቦችን በኅሊናችን መቅረጽ ይገባናል፡፡ ይህንን የማድረግ ምሳሌ የሚሆኑም አሉ፡፡

በፈተና ስትወድቅ ወይም የጉዳዮች አለመሳካት ሲገጥምህ ዲያቢሎስ በእግዚአብሔር ላይ እንድታጉረመርምና እንድትማረር

የሚገፋፉ ሃሳቦችን ያመጣብሃል ፤ እነዚህን ሃሳቦች ‹‹እግዚአብሔር ይመስገን!›› በማለት ተዋጋቸው፡፡ በመጀመሪያ ይህንን የምትለው በአንደበትህ ብቻ ሊሆን ይችላል ፤ ቆይቶ ግን ልብህ ከአንደበትህ ጋር ማመስገን ይጀምራል፡፡

የዲያቢሎስ የሹክሹክታ ምክር በበደለህ ሰው ላይ እንድትቆጣ የሚገፋፋ ቢሆን ለዚያ ሰው ጥፋት ማስተባበያ በመፍጠር ክፉ ሃሳብህን ተቃወመው፡፡ ምናልባት (የደረሰብህ በደል በኅሊናህ እየተመላለሰብህ) ቢያነዋውጽህ ‹‹ጌታ ሆይ ይቅር በለው ፤ እኔንም ይቅር በለኝ!›› በማለት ሃሳብህን ታገለው፡፡

ሌላው የዲያቢሎስን ክፉ ምክር መቃወሚያ መንገድ የንስሐ አባትህ እንዲጸልዩልህ መጠየቅ ነው፡፡ ‹‹አባቴ ዲያቢሎስ እየደለለኝ ነውና በጸሎትዎ ይርዱኝ!›› በል፡፡

‹ፓራዳይዝ ኦፍ ፋዘርስ› በተሰኘው መጽሐፍ ላይ ስለአንድ ወደ ከተማ ስለተላከ መነኩሴ ተጽፏል፡፡ ይህን አባት አንዲት ውብ ወጣት ከእርስዋ ጋር በኃጢአት እንዲወድቅ ልትማርከው ሞከረች፡፡ ይህ አባት ‹‹አምላኬ በንስሐ አባቴ ጸሎት አድነኝ!›› ብሎ ጮኸ፡፡ በቅጽበት ውስጥ ራሱን ወደ ገዳሙ በሚወስደው ጎዳና ላይ አገኘው፡፡

ምእራፍ ሦስት

# የስሜት ሕዋሳትን መቆጣጠር

ባሕታዊው ቴዎፋን የሰውን ነፍስ በንጉሥ የሚመስለው ሲሆን ሥጋውን ደግሞ በንጉሡ ቤተ መንግሥት ይመስለዋል፡፡ ይህ ቤተ መንግሥት አምስት መስኮቶችና አንድ በር አለው፡፡ እነዚህ አምስት መስኮቶች አምስቱ የስሜት ሕዋሳት ናቸው፡፡ በሩ ደግሞ አእምሮ ነው፡፡ ጠላት በመስኮትና በበር ካልሆነ በየትም ሊገባ አይችልም፡፡ እነዚህ ከተዘጉ ጠላት ለመግባት አይችልም፡፡

በእነዚህ መስኮቶች (የስሜት ሕዋሳት) የኃጢአት ነጋዴ ዲያቢሎስ ልዩ ልዩ ልምምዶችንና ነፍስን የሚያስደስቱ ስሜቶችን ያመጣል፡፡ በዚህም የተነካ ነፍስ እርካታን ጠቅልላ ትይዛለች፡፡ ከዚያም ይህንን እርካታ እንደ ዋና መልካም ነገርና እንደ ግብ መቁጠር ትጀምራለች፡፡ በዚህ መንገድ ነገሩ ይገለበጥና ነፍስ እግዚአብሔርን መፈለግ ትታ ደስታን መሻት ትጀምራለች፡፡

መንፈሳዊውን ፍጹምነት መንገድ ለመጀመር የሚፈልግ ሰው ትክክለኛውን የሕይወት ቅደም ተከተል ዳግም ሊመሠርት ይገባዋል፡፡ ይህም በደስታ ከመዋጥ ይልቅ እረፍትን ከአምላክ መፈለግ ነው፡፡ ትግሉ ረዥምና አስቸጋሪ ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ይህን ውሳኔ እንወስናለን፡፡ ለዓመታት ራስን ከማስደሰት ጋር ከኖሩ በኋላ ነፍስን ከክፉ ልማድ ማላቀቅ አስቸጋሪና ዓመታትን

የሚጠይቅ ነው፡፡ አንድ ሰው ነገሮችን በተገቢው መንገድ የማካሔድ ፍላጎቱን ለማሳካት ስሜትን መግዛት ወሳኝ ነገር ነው፡፡

እያንዳንዱ ስሜት አስደሳች ሊሆንም ላይሆንም ይችላል፡፡ ነፍስ በሚያስደስቱ ነገሮች ልትደሰትና ሱስ ልታደርጋቸው ትችላለች ፤ በቆይታም ሁልጊዜ እነዚያን ደስታዎች መመኘት ትጀምራለች፡፡ በዚህ መንገድ እያንዳንዱ ስሜት ለነፍሳችን በርካታ ምኞቶችንና ለመላቀቅ የሚያስቸግሩ ልማዶችን እንድታውቅ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ምኞቶች በነፍሳችን ውስጥ ተዳፍነው ይቆዩና የምንመኘውን ነገር ዳግመኛ የምናገኝበት አጋጣሚ ሲመጣ ይቀሰቀሳሉ፡፡ ይህ ስሜት አንድ ጊዜ ከተቀሰቀሰ በኋላ ቅዱስ ያዕቆብ እንደተናገረው በድግግሞሽ መታሰር ይጀመራል፡፡ ‹‹ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች ፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፡፡›› (ያዕ. ፩÷፲፭) በዚህም የኤርምያስ ትንቢት ተፈጸመ፡፡ ‹‹ሞት ወደ መስኮታችን ደርሶአል ወደ አዳራሻችንም ውስጥ ገብቶአል፡፡›› (ኤር. ፱÷፳፩) ይህም ማለት ሞት በስሜቶቻችን ውስጥ አልፎ ወደ ነፍሳችን ይገባል ማለት ነው፡፡

ስሜትን መግዛት ሁለት እጥፍ ጠቀሜታ ያለው ነገር ነው፡፡ ስሜቶቻችንን የምንጠብቀው በጎጂ ነገሮች ከመማረክና ከመወሰድ ብቻ አይደለም ፤ ይልቁንም በእያንዳንዱ ፍጥረትና በእያንዳንዱ ነገር ስሜታችን እንዲማረክና እንዲመሰጥ ማድረግም አለብን፡፡

## ዓይንን መቆጣጠር

ዓይኖቻችንን እንድንቆጣጠር የሚያዝዙን በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አሉ፡፡ ‹‹የሰውነት መብራት ዓይን ናት፡፡ ዓይንህ

እንግዲህ ጤናማ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ የጨለመ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ ከሆነ፥ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ!›› ማቴ. ፮÷፳፪–፳፫ ‹‹ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና።›› (ማቴ. ፭÷፳፱) ‹‹እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።›› (ማቴ.፭÷፳፰)

በጥንት ዘመን ዓይንን ክፉ ከማየት ንጹሕ ማድረግ ያን ያህል የሚያስቸግር ነገር አልነበረም። በዚያን ዘመን ሴቶች በሥርዓት የሚለብሱና የሚሸፈኑ ስለነበሩ ‹ወደ ሴት አይተህ አትመኝ› የሚለውን ትእዛዝ ለመከተል አያስቸግርም ነበር። ዛሬ ግን ዓይንን ከእነዚህ አጋጣሚዎች መጠበቅ አስቸጋሪ ነው። የአለባበስ ሥርዓቱ ስለተበላሸ ብቻ አይደለም ፤ ዲያቢሎስ ለዓይኖቻችን ርኩሰትን ለማስተዋወቅ የሚያቀርብልን ብዙ መንገድ ስላለ ነው።

በዚህ ዘመን መጻሕፍትና መጽሔቶች ለዝሙት በሚያነሣሡ ምስሎች ተሞሉ ናቸው። ኅብረተሰቡም ቀስ በቀስ እነዚህን ነገሮች ማየት እንግዳ የማይሆንበት ነገር እየሆነ መጥቷል። እንዲያውም የበለጠ ግልጥ ለሆኑ የዝሙት ምስሎች ፍላጎቱን እያሳየ ነው።

ወደ ገበያ ስትወጡ ዓይኖቻችሁ ከየአቅጣጫው በተሰቀሉ ዕርቃን በሚያሳዩ አስጸያፊ ምስሎች ይያዛሉ። በልብሶች መሸጫም ልብሶች የሚተዋወቁበት መንገድ ሌላው ዓይንን የሚፈታተን እይታ ሆኗል። በገበያ ማእከል ሕንጻዎች መካከል ስትሔዱ የማሳያ

መስኮቶች የውስጥ ልብሶችን በሚያስተዋውቁ የዕርቃን ምስሎች ተሞልተው ታገኙአቸዋላችሁ፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ፤ አንዳንድ መሸጫዎች በሰው መልክ በተሠሩ አሻንጉሊቶች ተለብሰው ይታያሉ፡፡ በየአደባባዩና በመንገዝ ሥፍራዎች በሚሰቀሉ ማስታወቂያዎች ዓይንን በክፉ እይታዎች በሚያሳድፉ (ዓይኖቹ ኃጢአትን ለሚናፍቁ ሰው ደግሞ ሊያስደስቱት በሚችሉ) ነገሮች የተሞሉ ሆነዋል፡፡

ቴሌቪዥን ደግሞ እነዚህን እይታዎች የበለጠ ሕይወት ሰጥቶ እንድንመለከታቸው ያደርገናል፡፡ ከሚታዩት ፊልሞችም ውስጥ ሌላው ቀርቶ በካርቱን ፊልሞችም ጭምር ወደ ዝሙት የሚያመራ ትዕይንት የሌለባቸውን ማግኘት የማይታሰብ ሆኗል፡፡ ኢንተርኔት ደግሞ ከቴሌቪዥን የሚስተካከል እንዲያውም የሚበልጥ ወደ ኃጢአት የሚመሩ እይታዎች አቅራቢ ሆኗል፡፡

እነዚህን በነውር የተሞሉ ነገሮች የማየትን ልማድ ለመላቀቅ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ነገር ላይ ማተኮር ይገባናል፡፡ ኦሪት ዘፍጥረት እንዲህ ይለናል ፡- ‹‹የእግዚአብሔር ልጆችም የሰዎች ልጆች መልካሞች እንደሆኑ አዩ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ፡፡›› ውጤቱም ጥፋት እንደነበር ተነግሮናል ‹‹እግዚአብሔርም ፡- የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ›› ዘፍ. ፮÷፪–፯ ሴትን አይቶ መመኘትም የሰው ልጅን ለጥፋት አደረሰው፡፡

ዓይናችን አንድን ነገር ያለገደብ በአድናቆት እንዲመለከት መፍቀድ ምን ያህል አደገኛ መሆኑን የዳዊት ታሪክ ያስታውሰናል፡፡

በግዴለሽነት ዓይኑን ከማየት አለመከልከሉ መዝሙረኛውን /የመዝሙራት ደራሲውን/ ቅዱስ ዳዊት ወደ ዘማዊና ነፍሰ ገዳይነት ቀየረው፡፡ ‹‹በንጉሥም ቤት በሰገነት ላይ ተመላለሰ ፤ በሰገነቱ ሳለ አንዲት ሴት ስትጣጠብ አየ ፤ ሴቲቱም መልከመልካም ነበረች፡፡ … መልእክተኞች ልኮ አስመጣት … ከእርስዋም ጋር ተኛ…›› (ጽንስ ለማሳሳት ባልዋን አስመጥቶ አልሆን ሲለው) ‹‹በደብዳቤውም ፡- ኦርዮን ጽኑ ሰልፍ ባለበት በፊተኛው ስፍራ አቁሙት ተመትቶም ይሞት ዘንድ ከኋላው ሽሹ ብሎ ጻፈ …. ኦርዮም ደግሞ ሞተ›› (፪ሳሙ. ፲፩÷፩–፳፩)

ከላይ ካየናቸው የዓይን ፈተናዎች ጋር አንድ ሰው እስከ ደም ድረስ መጋደል አለበት፡፡ ይህ ተጋድሎ አስቸጋሪ ቢሆንም ለድኅነት ግን የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ ሌላ ነገሮችን ለመግዛት ብለን በምንሔድበት ገበያ ወይም በመንገድ ላይ እንዲህ ዓይነት ነገሮች ማጋጠማቸው እንዳለ ሆኖ ሌላው ጉዳይ ደግሞ እንዲህ ያሉትን እይታዎች ፍለጋ መውጣትም ነው፡፡ ከቴሌቪዥንም ሆነ ከኢንተርኔት የዝሙት ምስሎችን መመልከትና ለዝሙት የሚገፋፉ ፊልሞችን መከራየትና ለዝሙት የሚያነሣሡ መጽሔቶችን መግዛት ደግሞ ከላይ ካየናቸው የከፋ ነው፡፡ ቅጣቱም ከዚያኛው የከፋ ነው፡፡

በሁከት የተሞሉ ትዕይንቶችን መመልከትም ሌላው ኃጢአት ነው፡፡ አብዛኛዎቹ መዝናኛ ፊልሞች ያለ አንዳች ብጥብጥና ሁከት አይሠሩም፡፡ የሕጻናት ፊልሞች እንኳን በጠብና ፍልሚያ የታጀቡ ናቸው፡፡ በርካታ ስፖርታዊ ውድድሮች ጠብን የተሞሉ ናቸው፡፡ ካለ ግጭትና አንዱ አንዱን ሳያደናቅፍ የሚደረግ የገና

ጨዋታም የለም፡፡ የበለጠ አደገኛው ደግሞ ስፖርት ተብዬው ትግል (the- so called -'sport' wrestling) ነው፡፡ ይህንን ትግል በማየት ሱስ የተያዙ ጥቂት ሕጻናትንም አውቃለሁ፡፡

ወላጆች ልጆቻውን መጠበቅና ለሕጻንነት ዕድሜያቸው የሚገባቸውን ነገር መመልከታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ልጆችን ከቴሌቪዥንም ሆነ በኢንተርኔት አስጸያፊ ትዕይንቶችን እንዳያዩ እንዲገለገሉበት ከመስጠት በፊት የሚቻለውን ቅድመ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በጾም ወራት በምግብ አምሮት መጠመድና የልዩ ልዩ ምግቦችን ምስል እያዩ መጎምጀትም የተከለከለ ነው፡፡ ሔዋን ያደረገችው ይህንን እንደነበረ አስታውሱ፡፡ ‹‹ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ አየች … ከፍሬውም ወሰደችና በላች›› (ዘፍ. ፫÷፮) ቀሪው እንደምታውቁት ነው፡፡ በዚህ ዘመንም አትብሉ በተባልንበት በጾም ወቅት አፍን በምራቅ የሚሞሉ የሚያስጎመጁ ምግቦችን በየሥፍራው እናያለን፡፡

መኪናን ፣ቤትን ፣ ዕቃዎችን ፣ ልብስን ወዘተ እየተመለከቱ በምኞት መቃጠልም ሌላው በዓይናችን የምንፈጽመው ኃጢአት ነው፡፡ የኃጢአት አሻሻጩ ዲያቢሎስ ጌታችንን በፈተነው ጊዜ ‹‹እጅግ ረጅም ወደ ሆነ ተራራ ወሰደው ፤ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ ፦ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው፡፡›› (ማቴ. ፬÷፬–፱) ሰይጣን በተመሳሳይ ዘዴ ምድራዊ ነገሮችን እንድንመኝ (እና ለእርሱ እንድንንበረከክ) ይፈትነናል፡፡ ጌታችን የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በመጥቀስ ዲያቢሎስን

ተቃውሞ ድል አድርጎታል፡፡ እኛንም ሲፈትነን ይህንኑ ማድረግ ይገባናል፡፡ ‹‹ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም›› ፣ ‹‹እንግዲህየዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል፡፡›› የሚሉትን ቃላት ማስታወስ ይገባናል፡፡ (፩ዮሐ. ፪፥፲ ያዕ. ፬፥፬)

ባለ ምቀኛ ዓይን ወይም ባለ ቀናተኛ ዓይን መሆን ሌላው የዓይናችን ፈተና ነው፡፡ ሌሎች ያላቸውን ነገር በምቀኝነትና በቅናት መመልከት በብሉይም ሆነ በሐዲስ ኪዳን እንድንጠነቀቀው የተነገረን ኃጢአት ነው፡፡ መጽሐፈ ኢዮብ ‹‹ሰነፍን ቅንዓት ያጠፋዋል›› ይላል፡፡ ኢዮ.፭፥፪

ለወይኑ አትክልት ስፍራ ሠራተኞችን ሊቀጥር ማልዶ – የወጣው የባለቤቱ ሰው ምሳሌም ቀናተኛ ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያህል የተጠላ እንደሆነ የሚያሳይ ምሳሌ ነው፡፡

ማቴ. ፳፥፩–፲፭ - ሠራተኞችንም በቀን አንድ ዲናር ተስማምቶ ወደ ወይኑ አትክልት ሰደዳቸው:: በሦስት ሰዓትም ወጥቶ ሥራ የፈቱ ሌሎችን በአደባባይ ቆመው አየ፥እነዚያንም:: እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ የሚገባውንም እሰጣችኊለሁ አላቸው:: እነርሱም ሄዱ:: ደግሞም በስድስትና በዘጠኝ ሰዓት ወጥቶ እንዲሁ አደረገ:: በአሥራ አንደኛውም ሰዓት ወጥቶ ሌሎችን ቆመው አገኘና:: ሥራ ፈትታችሁ ቀኑን ሁሉ በዚህ ስለ ምን ትቆማላችሁ? አላቸው:: የሚቀጥረን ስለ አጣን ነው አሉት:: እርሱም፦ እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ የሚገባውንም ትቀበላላችሁ አላቸው:: በመሸም ጊዜ የወይኑ

አትክልት ጌታ አዛዡን። ሠራተኞችን ጥራና ከኋለኞች ጀምረህ እስከ ፊተኞች ድረስ ደመወዝ ስጣቸው አለው። በአሥራ አንደኛው ሰዓትም የገቡ መጥተው እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ። ፊተኞችም በመጡ ጊዜ አብዝተው የሚቀበሉ መስሎአቸው ነበር፤ እነርሱም ደግሞ እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ። ተቀብለው እነዚህ ኋለኞች አንድ ሰዓት ሠሩ፥ የቀኑንም ድካምና ትኩሳት ከተሸከምን ከእኛ ጋር አስተካከልሃቸው ብለው በባለቤቱ ላይ አንጐራጐሩ። እርሱ ግን መልሶ ከእነርሱ ለአንዱ እንዲህ አለው፦ ወዳጄ ሆይ፥ አልበደልሁህም በአንድ ዲናር አልተስማማኸኝምን?ድርሻህን ውሰድና ሂድ፤ እኔ ለዚህ ለኋለኛው እንደ አንተ ልሰጠው እወዳለሁ፤ በገንዘቤ የወደድሁትን አደርግ ዘንድ መብት የለኝምን? ወይስ እኔ መልካም ስለ ሆንሁ <u>ዓይንህ ምቀኛ ናትን?</u>›› ይላል።

ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር እጅግ የራቁ ሰዎች እንዴት በሕይወታቸው መልካም ነገሮችን ያገኛሉ? ብለው ይጠይቃሉ። ይኸው ሐሳብ ሰባ ሁለተኛውን መዝሙር የጻፈልን የመዝሙረኛው የአሳፍም ነበር። ‹‹የኃጢአተኞችን ሰላም አይቼ በዓመፀኞች ቀንቼ ነበርና። እንደ ሰው በድካም አልሆኑም፥ ከሰው ጋርም አልተገረፉም። ዓይናቸው ስብ ስለ ሆነ ወጣ ልባቸውም ከምኞታቸው ይልቅ አገኘ። እነሆ፥ እነዚህ ኃጢአተኞች ይደሰታሉ፥ ሁልጊዜም ባለጠግነታቸውን ያበዛሉ።›› ከእነዚህ ሁሉ የውትወታ ጥያቄዎች በኋላ እግዚአብሔር ፍጻሜያቸውን አሳየው እንዲህ ሲልም ነገረን፡- ‹‹ወደ እግዚአብሔር መቅደስ እስክገባ ድረስ፥ ፍጻሜአቸውንም እስካስተውል ድረስ።

በድጥ ስፍራ አስቀመጥኻቸው፥ ወደ ጥፋትም ጣልኻቸው። እንዴት ለጥፋት ሆኑ! በድንገት አለቁ ስለ ኃጢአታቸውም ጠፉ።››

በእግዚአብሔር ዘንድ ኢፍትሐዊነት የለም። ለዘለዓለማዊ ሕይወት የሚያስፈልጋቸውም ምግባር አለመሥራትን ለሚመርጡ ሰዎች በዚህ ሕይወት የድርሻቸውን ይሰጣቸዋል። መጽሐፍ እንደሚል ፡- ‹‹አቤቱ፥ ከሰዎች፥ እድል ፈንታቸው በሕይወታቸው ከሆነች ከዚህ ዓለም ሰዎች በእጅህ አድነኝ ከሰወርኸው መዝገብህ ሆዳቸውን አጠገብህ ልጆቻቸው ብዙ ናቸው የተረፋቸውንም ለሕፃናቶቻቸው ያተርፋሉ። እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ ክብርህን ሳይ እጠግባለሁ።›› (መዝ. ፲፯÷፲፭)

የባለጸጋው ሰውና የአልዓዛር ታሪክም ሌላ ምሳሌ ነው። ባለ ጸጋው ሰው አብርሃምን ‹‹አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ›› ሲለው አብርሃም ‹‹ልጅ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ ፤ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ።›› ሲል መልሶለታል። (ሉቃ. ፲፮÷፳፭)

## ዓይን በተገቢ መንገድ መጠቀም

አንድ ሰው ራሱን ማስለመድ ያለበት ክፉ ነገሮችን አለማየትና አለመመኘትን ብቻ አይደለም። በእያንዳንዱ ሰውና በእያንዳንዱ ነገር ውስጥ አምላኩን ማየትን መልመድ አለበት። ይህንን እንዴት ማድረግ እንደምንችል የሚያስረዱ ምሳሌዎችን በበረሃውያን አባቶች ታሪክ ውስጥ እናገኛለን። አንድ መነኩሴ ወደ

እስክንድርያ ከተማ መልእክት እንዲያደርስ አበምኔቱ ላኩት፡፡ ሲመለስ መነኮሳት ጠየቁት ‹‹እስክንድርያ እንዴት ናት?›› እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው ‹‹በእስክንድርያ ምንም ነገር የማየት ተልእኮ አልነበረኝም!›› አንድ ጉዳይ ሊፈጽም ነበር የሔደው ፤ ሌላ ምንም ነገር ማየት አልፈለገም ነበር፡፡ በሌላ አጋጣሚም ዕርቃንን ተመልክቶ እንኳን የእግዚአብሔርን ፍጥረት ከማድነቅ በላይ ምንም ስሜት ያልተሰማው አባትም ነበር፡፡

እኛም በመንፈሳዊ መነጽር ነገሮችን መመልከትን ፤ ሕይወት ባላቸውም በሌላቸውም ነገሮች ውስጥ አምላክን መመልከት ልንለምድ ይገባል፡፡ በጾታ ከእናንተ ተቃራኒ የሆኑ መልከ መልካሞችን ባያችሁ ጊዜ የፍትወት ምክንያት ከምታደርጓቸው ይልቅ እነርሱን የፈጠረ እግዚአብሔርን አስቡ፡፡ ጌታችን ዓይንህ ብሩህ ሲሆን ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል ያለውም ይህንን ነው፡፡

በተመሳሳይም ያማረ ቤትን ባየህ ጊዜ በሰማያዊት ኢየሩሳሌም ያለውን እውነተኛውን ቤትህን አስታውስ፡፡ ‹‹ይህ ቤት እንዲህ ያማረ ከሆነ ‹በእጅ ያልተሠራው› እግዚአብሔር ለእኔ ያዘጋጀልኝ ቤት ምን ያህል ያማረ ይሆን?›› ብለህ ከራስህ ጋር ተነጋገር፡፡ ‹‹ኢየሩሳሌም የደስታ ቤቴ ሆይ ወደ አንቺ የምመጣው መቼ ነው? ዋይታዬ የሚያበቃው ደስታሽንስ የማየው መቼ ነው?›› የሚለውንም ዝማሬ በልብህ ደጋግመው፡፡ ዘመናዊ መኪናም አይተህ በተደነቅህ ጊዜ ኤልያስን ይዘው ወደ ሰማይ ያረጉት ሠረገላዎች ምንኛ ይልቅ ያማሩ እንደሆኑ አስብ፡፡

ሌላው አባቶች የሚከተሉት መንፈሳዊ ልምምድ ደግሞ ነገሮችን ባዩ ጊዜ የጌታን መከራ ማሰባቸው ነው። ለምሳሌ ገመድ ባየህ ጊዜ ጌታ ለአንተ ሲል እንደታሰረ አስብ። ሚስማርም ስታይ ስለ አንተ ኃጢአት የተቸነከረበትን የጌታን ችንካር አስብ።

በመጨረሻም ባለማወቅ /በስኅተት/ ያየሃቸውን ነገሮች ከአእምሮህ ሠርዛቸው። ያየኸውን ክፉ ነገር በቁርጠኝነት ከአእምሮህ አውጥተህ ጣለው። ጌታችን ‹‹ዓይንህ ብታሰናክልህ አውጥተህ ጣላት›› ያለው ለእንዲህ ዓይነቱም ነው። ክፉውን ሃሳብ ከአእምሮህ አውጥተህ በዓለት ላይ ፈጥፍጠው። ‹‹ሕጻናቶችሽን በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው።››

## ጆሮን መቆጣጠር

ምናልባትም ዋነኞቹ የጆሮ ጠላቶች ዘፈን ፣ ስድብንና ነቀፋን የተሞሉ ግጥሞችና ቀልዶች ናቸው። የሚጮኹና የሚያውኩ ሙዚቃዎችም እንዲሁ ልንሸሻቸው የሚገቡ ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ወደ ገበያ ስወጣ የሚያጮኹትን የሚያደነቁር ዘፈን እጅግ እጠላዋለሁ። አንዳንዶቹን ሙዚቃዎች ዲያቢሎስ ከበሮ እየደለቀ እንደሆነ እንዲሰማኝ ያደርጉኛል።

በአሁኑ ጊዜ በከፍተኛ ደረጃ ሰውን ለጥፋት ከሚዳርጉ ነገሮች መካከል አንዱ የዘፈን ቪድዮ ነው። እነዚህ የዘፈን ፊልሞች የሚጎዱት ፍትወትን በተሞሉ ግጥሞቻቸውና አቀራረባቸው ብቻ አይደለም ፤ ዓይኖቻችሁንም በፍትወታዊ ትርዒቶቻቸውም ያሳድፋሉ። የሚስከትሉት ውጤትም ፍጹም ጥፋትን ነው።

አንዳንድ ጊዜ ዘፈኖችን ከሰማችሁ በኋላ ቃላቱ በኅሊናችሁ ተቀርጾ እየሔዳችሁ ፣ እየሠራችሁ እያለ ሌላው ቀርቶ እየጸለያችሁም ጭምር በውስጣችሁ ይመላለሳል፡፡

ሌላው የጆሮአችን ፈተና በቴሌቪዥን የክህደት ትምህርቶችንና በክህደት የተሞሉ ዝግጅቶችንን መመልከት ነው፡፡ (በአሜሪካ) አንዳንድ ጊዜ በቴሌቪዥን ‹‹ወንጌላውያን›› ተብዬዎቹን ያየሁኝ ቢሆንም ጥብቅ በሆነው ኦርቶዶክሳዊ መሥፈርት ስገመግማቸው አንዳቸውም አላለፉም፡፡ የዋሆችንና የማያመዛዝኑ ሰዎችን ሊማርኩ የሚችሉ አንዳንድ ምርጥ ጥቅሶችን ቢጠቅሱም በዚህ ማር ውስጥ ግን ተደበቀ መርዝ መኖሩ አይቀርም ነበር፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፉትን ትንቢቶች ለመተርጎም እንደሚችሉ የሚያምኑ ‹‹ሰባኪዎች›› በየጣቢያዎቹ አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ‹ትቶ የመሔድ› ቅዠት ያስተምሩ ነበር ፤ይህም ‹የደስታ ኑፋቄ› ተብሎ የሚታወቀው ነው፡፡ ይህ ክህደት አንድ መቶ አምሳ ዓመታት እንኳን ያላስቆጠረ ሲሆን ክርስቶስ ከዓለም ፍጻሜ በፊት ቤተ ክርስቲያንን ከዓለም እንደሚያወጣት ያምናሉ፡፡ አንድ ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን ለመመለስ ያሰበ ፕሮቴስታንት ከላከልኝ ኢሜይል ልጥቀስ ፡-

‹‹ከበፊትም ጀምሮ እንደማደርገው (እውነተኛውን) ክርስትና ከልቤ እየፈለግሁ ነው፡፡ ስለኦርቶዶክስ እምነት ለመማር እፈልጋለሁ ፤ ከየት መጀመር እንዳለብኝ ግን አላውቅም፡፡ የሚጠቁሙኝ ነገር ካለ ደስ ይለኛል፡፡ እንዴት ወደ እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን የኦርቶዶክስ እምነት እንደመጣሁ ለማወቅ እንዲችሉ ትንሽ ስለቀደመ ማንነቴ ጥቂት ልበል፡፡ በመጀመሪያ

**በጴንጤቆስጤ እምነት ሥርዓት በኋላ ደግሞ በአንግሊካን እምነት ሥርዓት ውስጥ ሳለፉት ስድስት ዓመታት መጽሐፍ ቅዱስን እየተማርኩ ነበር፡፡ ትቶ የመሔድ በሚባለው የፈጠራ የዓለም ፍጻሜ ትምህርትም ተሳስቼ አምኜበት ነበር፡፡ የቤተክርስቲያንን ተቀደሰ ትውፊት በሚያቃልሉ ተቃውሞዎች ውስጤን ተቆጣጥረውት ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን በሚገባ ስመረምር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ለመረዳት የሚቻለው ከኦርቶዶክስ እይታ አንጻር ብቻ** (from an Orthodox perceptive) **እንደሆነ ተረዳሁ፡፡››**

*እንግዳ ትምህርትን መስማት በሐሳዊው መሲሕ ዘመን ለብዙዎች መውደቂያ ነው፡፡ ምክንያቱም ሐሰተኛው መሲሕ ሰዎችን ለማታለል መጽሐፍ ቅዱስን ስለሚጠቀምና መርዙንም በመጽሐፍ ቅዱስ በተሸፈነው እንክብል ውስጥ ስለሚያስቀምጥ ነው፡፡*

*አሉባልታን /ሐሜትን/ መስማትም ሌላው የጆሮአችን ጠላት ነው፡፡ ምናልባት በሐሜት ውስጥ አልተባበርም ወይም አላማም ልትሉ ትችላላችሁ ፤ ነገር ግን ሐሜትን መስማትም ጭምር ኃጢአት ነው፡፡ ሌሎች ሰዎችን ጉዳዮች ለማወቅ መጓጓት ቅዱስ ጴጥሮስ ከመግደልና ከመስረቅ ጋር አስተካክሎታል፡፡ ‹‹ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጉዳይ እንደሚገባ ሆኖ መከራን አይቀበል›› (፩ጴጥ. ፬÷፲፭)*

*ሐሜትን መስማት እያደር በሰዎች ላይ ወደ መፍረድ ፣ በእነርሱ ላይ የተሳሳተ አመለካከትን ወደ ማሳደርና ለሌሎችም ስለ እነርሱ ክፉነት ወሬን ወደ መንዛት ያደርሳል፡፡*

‹‹አንድ ሰው ስለ እኔ ለሰው እንዲህ ብሎ እንዳወራብኝ ሰማሁ›› የሚለው ጭንቀት ለብዙ ወጣቶች ትልቅ ራስ ምታት ነው፡፡ አንድ ሰው ወደ አንተ መጥቶ እገሌ ከጀርባህ እንዲህ ብሎ እያማህ ነው ብሎ ከነገረህ ከዚያ ሰው ጋር ተጨማሪ ውይይት ማድረግ የለብህም፡፡ ያልተረዳኸው ነገር ቢኖር ከጀርባህ እገሌ አምቶሃል ብሎ እየነገረህ ያለው ሰው ራሱ ሐሜተኛ ያለውን ሰው ከጀርባው እያማው መሆኑን ነው፡፡  ለዚህ መፍትሔው ምንድን ነው? መታማትህን ለሚነግርህ ሰው ‹‹በራሱ ፊት (ባማኝ ሰው ፊት) መጥተህ ይህንን ነገር ንገረኝ›› በለው፡፡ (ታምተሃል ብሎ የነገረህ ሰው ይህንን ማድረግ ካልቻለ ዋሽቶሃል ማለት ነው፡፡) አንድ ሰው እስካልተረጋገጠበት ድረስ ንጹሕ እንደሆነ አስታውስ፡፡

የማይጠቅሙ ተራ ወሬዎችንም መስማት ሌላው ኃጢአት ነው፡፡ ጌታችን ያለውን አስታውሱ ‹‹እኔ እላችኋለሁ፥ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤›› (ማቴ.፲፪÷፴፮) ከላይ የተረክነውን የመነኩሴውን ታሪክ አስታውሱ! ያ መነኩሴ ከሌሎች መነኮሳት ጋር ሲነጋገር ቆይቶ ወደ በዓቱ ከሔደ በኋላ እጅግ በተደጋጋሚ በአቱን ሲዞር አንድ መነኩሴ ተመለከተውና ምን እያደረገ እንደሆነ ጠየቀው ፤ እርሱም መለሰ ‹‹ስናወራቸው የነበርናቸውን ዓለማዊ ወሬዎች እያስወገድኩ ነው ፤ ወደ በአቴ ይገቡ መግባት አልፈልግም››

የመጨረሻው ልንላቀቀው የሚገባን ፈተና ሽንገላን መስማት ነው፡፡ ሁላችንም ሰዎች ስለ እኛ ጥሩ ነገር ሲናገሩልን መስማት እንወዳለን፡፡ ‹‹ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ››

(ሉቃ.፮÷፳፮) ሽንገላ ሐሳዊው መሲሕ በመጣ ጊዜ ሰዎችን ለማታለል የሚጠቀምበት ዋነኛ መሣሪያ ነው መጽሐፈ ዳንኤል የሚነግረን፡፡ በዳን ፲፩÷፳፩–፳፬ ላይ ‹‹በእርሱም ስፍራ የተጠቃ ሰው ይነሣል የመንግሥቱንም ክብር አይሰጡትም በቀስታ መጥቶ መንግሥቱን በማታለል ይገዛል፡፡›› ይላል፡፡ ዳግመኛም ‹‹ቃል ኪዳኑን የሚበድሉትንም በማታለል ያስታል ነገር ግን አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ይበረታሉ፥ ያደርጋሉም፡፡ በወደቁም ጊዜ በጥቂት እርዳታ ይረዳሉ ብዙ ሰዎችም በግብዝነት ወደ እነርሱ ተባብረው ይሰበሰባሉ፡፡›› ይላል፡፡

## ጆሮን ስተገቢው ነገር መጠቀም

አሁንም እዚህ ላይ ጆሮዎቻችንን በመስማት ተላመዷቸው ክፉ ነገሮች መከልከል አለብን፡፡ ለምሳሌ ጥሩ ዜማ በሰማህ ጊዜ በመንግሥተ ሰማያት ያለው ዜማ ምንኛ ያማረ እንደሆነ አስብ!

[2]‹‹እመቤታችን!

በጥዑመ ዜማ - ‹ተዐብዮ› ብላ - ስታመሰግነው

ደናግላን ሁሉ - አብረው ሲዘምሩ - ከእግሮቿ ሥር ሆነው.....!!

ሲቀ መዘምራን - ዳዊት በገናውን - በእጁ ይዞ ቆሞ

እልፍ በረከትን - ባገኘ ነበር ሰው - ቢሰማ ታድሞ››

የሚለውን ዝማሬ አስብ፡፡

---

[2] **There David stands with harp in hand as master of the choir.**
**Ten thousand times that man were blest that might this music hear**
**Our Lady sings Magnificat with tune harmonious and sweet**
**And all the the virgins sing their part sitting about her feet.**

ሌላው መልመድ ያለብን ነገር ደግሞ ነገሮችን ስንሰማ የጌታችንን መከራ ማስታወስ ነው፡፡ ለምሳሌ የሰዓት ደወል በሰማህ ጊዜ በጌታችን እጆች ላይ ሚስማሮች ሲቸነከሩ የተሰማውን ድምፅ አስታውስ፡፡

## ምላስን መቆጣጠር

መቅመስን በሚገባ መልመድ አስፈላጊ ነገር ነው ፤ አለዚያ ሰው የሚበላውን ምግብ ለይቶ ለመብላት አይችልም፡፡ ሁልጊዜ ጣፍጠው የሚዘጋጁ ምግቦችን መውደድና በተቃራኒው ደግሞ ተራ ምግቦችን መጥላት ወደ መንፈሳዊው ፍጹምነት የሚያደርስ መንገድ አይደለም፡፡ እናታችን ሔዋንን አስታውሱ ከተከለከለው ምግብ አንዴ ብቻ መጉረስ ያንን ያህል ውድመትን አስከትሏል፡፡ ነቢዩ እንዲህ ይለናል ‹‹ከዝሆን ጥርስ በተሠራ አልጋ ላይ ለምትተኙ፥ በምንጣፋችሁም ላይ ተደላድላችሁ ለምትቀመጡ፥ ከበጎችም መንጋ ጠቦትን ከጋጥም ውስጥ ጥጃን ለምትበሉ፥›› አሞ. ፮÷፬ እዚህ ጋር የተነቀፈው አኗኗራቸው ነው እንጂ የሚበሉት ምግብ አይደለም፡፡

ያንን ባለጸጋም አስታውሱ ‹‹ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር›› (ሉቃ. ፲፮÷፲፱) መጽሐፉ ‹‹ዕለት ዕለት›› የሚለው ላይ አተኩሮበታል፡፡ በአንዳንድ ጊዜ ልዩ ልዩ ውድ ምግቦችን መመገብ ኃጢአት አይደለም፡፡ ለምሳሌ በበዓላት እና እንግዶች በሚመጡብን ጊዜ፡፡ የጠፋው ልጅ አባትም ‹‹የሰባውን ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፥ እንብላም ደስም ይበለን›› ብሏል፡፡ (ሉቃ. ፲፭÷፳፫) ሌላው ቀርቶ በበረሃ ያሉ መናንያን አበው እንኳን እንግዳ ሲመጣባቸው የተለመደውን ደረቅ ዳቦና ውኃ በጨው

መመገባቸውን ያቆሙ ነበር፡፡ ለእንግዳው ክብር ሲባል ደቀ መዝሙራቸው ምስር እንዲቀቅል ይነግሩና አብረው ይመገባሉ፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል ‹‹መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤ በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ፡፡›› (ፊል. ፬÷፲፪) ይህም ማለት ጥሩ ማዕድን መመገብ እችላለሁ ፤ ረሃብንም መቋቋም እችላለሁ ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ የሚጣፍጡ ምግቦችን እመገባለሁ ፤ ተራ ምግቦችንም መመገብ ባለብኝ ጊዜ (ለምሳሌ በጾም ወቅት)እመገባለሁ፡፡ ማንኛውንም ምግብ ማጣጣምን ለምላስህ አስለምድ፡፡

## ወሬ ማብዛት

ወሬን ማብዛት ኃጢአት ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብዙ ጊዜ የተነገረ ጉዳይ ነው፡፡ የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ወሬኛነት በብሉይ ኪዳን የተነገሩ ናቸው፡፡ ‹‹በቃል ብዛት ውስጥ ኃጢአት ሳይኖር አይቀርም ከንፈሩን የሚገታ ግን አስተዋይ ነው፡፡›› ‹‹ጥቂት ቃልን የሚናገር አዋቂ ነው፥›› ‹‹የሰነፍ ድምፅ በቃሉ ብዛት ይሰማል፡፡›› (ምሳ. ፲÷፲፱ ፲፯÷፳፯ ፤ መክ. ፭÷፫)

ወሬን ስለማብዛት ከበድ ያለ ማስጠንቀቂያ የተሰጠው ግን ከራሱ ከክብር ጌታ ነው፡፡ በማቴ.፲፪÷፴፮–፴፯ ላይ ‹‹እኔ እላችኋለሁ፥ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል ፤ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ፡፡›› ብሏል፡፡

ይህም ማለት እንደ ዋዛ በምንናገረው በእያንዳንዱ ቃል በፍርድ ቀን እንጠየቅበታለን ማለት ነው፡፡ እንዴት ያስፈራ?!

አበው ‹‹ተናጋሪነት በራስ የኩራት ምልክት ነው›› ይላሉ፡፡ በጣም የሚያወራ ሰው ብዙ እውቀት እንዳለውና ይህንን እውቀቱንም ለዓለም ማካፈል እንዳለበት ይሰማዋል፡፡

ወሬን ማብዛት አሉባልታንና ሐሜትን ፣ ስም ማጥፋትን ይወልዳል፡፡ የክርክርና የመኮፈስም መነሻው ወሬን ማብዛት ነው፡፡ ወሬኛ ሰው የአድማጮቹን አድናቆት ለማግኘት ሲል ገጠመኞቹን የሚያወራው ከፊል እውነትን በግነት አስጊጦ ነው፡፡

ወጣቶች ምንም ስኅተት እንደሠሩ ሳይሰማቸው በሰዓታት የሚቆጠር ጊዜን በስልክ ማውራት ያጠፋሉ፡፡ ኂላ መልስ የምንሰጥበት ‹‹ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር›› የተባለውም ይህ ዓይነቱ ነው፡፡

ለሰዓታት በስልክ ማውራትን ያስቀረው አዲሱ ምትክ ደግሞ መልእክት መጻጻፍ ነው፡፡ በኢንተርኔት ምልልስ ማድረግ ሆኗል ነገሩ፡፡ ሌላው ቀርቶ አገልግሎቱን በስልክ ለማግኘት ስለሚቻል ኮምፒውተር መጠቀምም አይጠይቅም፡፡ የሚያገርመው ነገር በኢንተርኔት ለረዥም ሰዓታት ምልልስ ሲያደርጉ ከቆዩ በኂላ ከዚያው ሰው ጋር ለመነጋገር ስልካቸውን ማንሣታቸው ነው፡፡

አባቶቻችን ይህንን ኃጢአት በጥብቅ ተቃውመው የዝምታን በጎነት በተለያዩ መንገዶች አሳይተዋል፡፡ በአንድ ወቅት ቅዱስ አርሳንዮስ ‹‹ብዙ ተናገርሁ ፤ ተጸጸትሁም፡፡ በዝምታ ግን ተጸጽቼ አላውቅም›› ብሏል፡፡

ይህን ኃጢአት በመዋጋት ሒደት ውስጥ የመጀመሪያው እርምጃ ኃጢአት መሆኑን ማመን ነው። ‹ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር› የሚለውን የወንጌል ቃል በአእምሮ ውስጥ ማሳደር። ከዚህ ቀጥሎ ዝምታን መለማመድ ነው። ከአባቶች አንዱ የማውራት ፍላጎት ሲፈትነው በአፉ ውስጥ ጠጠሮች እስከመጨመር ደርሶአል። እናንተ ደግሞ ከዚህ በተሻለ መንገድ አሮጌ ልብስህን እንደ መዝጊያ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

## መምከር

ደግሞ መምከር ኃጢአት ነው እንዴ? ትሉ ይሆናል። አዎን! በአንዳንድ ሁኔታዎች ኃጢአት ነው! [3]አንደኛው ሳይጠየቁ ልምከር ማለት ነው። ሁለተኛው ለመምከር ብቁ ሳንሆን ስንቀር ነው። ችግሩ ምክር በተጠየቅን ጊዜ ምንም በማናውቅበት ጉዳይ ላይ በጉዳዩ ላይ እንደ ተጠያቂ ሊቅ መሆናችን ላይ ነው። ‹ኧረ እኔ አላውቅም› ለማለት አቅም ያላቸው ጥበበኞች ጥቂቶች ናቸው።

በሚያሳዝን ሁኔታ ብዙ ወጣቶች በመንፈሳዊ ጉዳዮችም ሆነ በእጮኝነት ሕይወታቸው ዙሪያ እርስ በእርሳቸው ምክር ይሰጣጣሉ። በጉዳዩ ላይ የሚያውቅን ሰው በመጠየቅ ፈንታ በቂ ልምድ ከሌለውና ምንም ሊጠቅማቸው ከማይችል ሰው ምክር ይፈልጋሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ የሚነግረን ነገር አለው።

[3] ይህ ሃሳብ በመጽሐፈ መነኮሳት ላይ ‹‹ይኸውም አስተምረን ሳይሉት ሰሚዎቹን የሚጠቅምበት ምክንያት ሳይኖረው ላስተምራችሁ የሚል ሰው ዐላዋቂ ነው እንጂ ዐዋቂ አይባልም።››(‹‹ወዝኬ ዘሰ ዘይሜህር ዘእንበለ ይኅሥሡ እምኔሁ ወዘእንበለ ምክንያተ ድልወት ለበቁዔተ ሰማዕያን ውእቱኬ አብድ ወአኮ ጠቢብ ››) ከሚለው ጋር የተስማማ ነው። (መጽሐፈ መነኮሳት / ፊልክስዩስ)

‹‹ዕውር ዕውርን ሊመራ ይችላልን? ሁለቱ በጕድጓድ አይወድቁምን?›› (ሉቃ. ፮÷፴፱)

በከባድ ጉዳዮች ላይ ደርሶ ምክር መስጠት ከባድ ኃጢአት ነው ፤ ምክንያቱም ምክር በምትሰጠው ሰው ጠባይ ላይ ተጠያቂ ስለሚደርግህ ነው፡፡ በእርግጥ አንድ ሰው የቤት ሥራውን እንድታሠራው ወይም ይህንን መሰል እርዳታህን ቢፈልግ ልትረዳው ይገባል፡፡ በአንጻሩ ጓደኛህ ‹‹እገሊት እኮ ለእጮኝነት ፈለገችኝ ፤ ምን ይመስልሃል?›› ቢልህ በእንዲህ ዓይነቱ ጠንከር ያለ ጉዳይ ላይ በመሰለህ መንገድ ለመምከር እንዳትነሣ ምክንያቱም ነገሩ ወደ ኃጢአት ቢያመራ ተጠያቂው አንተ ትሆናለህ፡፡

እንዲሁም አንድ ሰው በሱስ እንደተያዘ ፣ በፍትወታዊ ልማዶች እንደተጠመደ ቢነግርህ አንተ ራስህ ረዳት የሚያስፈልግህ ስለሆንክ ከመምከር ይልቅ ወደ ካህን እንዲቀርብ አበረታታው፡፡ ‹‹ታውቃለህ? እኔ ራሴ ተመሳሳይ ችግሮች ነበሩብኝ ፤ ወደ ንስሐ አባቴ ሔጄ ነግሬያቸው ከዚህ ችግር መውጣት እንደምችል አሳዩኝ›› ብለህም ልታበረታታው ትችላለህ፡፡

ሌላው ለጓደኛህ ልታደርግለት የምትችለው ነገር ስለ እርሱ መጸለይ ነው፡፡ የክርስትና ስሙን ጽፈህ ለንስሐ አባትህ በመስጠትም እንዲጸልዩለት አድርግ፡፡

‹‹አንዳንዴ ጉዳዩ በጣም ከባድ ቢሆንና ንስሐ አባቴ ሊያውቁት የሚገባ ቢሆን የጓደኛዬን ምሥጢር እንዴት መጠበቅ ይኖርብኛል?›› የሚል ጥያቄም አለ፡፡ ልታደርግ የምትችለው እየነገርካቸው ያለኸው የጓደኛህን ምሥጢር የሆነ ኑዛዜ መሆኑን

ለንስሐ አባትህ መንገር ነው። ከዚያ በኋላ አባትህ ይህን ጉዳይ ሌላውቀርቶ ለጓደኛህም ጭምር መልሰው ሊነግሩት አይችሉም። ነገርካቸውን ነገር ሳይገልጡም እግዚአብሔር ለጓደኛህ መንገድ እንዲመራው ሊጸልዩለት ይችላሉ።

## አፍንጫን መቆጣጠር

በምናሸትተው ነገር የፍትወት ሐሳቦችንና ስሜቶችን ሊያነቃቃ ይችላል። በጣም የሚያውዱ ሽቱዎች ሥጋን ለፍትወታዊ ድርጊቶች ይገፋፋሉ። ሴቶች ከሩቅ የሚጣሩ ሽቱዎችን በመቀባት ሌሎችን ማወክ የለባቸውም። መጽሐፍ ቅዱስ ውድ ልብሶችን ስለመግዛትና ልዩ የሆኑ ሽቱዎችን ስለመቀባት የሚለው ነገር አለ። አሞጽ ፮÷፮ ‹‹በፋጋ የወይን ጠጅ ለምትጠጡ ፥ እጅግ ባማረ ሽቱም ለምትቀቡ ፥ ወዮላችሁ!›› ሲል በኢሳይያስ ፫÷፳፬ ላይ ደግሞ ‹‹እንዲህም ይሆናል በሽቱ ፋንታ ግማት!›› ይላል።

የሚያውድ ሽታ ወደ ዝሙት ሐሳብ ከመራህ እየተመኘኸው ያለኸው ሥጋ ኢሳይያስ እንዳለው እንደሚበሰብስና ወደ ሽታ እንደሚለወጥ አስታውስ።

በምትጾምበት ወቅት ደግሞ የምግብ ሽታ ፈተና ሊሆንብህ ይችላል። ምግብ በሚሸጥባቸው ቦታዎች ስታልፍ በጣም የሚረብሽ ምግብ መዓዛ ያጋጥምሃል። ብቸኛው መፍትሔ ያንን ሽታ እንደምንተነፍሰው አየር አለመሳብ ነው። (don't inhale!)

የፋዩም ሊቀ ጳጳስ የነበረው ጻድቁ አባ አብርሃም በአንድ ወቅት በግብፅ ተወዳጅ ምግብ የነበረውን ‹ፔግዮን› የመብላት አምሮት መጣበትና ለደቀ መዝሙሩ እንዲያዘጋጅለት ነገረው።

አገልጋዩም የተባለውን ምግብ ካዘጋጀ በኂላ እንደደረሰለት ሲነግረው ‹‹ተወው!›› አለው፡፡ አገልጋዩ ከዚህም በኂላ ቆይቶ ሲጠይቀው የአባ አብርሃም መልስ ‹‹ተወው!›› ብቻ ነበር፡፡ ከጥቂት ቀናት በኂላ ምግቡ ተበላሸ፡፡ (በዚያን ጊዜ ማቀዝቀዣ አልነበረምና) አባ አብርሃም የተበላሸውን ምግብ እንዲያቀርብለት አገልጋዩን ጠየቀው፡፡ በጣም ይሸትት ነበር፡፡ ጻድቁም ለራሱ እንዲህ አለ ፡- ‹‹አብርሃም ልብህ የተመኘው እንግዲህ ይህንን ነበር ፤ እስቲ ብላ!...››

## አንፍንጫን በአግባቡ መጠቀም

በጎ መዓዛ አፍንጫህን ባወደው ጊዜ ልዩ መዓዛ ባለው ውድ ሽቱ ጌታዋን የቀባችውን ማርያምን አስባት፡፡ ‹‹ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ፡፡›› ዮሐ. ፲፪÷፫

## የምንነካውን ነገር መቆጣጠር

በእጅ መንካት በበደል መጀመሪያ (በጥንተ አብሶ) ወቅት ትልቅ ሚና ተጫውቶአል፡፡ ሰይጣን እንደ ዕባብ ሆኖ እናታችን ሔዋንን ባሳታት ጊዜ ክፉንና በጎውን ነገር የሚሳውቀውን ዛፍ አስመልክቶ እግዚአብሔር ምን ትእዛዝ እንዳዘዛቸው ጠየቃት፡፡ እርስዋም ‹‹እግዚአብሔር አለ፦ እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም፡፡›› ብላ ለዕባቡ መለሰችለት፡፡ ሔዋን በመጎምጀት እንድትቀጥፈው ፤ የሚያጓጓ መስሎ እንዲሰማት የተከለከለችውን ዕፅ መንካት ነበረባት፡፡

በመንካት የሚሰማን ስሜት ቢያስደስተንም ኅሊናችንን ግን ወዳልተቀደሱ ሃሳቦች መምራቱ አይቀርም፡፡ ለምሳሌ በአውቶቢስ ውስጥ ተቀምጠህ በጾታ ከአንተ ተቃራኒ ከሆነ ሰው ጋር ስትነካካ

ሰውነትህ በልብስ ቢሸፈንም መንፈሳዊ ያልሆነ ስሜት በሰውነትህና በኅሊናህ ላይ ሊፈጠር ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹን ሁኔታዎች አንዳንድ ጊዜ የምንዋጋቸው ቢሆኑም አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ልንመኛቸው ሁሉ እንችላለን፡፡ ስሜቱን መግዛትን የሚያውቅ ሰው ግን በማንኛውም መንገድ ከዚህ ሁኔታ ራሱን ያርቃል፡፡

በ‹ፓራዳይዝ ኦፍ ፋዘርስ› በተሰኘው መጽሐፍ ላይ አንድ ታሪክ አስታውሳለሁ፡፡ የአንድ ወጣት መነኩሴ እናት ልጅዋን ለመጠየቅ ወደ ገዳም ትሔዳለች፡፡ ይህ መነኩሴ እስከ መንደሩ መውጫ ድረስ እናቱን ለመሸኘት ተከትሎአት ይወጣል፡፡ ወደ መንደሩ ጫፍ ለመድረስ ግን አንድ ጥልቀት ወንዝ መሻገር ያስፈልግ ነበርና መነኩሴው እናቱን ተሸክሞ አሻገራት፡፡ ይህንን ከማድረጉ በፊት ግን የእናቱን ሰውነት ላለመንካት በብርድ ልብስ ጠቀለላት፡፡ እናቱ በድርጊቱ ተገርማ ‹‹እናትህ እኮ ነኝ!?...›› ስትለው ‹‹የፈራሁት የእናቴን ሰውነት መንካትን አይደለም ፤ ነገር ግን የአንቺን ሰውነት ስነካ ባለማወቄ ወራት የነካሁትን ሌላ ሰውነት እንዳያስታውሰኝ ነው፡፡›› አላት፡፡

ቅዱስ ይሁዳ ሌላው ቀርቶ [4]በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳን ሳይቀር እንድንጠላ አስጠንቅቆናል፡፡ (ይሁ. ፩፥፳፫) በአንዳንድ የልብስ መሸጫዎች የማሳያ መስኮቶች በምናየው እይታ ፣ በምርት ማስተዋወቂያ መጽሔቶችም ምክንያት ንጹሕ ያልሆነ ስሜት

[4] ‹‹አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ፡፡›› (ይሁ. ፳፫)

ሊፈጠርብን ይችላል፡፡ እነዚህን አልባሳት መንካትም እንዲሁ ላልተቀደሰ ስሜት ሊዳርገን ይችላል፡፡

የገዛ ሰውነታችንንም መነካካት ወደ ጋለ ሥጋዊ የስሜት መነሣሣት ሊገፋፋን ይችላል ፤ ይህም ስሜት ያልተቀደሰና የረከሰ ስሜት ነው፡፡ ብዙ ወጣት ወንዶችና ሴቶች ከዚህ ዓይነቱ ፈተና ጋር እንደሚታገሉ አውቃለሁ፡፡

በማኅበራዊ ግንኙነቶቻችን በሚኖረን አካላዊ መነካካት ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄን ማድረግ ያስፈልገናል፡፡ በተለይም በጾታ ተቃራኒያችን ከሆኑ ሰዎች ጋር ያለ ጥንቃቄ መላመድ አይገባንም፡፡ ወጣቶች አንዳንድ ጊዜ በጓደኝነት ስም በጾታ የማይመስሏቸውን ሲያቅፉና እጃቸውን በላያቸው ላይ ሲሳርፉ ይታያል፡፡ ምናልባት አንዳንዱ ‹‹ምንም ነገር አስቤ አይደለም›› ሊል ይችላል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ‹‹በውስጤ ምንም ነገር አይሰማኝም!›› ሊሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ስለ ራስህ በእርግጠኝነት መናገር ትችል ይሆናል፡፡ ስለሌላው ሰውስ? በምነካካው ሰው ላይ ሌላ ስሜት ፈጥሬ ከሆነ እኮ እጠየቅበታለሁ፡፡

ይህንን ሕዋሳትን የመግዛት ልምምድ ‹ዘመናዊነት› ተብሎ ከሚጠራው ሰውነትን በውድ ልብሶች በመልበስ ማቀመጠልን ፣ ውድ የሆኑ ቅባቶችንና ክሬሞችን ማስለመድን እስከመተው ድረስ ልንመለከተው ይገባል፡፡

ንክኪ ጥሩ ያልሆነ ስሜትን ወይም ስቃይን የምናስተናግድበት መሣሪያ ነው፡፡ የመንካት ስሜቱን መግዛት የቻለ ሰው ሕመምን መቋቋም ይችላል፡፡ በስቃዩም ውስጥ ጌታ ስለ እርሱ

የተቀበለውን ሥቃይ ያስባል፡፡ ባሕታዊው ቴዎፋን በዚህ ነገር ልምዱን አካፍሎናል፡፡ ‹‹እጄን ቢያመኝ በጌታ እጆች ውስጥ ዘልቀው የገቡትን ችንካሮች ላስብ ይገባኛል፡፡ ጀርባዬን ሲሰማኝ ጌታዬ ስለ እኔ የተቀበላቸውን ግርፋቶች ላስብ ይገባኛል፡፡ ከጎኔ ሕመም ሲሰማኝ በጦር መወጋቱን ላስብ ይገባኛል፡፡ ራሴን ባመመኝ ጊዜ የእሾኽ አክሊሉ በኅሊናዬ ሊመላለስ ይገባል፡፡››

*ምእራፍ አራት*

# ስለ ትውስታዎችና ስለፈጠራ ሃሳቦች

እግዚአብሔር ብዙ መረጃዎችን በአእምሮችን መያዝና በፈለግን ጊዜም አስታውሶ መጠቀም እንድንችል አድርጎ ፈጥሮናል፡፡ እግዚአብሔር የማስታወስ ችሎታን የሰጠን ከሁሉ በፊት ትእዛዛቱን እንድናስታውስ ነው፡፡ ‹‹የእግዚአብሔርንም ትእዛዝ ሁሉ ታስቡና ታደርጉ ዘንድ… ይሁን፡፡›› ዘኍ. ፲፭÷፴፱–፵

የጌታችን ደቀመዛሙርት በዚህ የማስታወስ ችሎታ ተጠቅመው ጌታ ከእነርሱ ጋር ሳለ የተናገራቸውን ቃላት በማስታወሳቸው ወንጌላትንና መልእክታትን ጽፈዋል፡፡ ወንጌላትም ከመጻፋቸው በፊት በምእመናን አእምሮ ውስጥ ስለነበሩ በቃል ትውፊትነት ቆይተዋል፡፡

የማስታወስ ችሎታ ለእኛ የተሰጠበት ሌላው ምክንያት እግዚአብሔር ለእኛ ያደረጋቸውን መልካም ነገሮች ሁሉ እንድናስታውስ ነው፡፡ ‹‹ሙሴም ሕዝቡን አለ፡፡ ከባርነት ቤት ከግብፅ የወጣችሁበትን ይህን ቀን አስቡ፥ እግዚአብሔር ከዚህ ቦታ በብርቱ እጅ አውጥቶአችኋልና›› (ዘጸ. ፲፫÷፫)

በሌላ በኩል ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ ፈጥሮ ማሰብ ግን የእግዚአብሔር ሥጦታ አይደለም፡፡ ባሕታዊው ቴዎፋን እንደሚነግረን ለባዊያን (የሚያስቡ) የሆኑት ሰውና መላእክት ከዚህ ዓይነቱ የፈጠራ ሐሳብ ጋር አልተፈጠሩም፡፡ ሰይጣን ከጸጋው የተዋረደው ይህን ዓይነቱን የፈጠራ ሐሳብ ማሰብ ሲጀምርና

ከእግዚአብሔር እኩል መሆን እንደሚችል ሲያስብ ነው፡፡ እንዲሁም ከተከለከሉት ዕፅ ቢበሉ እንደ አግዚአብሔር እንደሚሆኑ በነገራቸው ጊዜ ሰይጣን ለአዳምና ለሔዋን የፈጠራ ሐሳብን አስስተዋውቆአቸዋል፡፡

በኃጢአት እንድንወድቅ ለማድረግ ሰይጣን ትውስታንም ሆነ የፈጠራ ሃሳብን ሊጠቀም ይችላል፡፡ በሐሳባችን የሚታየን ማንኛውም ነገር በውስጣችን አድናቆት ያሳድርና ቆይቶ ለመልካምም ሆነ ለክፉ ነገር ልናስታውሰው እንችላለን፡፡

በትውስታና በፈጠራ ሃሳብ የምንሠራው ኃጢአት በሚከተሉት ምክንያቶች በሕዋሳቶቻችን ከምንሠራቸው ኃጢአቶች በላይ የከፋ ነው፡፡

በሕዋሳቶቻችን የምንሠራቸው ኃጢአቶች የሚጀምሩት ሕዋሳትን ከሚያነሣሡ ነገሮች ነው፡፡ አንድ ሰው ወይም አንድን ነገር ከማየት ፣ ከመስማት ፣ ከማሽተት ወዘተ. ይህም ማለት በሕዋሳቶቻችን የሚፈጸሙ ኃጢአቶች የሚመጡት በውጪያዊ ነገሮች ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ በተለየ ግን በትውስታዎቻችን ምክንያት ግን በማናያቸውና በሌሉ ነገሮች ጭምር ልንፈተን እንችላለን፡፡

የምንፈጥረው ሃሳባችን ለነገሮች ልዩ ገጽታ የሚሰጣቸው ሲሆን አንዳንድ ነገሮችን ከሆኑት በላይ አጓጊና የሚያስደስቱ ያደርጋቸዋል፡፡ በመጨረሻ ሕዋሳቶቻችን በእንቅልፍ የሚወድቁ ሲሆን በማስታወስና ፈጥሮ በማሰብ የምንፈጽመው ኃጢአት ግን በተኛንም ጊዜ በሕልማችን መጥቶ ይፈትነናል፡፡

# የማስታወስ ኃጢአቶች

## የቀደሙ ክፉ ሥራዎቻችንን ማስታወስ

በቅዳሴ ላይ ‹‹ሞትን ከምታመጣ ከክፉ ሃሳብ እንለይ ዘንድ›› ወደ እግዚአብሔር እንለምናለን፡፡ ክፉን ማሰብ ማለት እኔ ራሴ ከዚህ በፊት የሠራሁትን ክፉ ሥራ አለዚያም ሌሎች በእኔ ላይ የሠሩትን ክፉ ሥራ ማሰብ ማለት ነው፡፡

### የቀደመ ዝሙት

ቀድሞ የፈጸምናቸው ኃጢአቶች ትውስታ ከኃጢአቶቹ ከራቅን በኋላ ሊያውከን ይችላል፡፡ ከበረሃውያን ቅዱሳን መካከል አንዳንዶቹ በዚህ ፈተና ለዓመታት ተሰቃይተዋል፡፡ ቅዱስ ሙሴ ጸሊም በቀደሙ ኃጢአቶቹ ትውስታ ለረዥም ጊዜ ተፈትኖ ነበር፡፡ በታላቁ ቅዱስ መቃርዮስ ዘመን የነበረችው እማ ሣራ ደግሞ ጌታ ከዚህ ፈተና አላቅቆ ነጻ እስካደረጋት ጊዜ ድረስ ለዐሥራ አራት ዓመታት ተፈትናለች፡፡

በቴሌቪዥንም ሆነ በመረጃ መረብ የተመለከትናቸው ልቅ የሆኑ የዝሙት ትዕይንቶች በኅሊናን ተቀርጸው ይቀሩና በየጊዜው በትውስታ እየመጡ ሊፈትኑን ይችላሉ፡፡

### ቁጣ

ከአንድ ሰው ጋር ልከራከር ወይም ልጣላ እችላለሁ፡፡ ከታረቅንም በኋላ ግን ያለፈውን በማስታወስ የሚመጣው የቁጣና የበቀል ሐሳብ ግን የሚጎዳ ነው፡፡ ዲያቢሎስ ነገሮችን ከሆኑት በላይ

ተባብሰው እንዲታዩን ያደርጋል፡፡ ብዙ ባልና ሚስት በዚህ የተነሣ በችግር ላይ ናቸው፡፡ ጠዋት ወደ ሥራ ከመሔድ በፊት የሚፈጥሩትን አነስተኛ ጭቅጭቅ ዲያቢሎስ በአግባቡ ይጠቀምበታል፡፡ በሥራ ላይ እያሉ ሁለቱም የጠዋቱን ጭቅጭቅ የሚያስታውሱበትን አጋጣሚ ያመቻቻል፡፡ በሁለቱም ልብ ኃይለኛ ቁጣና ብስጭት ይቀሰቀሳል፡፡ ከሥራ ወደ ቤታቸው ተመልሰው ሲገናኙ በጠዋት የተነሣው ትንሽ አለመግባባት ለሳምንታት ያህል የሁለቱንም ሰላም ሊነጥቅ ወደሚችል ትልቅ ጠብ ይሆናል፡፡ ፍቺዎች የሚጀምሩት በምን ሆነና?

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ጭቅጨቅ በተነሣ ቁጥር የቆዩ ጉዳዮችን ፈልፍለው በማስታወስ እያነሡ ይጨቃጨቃሉ፡፡ ለምሳሌ ከተጋቡ ዐሥር ዓመታትን ያሳለፉ ባልና ሚስት ይኖራሉ፡፡ በተጣሉ ቁጥር ሚስት ባሏ በጫጉላቸው ጊዜ ያደረገውን ወይም ያላደረገውን ነገር እያነሣች ልትናገረው ትችላለች፡፡ በተመሳሳይ ባልየውም በተጫጩ ጊዜ እናቷ የተናገሩትን ነገር እያነሣባት ሊናገራት ይችላል፡፡

**መፍረድ**

የሆነ ሰው ያደረገውን ነገር ልትሰማ ወይም ልታይ ትችላለህ ፤ ወዲያውኑም በዚያ ሰው ላይ ትፈርዳለህ፡፡ ምናልባት በዚያ ሰው ላይ በመፍረድህ ተጸጽተህ ተናዝዘህም ሊሆን ይችላል ፤ ነገሩ ግን አያበቃም፡፡ ያንን ሰው ባገኘኸው ቁጥር ያደረገውን እያስታወስክ በውስጥህ ትፈርድበታለህ፡፡ ምናልባትም እኮ ያ ሰው ባደረገው ነገር ተጸጽቶ ኃጢአቱን ተናዝዞ ፣ ያደረገውን ነገር

ረስቶትም ሊሆን ይችላል፡፡ አንተ ግን አሁንም በማስታወስህ ምክንያት በሰው ላይ በመፍረድ ኃጢአት ትወድቃለህ፡፡

## ከንቱ ውዳሴ

አንዳንድ ጊዜ ለእኛ ጥሩ የመሰለንን ነገር ልናደርግ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ ሁለት ሰዎችን አስታርቄ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን ለእነሱ የተናገርኳቸውን ጥበብ የተሞሉ ንግግሮች ማስታወስ እጀምራለሁ፡፡ በውስጤም ‹‹ቀላል ሰው አይደለሁም ለካ!›› እላለሁ፡፡ አንድ የሰንበት ትምህርት ቤት መምህር የማስተማር ጸጋ ሊሰጠው ይችላል፡፡ ይህ ጸጋ ግን የተሠጠው ከመምህሩ ብቃት ሳይሆን ለተማሪዎቹ ሲባል ነው፡፡ ነገር ግን እሱ የተናገራቸውን ቃላት እያስታወሰ ከእግዚአብሔር የተሰጡ መሆናቸው ቀርቶ ከራሱ ያመነጫቸው አድርጎ በማሰብ ራስን ከፍ ወደ ማድረግ ልቡ ይሞላል፡፡

ይህንን ፈተና እንዴት እንደምትዋጋው መንገዱን ልንገርህ! እንዲህ ዓይነቱ ሐሳብ በኅሊናህ ማደግ ሲጀምር ነቢዩ በለዓምን ለመገሠጽ እግዚአብሔር አህያን እንደተጠቀመ አስታውስ! (ዘኁ. ፳፪÷፳፩–፴፫ ፪ .፪÷፲፬–፲፰) ለራስህም እንዲህ በለው ፡- ‹‹በተናገርኳቸው ቃላት እንድመካ ከበለዓም አህያ የተሻለ ሥልጣን የለኝም!››

# በፈጠራ ሃሳብ የሚፈጸሙ ኃጢአቶች

## ዝሙት

በጾታ ከአንተ ተቃራኒ ከሆኑ ሰዎች ጋር አብረህ ትሠራለህ እንበል። አብራህ የምትሠራው ሴት ረጋ ያለችና ፈጽሞ ከአንተ ጋር ሌላ ግንኙነት የማትፈጥር ልትሆን ትችላለች። ነገር ግን በፈጠርኸው ሐሳብህ በንጽሕና ካለችው ሴት ጋር ብዙ ግብረ ዝሙት ልትፈጽም ትችላለህ።

እንዲሁም በአለባበሷ ሥርዓት ያላትን ሴት በፈጠራ ሐሳብህ የሚያስደስትህን የማይሆን ልብስ ልታለብሳት ወይም ዕርቃኗን አድርገህ ልታስባት በሐሳብህም በዝሙት ልትወድቅ ትችላለህ። ባየሃትም ቁጥር በሐሳብህ የፈጸምኸውን ዝሙት ማስታወስ ትጀምራለህ። ጾታዊ ጥቃት ማድረስስ የሚጀመረው በእንዲህ ዓይነቱ ሐሳብ መነሻነት አይደል?

ሌላው ክፉ የፈጠራ ሐሳብ ሰዎችን ያለ አግባብ በዝሙት አጣምሮ ማሰብ ነው። ምሳሌ ልስጣችሁ። በአንድ ምግብ ቤት ውስጥ ወይም በአውቶቢስ ውስጥ አንድ ሽማግሌ ከአንዲት ወጣት ጋር ተቀምጠው በወዳጅነት ሲነጋገሩ ልታዩ ትችላላችሁ። በዚህ ወቅት ክፉ ሥዕል በኅሊናችሁ ይመጣና ወጣቷን ሴት ከአለቃዋ ጋር የምትዘሙት አድርጋችሁ ታስባላችሁ። በእውነታው ግን ልጅቷ የተቀመጠችው ከአባቷ ጋር ሊሆን ይችላል። እናንተ ግን ከፍትወት ሐሳብ አልፎ በንጹሐን ላይ በመፍረድ ኃጢአት ወድቃችኋል።

**ቁጣ**

ሁልጊዜ የሚያቃልልህ አለቃህ ወይም በትምህርት ቤት የሚያስቸግርህ በጥባጭ ሰው ሊኖር ይችላል፡፡ በእውነታው ዓለም ምንም ልታርደግ አትችልም ፤ በዚህ ፈንታ ግን በምትፈጥረው ሐሳብ ግን ትበቀለዋለህ፡፡ ያንን ሰው ስትሰድበው ወይም ወደ ማጥ ውስጥ ስትጨምረው ይታይሃል፡፡ ወይም በኅሊናህ አንዳች አደጋ ወይም የመኪና አደጋ ሲደርስበት ፣ ከረዥም ሕንጻ ላይ ሲፈጠፈጥ ወዘተ የመሳሰሉ ክፉ ሐሳቦች በልብህ እየተመላለሱ በደስታ ሊሞሉህ ይችላሉ፡፡ ያልገባህ ነገር ግን በሐሳብህ ሰው እየገደልህ ያለህ መሆንህን ነው፡፡

**መፍረድ**

አንድ ሰው የሚያደርገውን መልካምም ሆነ ክፉ ነገር አይተን የምንታዘብ ከሆነ በኅሊናችን ያንን ሰው ስናስተምረው ይታየናል፡፡ ንስሐ እንዲገባ ስንነግረው ፣ ስለ ክፉ ሥራዎቹ ስንገሥጸው ፣ ከፈጣሪ ዘንድ እርሱ ያደረገውን የሚያደርጉ ሰዎች የሚጠብቃቸውን ፍርድ ስንነግረው ፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች የተሞላ ስብከትን ለዚህ ሰው ስንሰብክ ይታየናል፡፡ ያልተረዳነው ነገር ቢኖር በከፋ የመፍረድ ኃጢአት ላይ መውደቃችንን ነው፡፡ እኛ እግዚአብሔር በዚያ ሰው ላይ ከሚፈርደው በላይ በመፍረዳችን እግዚአብሔር ሊፈርድብን እንደሚችልም ጭምር አልተረዳንም፡፡

ለሰንበት ትምህርት ቤት መምህራኖቻችን ፣ ለወላጆቻችን ሌላው ቀርቶ ለንስሐ አባቶቻችን ጭምር ልናስተምር የሚቃጣን ትምህርት ከዚህ ዓይነቱ የድፍረት ሃሳብ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

## ከንቱ ውዳሴ

ዲያቢሎስ አንዳንድ ጊዜ ፈጥረህ በምታስባቸው እይታዎችህ ጻድቅ በመሆንህ እንድትደሰት ያደርግሃል። ለምሳሌ እኔ ራሴን በቅድስና ሕይወቱና ጥበብ በተሞሉ ንግግሮቹ የሚልዮኖችን ነፍስ የሚታደግ ዝነኛ ካህን እንደሆንኩ በማሰብ እንድደሰት ሊያደርገኝ ይችላል። ወይም ደግሞ ሌሎች ራሳቸውን ብዙ አርድእት እንዳላቸውና እንደዘጉ መነኩሴ / መነኩሲት አድርገው እንዲያልሙ ሊያደርጋቸው ይችላል።

እኔ እንኳን የዐሥራ ሁለት ዓመት ልጅ እያለሁ አንዳንድ ጊዜ ሰማዕት እንደሆንኩ አድርጌ የምደሰትበት ጊዜ ነበር። ‹‹ቅድስናዬ››ን የሚፈታተኑ የዲያቢሎስ ጥቃቶችና ሥቃዮችን ሁሉ በጽናት ስቋቋማቸው ይታየኝ ነበር።

## የቀን ሕልም

ማንም ሰው ከቀን ሕልም ነጻ አይደለም። ይሁንና ከመጠን በላይ በቀን ሕልም እየዋኙ መደሰት ግን ንስሐ ልንገባበት የሚያስፈልግ ኃጢአት ነው። የቀን ሕልም መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ ፣ በመማር ፣ በመጸለይ ልናሳልፈው የምንችለውን ጠቃሚ ጊዜ የሚያባክን እና ጥቅም የሌለው ነገር ነው። ብዙ ተማሪዎች መጽሐፋቸውን ገልጠው ፣ እርሳሶቻቸውን ቀርጸው ሊያጠኑ ይቀመጣሉ ፤ ብዙም ሳይቆዩ ግን ኀዘንና ደስታን በሚያፈራርቁባቸው ሐሳቦች ውስጥ መዋኘት ይቀጥላሉ።

የዚህ የቀን ሕልም ዋነኛ አደጋው በጤነኛ ሐሳቦች ተጀምሮ በጾታዊ ምኞቶች መጠናቀቁ ላይ ነው። ወጣት ሴቶች ስለ ሰርጋቸው

ያልማሉ፡፡ ሲያገቡ የሚለብሱትን ቀሚስ ፣ ስለ ሚዜዎቻቸው ፣ ሰርጉን ስለሚያደርጉበት ቤተ ክርስቲያን ፣ ስለሚደረግላቸው አቀባበል.... ይህ በተመስጦ የሚታሰብ በጎ ሐሳብ በዚህ አያቆምም፡፡ ስለ ጫጉላ ምሽት በማሰብ ይጠናቀቃል፡፡

## ፍቅረ ዓለም

ዓለምን መውደድ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል ነው፡፡ (ያዕ.፬÷፬) ቅዱስ ያዕቆብ በዚሁ ጥቅስ ላይ ዓለምን የሚወድ ቢኖር የእግዚአብሔር ጠላት ሆኗል ይለናል፡፡ ይህ ሆኖ ሳለ ግን እኛ በምንፈጥራቸው ሐሳቦቻችን በታላላቅ አብያተ መንግሥታት ስንኖር ፣ ውድና ዘመናዊ ልብሶችን ስንለብስ ፣ አሉ የሚባሉ መኪኖችን ስንነዳ ይታየናል፡፡ መኪኖች በተለይ ከዐሥር ዓመት በታች ባሉ ሕጻናት ኅሊና ትልቅ ነገሮች ናቸው፡፡ ስለ መኪኖች ማውራት በመኝታ ቤቶቻቸው የመኪኖች ሥዕል መለጣጠፍ ፣ መኪኖችን መመኘት ሥራቸው ነው፡፡

በቶሮንቶ ካደረግነው አንድ ጉዞ ስንመለስ በመኪናዬ ያደረስኳቸው ወጣቶቻችን አሳስቦአቸው የሚነጋገሩበት የወሬያቸው ርእስ ስለ መኪኖች ነበር!

ይህ ፈተና ዲያቢሎስ ጌታችንን ለመፈተን ካቀረባቸው ሦስት ፈተናዎች አንዱ ነው፡፡ ጌታችን ወደ ተራራ ወስዶ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ ክብራቸውንም አሳይቶ፡፡ ‹‹ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ አለው፡፡›› (ማቴ. ፬÷፱) አዎን ያን ጊዜ ጌታችን ዲያቢሎስን ገሥጾታል፡፡ ነገር ግን ዲያቢሎስ እኛን

በተመሳሳይ ተንኮሉ የዓለምን ነገሮች እያሳየ ሊጥለን ስንት ጊዜ ሞክሮ ይሆን?

## ምግብን እያሰቡ መጎምዠት

ይህ ዓይነቱ ሃሳብ በተለይ በጾም ወቅት አደገኛ ነው፡፡ ዐቢይ ጾም ሊጠናቀቅ ሁለት ሳምንታት በሚቀሩት ጊዜ በዕለተ ትንሣኤ ሌሊት ከቅዳሴ መልስ ስለሚቀርበው ልዩ ምግብ እያሰብክ ልትጎመዥ ትችላለህ፡፡ ምግቡ በአፍህ እያላመጥኸው ያለህ ያህል እና አፍንጫህን ሲያውደው ይሰማሃል፡፡ አፍህ በምራቅ መሞላት መጀመሩም አይቀሬ ነው!

በጾም ወቅትም ባይሆን እንኳን ድንገት የምትወዳቸውን የምግብ ዓይነቶች እያሰብህ በመጎምዠት ምራቅህን ልትውጥ ትችላለህ፡፡ ያልገባህ ነገር ግን በኅሊናህ ሆዳም እየሆንህ መሆኑን ነው!

በብሉይ ኪዳን ይህ ዓይነቱ ኃጢአት እስራኤላውያንን ከግብፅ ከወጡ በኋላ ድል አድርጓቸው ነበር፡፡ ‹‹በመካከላቸውም የነበሩ ልዩ ልዩ ሕዝብ እጅግ ጕመጁ የእስራኤል ልጆች ደግሞ ያለቅሱ ነበር፡፡ የምንበላውን ሥጋ ማን ይሰጠናል?›› ለሙሴ እንዲህ አሉት ፡- ‹‹በግብፅ ያለ ዋጋ እንበላው የነበረውን ዓሣ፥ ዱባውንም፥ በጢኹንም፥ ኩራቱንም፥ ቀዩንም ሽንኩርት፥ ነጩንም ሽንኩርት እናስባለን ፤ አሁን ግን ሰውነታችን ደረቀች ዓይናችንም ከዚህ መና በቀር ምንም አታይም አሉ፡፡›› (ዘኍ. ፲፩÷፭) እግዚአብሔር የፈለጉትን ሰጣቸው ፤ ሆኖም ስለ ሆዳምነታቸውና መስገብገባቸው ተቀጡ፡፡ ‹‹ሥጋውም ገና በጥርሳቸው መካከል ሳለ ሳያኘኩትም፥ የእግዚአብሔር ቍጣ

በሕዝቡ ላይ ነደደ እግዚአብሔርም ሕዝቡን በታላቅ መቅሠፍት እጅግ መታ:: የጐመጁ ሕዝብ በዚያ ተቀብረዋልና የዚያ ስፍራ ስም የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ::›› (ዘኁ.፲፩÷፴፫)

## በፈጠራ ሐሳቦች ኃጢአት ባለመሥራት መፍትሔው ምንድር ነው?

የመጀመሪያው እርምጃ እነዚህን የፈጠራ ሐሳቦች ኃጢአት መሆናቸውን ማመን እና ምንም የማይጎዱ ሐሳቦችና መዝናኛዎች ናቸው ብሎ አለማሰብ ነው:: እንዲሁም እነዚህን ኃጢአቶች በንስሐ ጊዜ መናዘዝ ይገባል:: ሌሎች ኃጢአቶችን እንደምንዋጋቸው ሁሉ እነዚህንም ኃጢአቶች ድል ለማድረግ መጸለይና ረድኤት እግዚአብሔርን መጠየቅ ያስፈልጋል::

### ምእራፍ አምስት

# የድፍረት ኃጢአቶች

በመዝሙር ፲፰÷፲፫ ላይ ቅዱስ ዳዊት ‹‹የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ፥ ከታላቁም ኃጢአት እነጻለሁ።›› ብሏል።

እነዚህ የድፍረት ኃጢአቶች ምንድር ናቸው? የተሠወሩት ናቸው። ኃጢአት የማይመስሉ ነገር ግን በውሸት ጽድቅ ውስጥ የተሸፈኑ ኃጢአቶች ናቸው። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድና እግዚአብሔርን ደስ በማያሰኝ መንገድ የሚደረጉ መልካም ሥራዎችም ሊሆኑ ይችላሉ። ይህን የመሰሉት ኃጢአቶች እንደ በጎ ሥራ ያማሩ ኃጢአቶች በመሆናቸው ‹የቀኝ እጅ ኃጢአቶች› ይባላሉ።

## የድፍረት ኃጢአት ምሳሌዎች

### ፩. በራስ መመካት

ስብከት ስትማር ልብህ እንደተነካ ይሰማሃል ፤ እንዲሁም በውስጥህ ጽድቅን የመከተል ምኞት እንደ እሳት ይንቀለቀላል። ስለዚህም በታላቅ መንፈሳዊ ቅናት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ፣ መጾም ፣ አብዝቶ መጸለይ ትጀምራለህ። ከተለመደው የተለየ (የእግዚአብሔር ጸጋ የሚመስልህ) ኃይል እየመራህ እንዳለ ይሰማሃል ፤ እንዳይሆን ይሆንና በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ ቀደመ ማንነትህ ትመለሳለህ ፤ ከበፊቱም ብሰህ ቁጭ ትላለህ። ችግሩ በራስ

መመካት ነው፡፡ መፍትሔውም ወደ መምህረ ንስሓ መሔድና ማማከር ነው፡፡ የንስሓ አባታትህ ተገቢውን ጸሎት ፣ ጾምና ስግደት ሊያዝዝህ ይችላል፡፡

## ፪. እጅግ ጻድቅነት

በምክረ ካህን በተገቢው መንገድ እየተመራህ እያለ እንኳን ዲያቢሎስ ከንስሓ አባትህ ትእዛዝ በላይ አንዳንድ ነገሮችን እንድታደርግ ሊያሳምንህ ይችላል፡፡ ‹‹ምናልባትም እኮ አባ የአንተን መንፈሳዊ ደረጃ አያውቁ ይሆናል!›› ‹‹አዬ! የንስሐ አባትህ መንፈሳዊ ዕድገትህን እያዘገዩብህ ነው!›› ብሎ ሊነግርህ ይችላል፡፡ ስለዚህም የምታደርጋቸውን የመንፈሳዊ ተጋድሎ ጥረቶች ሁሉ ከንስሐ አባትህ መደበቅ ትጀምርና ኃጢአትህን ብቻ መናዘዝ ትጀምራለህ፡፡ ይህንን ማድረግ አንድ ጊዜ ከጀመርህለት ለረዥም ሰዓታት እንድትጾም ፣ ከምንጊዜውም በበለጠ እንድትጸልይ ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን አብዝተህ እንድታነብ ዲያቢሎስ በጥረትህ ላይ ሊያግዝህ ሁሉ ይችላል፡፡ (ምንም ዓይነት ፈተና ባለመፈተን ማለት ነው፡፡)

ዲያቢሎስ ለምንድር ነው እንዲህ የሚያደርገው? የመንፈሳዊ ተጋድሎ ሙከራህ ወደ ፍጹምነት የምትደርስበት መንገድ መሆኑ ቀርቶ ራሱ ግብህ እንዲሆን ለማድረግ ነው፡፡ እናም ምን ያህል ሰዓታት እንደጾምክና ምን ያክል እንደሰገድህ በማሰብ መደሰት ትጀምራለህ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ይነግረናል፡፡ ‹‹እጅግ ጻድቅ አትሁን፥ እጅግ ጠቢብም አትሁን፥ እንዳትጠፋ፡፡›› (መክ. ፯÷፲፯)

‹‹እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው፥ እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ›› (ሮሜ. ፲፪÷፫)

ቅዱስ እንጦኒ ዘወትር ጸሎቱን ፈጽሞ ዕረፍት በሚያደርግበት ሰዓት ዲያቢሎስ መታ መታ እያደረገ ‹‹እንጦኒ ተነሣና ጸልይ!›› ይለው ነበር፡፡ ጥበበኛ የነበረው ቅዱስ እንጦኒ ግን ‹‹አንተን አልሰማህም፤ ስፈልግ እጸልያለሁ›› ይለው ነበር፡፡

ሁሉን ነገር በመጠን መሆንና ማድረግ ይገባል ፤ ወደ ቀኝም (እጅግ ጻድቅ ሳይሆኑም) ወደ ግራም (በኃጢአተኝነት) የሚኖሩትን የመጠን አኗኗር አበው የከበረ የልዕልና መንገድ ብለው ይጠሩታል፡፡

መነኮሳት ለጾም ለጸሎትና ለንባብ በአበምኔት የሚታዘዝ መመሪያ ያላቸው ለዚህ ነው፡፡ ስለ መንፈሳዊ ሕይወት የንስሐ አባትን ማማከርና ለእያንዳንዱ ነገር መመሪያ ይሰጡ ዘንድ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡

## ፫. ራስን መቅጣት

አንዳንድ ጊዜ በራስ መር መንፈሳዊነታችን (do it yourself spirituality) ለሠራናቸው ኃጢአቶች ራሳችንን እንቀጣለን፡፡ በዚህ ስኅተት ስንያዝ ችግራችንን የምንፈታ ስለሚመስለን ጾም ጸሎታችንና ስግደታችን የበዛ ይሆናል፡፡ ወዲያውም ይህ አካሔድ ወደ ሚከተሉት ይመራናል ፦

## ፬. ለራስ ነፃነት መስጠት

ለምሳሌ በጾም ወቅት በአውሮፕላን ተሳፍረህ ስትሔድ የሚቀርብልህ ምግብ የፍስግ ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ ብዙ እንደጾምክና አሁን ዕረፍት ማድረጊያህ ጊዜ እንደሆነ ታስብና ለራስህ ያለ መጾም መብት ትሰጣለህ። ያልተረዳኸው ነገር ግን ዲያቢሎስ ለካህናት የተሰጠውን የማሠርና የመፍታት ሥልጣን ለራስህ እንድትሰጥ እንዳደረገህ ነው።

በእውነቱ ከሆነ እያሰረህና እየፈታህ ያለው ዲያቢሎስ ነው። እርሱ መንፈሳዊ አባትህን እንድትተው አድርጎ እርሱ በመንፈሳዊ ሕይወት ጉዳይ አማካሪህ ሆኗል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ይላል፡- ‹‹መብራትንም አብርቶ በስውር ወይም በእንቅብ በታች የሚያኖረው የለም፥ የሚገቡ ሰዎች ብርሃኑን እንዲያዩ በመቅረዝ ላይ ያኖረዋል እንጂ።›› (ሉቃ. ፲፩÷፴፩)

የበረሃ አባቶች የዚህ ቃል ሐሳብ ‹‹መንፈሳዊ ተጋድሎችህን ከመንፈሳዊ አባትህ አትሸሽግ ፤ ለንስሐ አባትህ ሳትናገር መንፈሳዊ ሥራ አትጀምር›› ማለት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

## ፫. የተሳሳተ የጻድቅነት ስሜት

በዚህ መንገድ ከቀጠልህ ድኅነትህን እያጣህና ወደ ሲኦል እየተነዳህ እያለ ዲያቢሎስ በጎ ሥራ እየሠራህ እንዳለህና በዘላለም ሕይወት ጎዳና ላይ እንዳለህ እንዲሰማህ ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለዚህ ነገር ያስጠነቅቀናል ፡- ‹‹እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ እንዳይሆን ተመልከት።›› (ሉቃ.፲፩÷፴፭) በራእይ ፫÷፲፯ ላይ ጌታ በሎዶቅያ ያለውን የቤተ ክርስቲያን አለቃ እንዲህ ሲል ይገሥጸዋል። ‹‹ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ

አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፥ ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ፥ ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፥ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኵል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ።››

እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች የጠፉ ያህል ናቸው። ባሕታዊው ቴዎፋን እንደሚነግረን ራሳቸውን ጻድቅ አድርገው የሚያስቡ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ የሚረዱት ከሞቱ በኋላ ነው። ጌታችን እንዲህ ሲል የተናገረው ስለ እነርሱ ነው ፦ ‹‹በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል። የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።›› (ማቴ. ፯፥፳፪)

## ፯. የሐሰት መገለጦች ፣ ራእዮችና ሕልሞች

በተሳሳተ አስተሳሰብህ እንድትቀጥል ለማድረግ አንዳንድ ጊዜ ዲያቢሎስ ነገሮችን ከመሆናቸው በፊት እንድታውቃቸው ሊያደርግህ ይችላል። ወይም የሌሎች ሰዎችን ሐሳብ እንድታውቅ ሊያደርግህ ይችላል።

ዲያቢሎስ እንዴት ይህን ማድረግ ይችላል? በጣም ቀላል ነው! ለምሳሌ ሀገር ቤት ያሉ አያትህ በጠና እንደታመሙ ያውቃል ፤ ስለዚህ ይህንን ሐሳብ በአንተ ኅሊና እንዲታሰብ ያደርጋል። አንተም ደንገግጠህ ስልክ ትደውላለህ ፤ በዚህ ጊዜ አያትህ በጣም

እንደታመሙ ይነገርሃል፡፡ ይህንን ስታምን ሌሎች ነገሮችንም እየነገረህ እግዚአብሔር የገለጠልኝ ነው ብለህ እንድታስብ ያሳምንሃል፡፡ በትዕቢትና ራስን እንደ ጻድቅ  በማየት ኃጢአትም እንድትሞላ ያደርግሃል፡፡

ዮሐንስ ክሊማከስ ደግሞ እንዲህ ሲል ገልጾታል፡፡ ዲያቢሎስ ሐሳቦችን በአንድ ሰው ኅሊና ላይ ከተከለ በኋላ ይህንኑ ሐሳብ ለሌላ ሰው በመንገር ራሱን የሰውን አእምሮ የሚያነብ እንደሆነ እንዲሰማው ያደርገዋል፡፡ ጠንቋዮች የሚያውቁትን ነገር ከየት የሚያገኙት ይመስላኋል? ከዲያቢሎስ እኮ ነው! በእርግጥም አብዛኞቹ ጠንቋዮች በትክክል በአጋንንት የተያዙ ናቸው፡፡

ሦስት መነኮሳት አንድ ነገር ተገልጦላቸው የተገለጠው ነገር ከእግዚአብሔር ነው ወይንስ ከዲያቢሎስ እያሉ ይከራከሩ ነበር፡፡ በመጨረሻም ወደ ቅዱስ እንጦንስ ሔደው ሊጠይቁት ወሰኑ፡፡ ወደ ቅዱስ እንጦንስ ሲሔዱ በመንገድ ላይ ይዘውት ሲሔዱ የነበረ አህያ ሞተባቸው፡፡ መንገዳቸውን ቀጥለው ወደ ቅዱስ እንጦንስ ሲደርሱ ‹‹አህያችሁ መሞቱ በጣም ያሳዝናል!›› አላቸው፡፡ እነርሱም ‹‹ስለ አህያው እንዴት ልታውቅ ቻልህ?›› ሲሉ ጠየቁት፡፡ እርሱም ‹‹ሰይጣን ነገረኝ!›› አላቸው፡፡ እነርሱም ‹‹ሳንጠይቅህ ጥያቄያችንን መለስህልን!›› አሉት፡፡

አንዳንድ ሰዎች መላክትንና ቅዱሳንን በራእይ ያያሉ፡፡ ነገር ግን እንዲህ ያሉትን ራእዮች ከመቀበል በፊት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልጋል ፤ ምክንያቱም ዲያቢሎስ መንፈሳዊ ሕይወታችንን ለማፈራረስ ሲል ሊያስመስል ይችላል፡፡ የበረሃ አባቶች ታሪክ

ራእይና ሕልምን ከእግዚአብሔር መሆኑንና ከሰይጣን መሆኑን ሳይለዩ ስለተቀበሉ ሰዎች በሚናገሩ አስፈሪ ታሪኮች የተሞላ ነው። ከእነዚህ ታሪኮች አንዱ የሄሮን ታሪክ ነው። ይህ መነኩሴ ለሃምሳ ዓመታት በብሕትውና የኖረ ሲሆን ለረዥም ጊዜ ይገለጥለት በነበረ የሐሰት መልአክ እየወደቀ የመጣ ነው። መልአክ ስለተገለጠለት ወደ ቤተ ክርስቲያን መሔድ አቆመ ፣ ለአበምኔቱ እንዲነግራቸው ሌሎች መነኮሳት የመከሩትንም ምክር አልተቀበለም። በመጨረሻም ‹‹መልአኩ›› ለዚህ አባት በሕይወቱ እያለ እንደ ኤልያስ ወደ ሰማይ እንደሚወሰድ ነገረው። ይህ ምስኪን መነኩሴም ወንድሞቹ መነኮሳትን ሊሰናበት ሔደ። ነገሩ ከዲያቢሎስ ቢሉትም አልሰማቸውም። መልአክ ነኝ ባዩም ይህንን አባት ወደ ተራራ ይዞት ወጣ። እንዲዘልልም ነገረው ፤ ይህ አባትም በተባለው አምኖ ሲዘልል ወድቆ ተከስክሶ ሞተ። አበምኔቱ ይህ መነኩሴ ራሱን እንዳጠፋ በመቁጠር ጸሎተ ፍትሐት እንዲደረግለት እንኳን አልፈቀደም።

ሌላ መልአክ ነኝ ባይ ደግሞ ለሌላ መነኩሴ ለሦስት ዓመታት ተገለጠለት። በዚህ መልአክ ብርሃን ይህ አባት የሚኖርባት በአቱ ታበራ ነበርና ሻማዎችን ማብራት አያስፈልገውም ነበር። ከሦስት ዓመታት በኋላ ይህ በራእይ በ‹‹ገነት›› አይሁዳውያን በአብርሃም እቅፍ ሆነው ክርስቲያኖች ደግሞ በሲኦል ሲሰቃዩ አስመስሎ አሳየው። ይህ መነኩሴ ክርስትናን ትቶ አይሁዳዊ ሆነ።

ጥበበኛ የሆኑ መነኮሳትም አሉ። ለአንዱ መነኩሴ ‹‹ገብርኤል›› ነኝ ባይ ጋኔን ከእግዚአብሔር ተልኬ መጣሁ አለው።

መነኩሴውም ‹‹የመጣኸው ወደ ትክክለኛው በአት አይደለም ፤ እኔ ገና ራእይ ለማየት የማይገባኝ ኃጢአተኛ ነኝ! ከዚህ ቀጥሎ ያለው መነኩሴ ግን ጻድቅ ሰው ነው›› ሲል መለሰለት፡፡ ገብርኤል ነኝ ባዩም እንደ ጢስ ተነነ!

ለሌላ አባት ደግሞ ዲያቢሎስ ‹ክርስቶስ ነኝ› ብሎ ተገለጠለትና የአምልኮት ስግደት እንዲያቀርብለት ነገረው፡፡ ይህ አባት ግን ‹‹እኔ ክርስቶስን በሰማይ እንጂ በምድር ላይ ለማየት አልፈልግም!›› አለው፡፡ ይህም ክርስቶስ ነኝ ባይ እንደ ጢስ ተንኖ ጠፋ፡፡

እነዚህ ነገሮች ከዘመናት በፊት በመነኮሳት ላይ የተፈጸሙ ናቸው፡፡ ነገር ግን ዲያቢሎስ ዛሬም ይህንኑ ስልት እየተጠቀመ እና እየተሳካለት ነው፡፡

ከዓመታት በፊት ነው ፤ አንድ አገልጋይ ወደ ቤተ ክርስቲያን መምጣት እንዳቆመና ለረዥም ጊዜም ሥጋ ወደሙ መቀበል እንደተወ ተረዳሁ፡፡ መጠየቅ እንደሚገባኝ በማመን ወደ እርሱ ሔጄ ምክንያቱን ልጠይቀው ሞከርሁ፡፡ ቀለል አድርጎ መለሰልኝ ፡- ‹‹እሑድ እሑድ አቡነ ቁርሎስ ይገለጡልኛል ፤ ሥጋ ወደሙም ያቀብሉኛል!››

ከሌላ ቦታ የመጣ አንድ አገልጋይ ደግሞ ወደ እኔ መጥቶ ኅሊናውን የሚረብሸው ነገር እንዳለ ነገረኝ፡፡ እኔም የንስሐ አባቱ ባለመሆኔ የንስሐ አባቱን እንዲያናግርና እንዲናዘዝ መከርሁት፡፡ በማግሥቱ ጠዋት መጥቶ ጠራኝና በሕልሙ ‹‹አቡነ ቁርሎስ›› መጥተው ተናዘዝ እንዳሉትና ጸሎተ ንስሐ እንዳደረጉለት ነገረኝ፡፡

ከዚያም ይህ ይበቃው እንደሆነ ጠየቀኝ ፤ እኔ ግን አሁንም ወደ ንስሐ አባቱ ሔዶ እንዲናዘዝና ስላየው ሕልምም እንዲነግራቸው ነገርሁት።

ትክክለኛ ገንዘብ አለ ፤ የሐሰት ገንዘብ ደግሞ አለ። እንዲሁም እውነተኛ መገለጥ አለ ፣ የሐሰትም መገለጥ አለ። ሕልሞችን ፣ ራእዮችና መገለጦችን ለማስተናገድ ትክክለኛው መንገድ የንስሐ አባትን ማማከር ነው።

መንፈሳዊ ሰው ሁልጊዜም ራሱን ሕልም ራእይ ለማየት የማይገባው አድርጎ ማየት ይገባዋል። በተለይ ሕልሞች በዲያቢሎስ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ናቸው ማለት ይቀላል። እግዚአብሔር ለአንዳንድ ሰዎች ጋር በሕልም ተናግሯል። ሆኖም እነዚህ በጣት የሚቆጠሩ ሲሆኑ እነርሱም ነቢያትና ቅዱሳን ነበሩ እንጂ እንደ እኛ ኃጢአተኞች አልነበሩም። ለሕልሞችም ይህን ያህል ክብደት መስጠት የለብንም። አንድ ጊዜ ቅዱስ እንጦንስ እንዲህ ብሏል፡- ‹‹በሕልሞች የሚያምን የዲያቢሎስ መጫወቻ ነው።››

### ፯. የሐሰት ጸጋዎች

ወደ መጨረሻ ዲያቢሎስ እንደ መፈወስ ያሉ ‹‹መንፈሳዊ ጸጋዎችን›› ሊሠጥህ ይችላል። ወይም ደግሞ ሰዎች ጸልይልን እንዲሉህና ችግራቸውም ወዲያው እንዲፈታ ሊያደርግ ይችላል። ለምሳሌ ዲያቢሎስ አንድን ሰው ራስ ምታት እንዲያመው ያደርጋል። ከዚያም አንተ እንደጸለይህለት ራስ ምታቱ እንዲለቅቀው ያደርጋል። ወይም ደግሞ አንድ ሰው ችግር እንዲገጥመው ያደርግና አንተ ስትጸልይለት ችግሩ እንዲፈታ ያደርጋል።

ለዚህ ዓይነቱ ማታለያ ምሳሌ የሚሆነን በቅዱስ ጳኩሚስ ሕይወት ላይ ተቀምጦልናል፡፡ ከአባ ጳኩሚስ ጋር አብሮ የቅዱስ ጵላሞን ረድእ የነበረ መነኩሴ ነበር፡፡ ይህ መነኩሴ ቅዱስ ጳኩሚስ ትጋት እንደሚጎድለው ይነግረው ነበር፡፡ ይህንንም ለማስረዳት ይህ መነኩሴ በእሳት ፍሕም ላይ ሳይፈራ ይራመድ ነበር፡፡ ቅዱስ ጳኩሚስ ይህንን ለማድረግ ባለመቻሉ ምክንያት ያዝን ነበር፡፡ አንድ ቀን ይህ መነኩሴ ወደ አባ ጳኩሚስ መጣና እንዲህ አለው ‹‹ዛሬ ወደ እሳት ነበልባል ውስጥ እዘልላለሁ ፤ ምንም ሳልሆንም እወጣለሁ!›› አለው፡፡ እንዳለውም ይህ መነኩሴ ወደ እሳት ዘለሎ ገባ ነገር ግን በእሳቱ ተቃጥሎ ሞተ፡፡

ቅዱስ ጳኩሚስ ባየው ነገር በጣም ደነገጠ ወደ በረሃም ሔዶ መጸለይም ጀመረ፡፡ እግዚአብሔርንም ‹‹ይህ ነገር ግራ አጋብቶኛል!›› ሲል ጠየቀ፡፡ እግዚአብሔር ግን መልአኩን ልኮ እንዲህ ሲል ነገረው፡፡ ስለ ትሕትናህ ምክንያት እግዚአብሔር ይህንን መለየት እንድትችል ሰጥቶሃል፡፡ ስለዚህም ዲያቢሎስ በዚህ መንገድ አያታልልህም፡፡ ሌሎችን ለመርዳት የምትችል ትሆናለህ ፤ ብዙ ደቀ መዛሙርትንም ታፈራለህ፡፡››

በየቴሌቪዥን ጣቢያዎች የሚታዩት ‹‹ፈዋሾች›› ጸጋቸውን ከየት የሚያገኙት ይመስላችኋል? ከዲያቢሎስ እኮ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ዲያቢሎስ ሕመምን ሊያመጣ እንደሚችል ይነግረናል፡፡ ጌታችን የፈወሳቸው ዓይነ ስውራን ፣ መስማት የተሳናቸው ፣ የሚጥላቸው እና ሌሎችም በሽታዎች በዲያቢሎስ ምክንያት የመጡ ነበሩ፡፡ በመጽሐፈ ኢዮብ ‹‹ሰይጣንም ከእግዚአብሔር ፊት ወጣ፥

ኢዮብንም ከእግሩ ጫማ ጀምሮ እስከ አናቱ ድረስ በክፉ ቍስል መታው።›› ተብሎ ተነግሮናል።

ሰይጣን አንድን ሰው ለተወሰነ ጊዜ ዐይኑን ሊያሳውረው ይችላል። ከዚያው ፈዋሽ ነኝ ባዩ ሰው ‹‹እንዲፈውሰው›› ያደርጋል! ለምንድር ነው እንዲህ የሚያደርገው? ፈዋሹም ተፈዋሹም እንዲሁም ተመልካቾች በዚህ የሐሰት ተአምር ይታለላሉ።

## ፰. የሐሰት ጸጸትና የሐሰት ዕንባ

አንዳንድ ጊዜ ዲያቢሎስ በስኅተትህ እንድትቀጥል ለማድረግ የሐሰት የሆነ የልብ መቃጠልን እና ሌላው ቀርቶ በምትጸልይበት ጊዜ የሐሰት ዕንባ ከዓይንህ እንዲወርድ ያደርጋል። ይህን ማድረግ ለእርሱ በጣም ቀላል ነው። እንድትታለልና መልካም ነገር እያደረግህ እንደሆነ እንዲሰማህ ለማድረግ አጋንንቱን በጸሎትህ ጊዜ እንዳይረብሹህና እንዳይፈትኑህ ያዝዛቸዋል።

ይህንን እንዴት እንደሚፈጽመው የሚያሳይ ጥሩ ምሳሌ አለ። ከብዙ ዓመታት በፊት አብረው በኃጢአት የሚኖሩ ሁለት ወጣቶችን አገኘሁ። ሁልጊዜ የሚነግሩኝ ግን አንድ ዓይነት ነገር ነበር። ‹‹አባ አብረን ጸሎት እናደርጋለን ፣ መጽሐፍ ቅዱስም አብረን እናነብባለን ፣ ታዲያ ይህ እንዴት ኃጢአት ሊሆን ይችላል?››

‹‹ትክክል መሰሎ ከተሰማህ ስኅተት ሊሆን አይችልም!›› የሚል አንድ የድሮ ዘፈን ነበር። ይህንን ዘፈን ስሰማ ‹‹ይህንን ዘፈን የደረሰው ራሱ ዲያቢሎስ ሳይሆን አይቀርም!›› ብዬ አሰባለሁ።

## ፱. ከመታወክ በፊት የሚገኝ ሰላም

ይህ ደግሞ ዲያቢሎስ ወጣቶችን በኃጢአት ለመጣል የሚጠቀምበት ሌላው ዘዴ ነው፡፡ እንደሚከተለው ያለ ነው፡፡ አንድ ወጣት ከአንዲት ልጅ ጋር ይተዋወቃል፡፡ ከዚያም ቤተሰቦቻቸው ሳያውቁ መገናኘት ይጀምራሉ፡፡ ይህንን መቀራረባቸውን ለንስሐ አባታቸው ለመናገር ስለሚፈሩም በኑዛዜ ጊዜ ስለዚህ ጉዳይ ምንም ነገር አያነሡም፡፡ ዲያቢሎስም በጆሮአቸው ‹‹ይሔ እኮ ንጹሕ ጓደኝነት ነው!›› እያለ ያንሾካሹክላቸዋል፡፡ ሌላ የፍትወት ሃሳብ ሳይቀሰቅስባቸውም ረዥም ሰዓታትን አብረው ያሳልፋሉ፡፡ ምንም አይነት መነካካትና አካላዊ ቅርበት አይኖራቸውም፡፡ (ምክንያቱም ዲያቢሎስ አጋንንቱን ‹አትፈትኗቸው› ብሎ ነግሮአቸዋል፡፡) ከዚህ የተነሣ የተሳሳተ የደህንነትና በራሳቸው የመተማመን ስሜት ያድርባቸዋል፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ ለብቻቸው ቢገናኙም እንኳን ቅድስናቸውን የሚያሳድፍ ምንም ዓይነት ድርጊት አይፈጽሙም፡፡ (ይህም በዲያቢሎስ የተጻፈ ተውኔት ስለሆነ ነው፡፡)

አንድ ቀን በአንድ ላይ ባለፉት ወራት እንዳደረጉት በአንድ ሶፋ ላይ አብረው ሲሆኑ ዲያቢሎስና ሠራዊቱ በድንገት ከየአቅጣጫው ፈተናን ያመጡባቸዋል፡፡ የፍትወት ፍላጎትም ይቀጣጠልባቸዋል፡፡ ፈጽሞ ባልጠበቁት ሁኔታ በኃጢአት ይወድቃሉ፡፡

## ፲. የተቃራኒ ሐሳቦች ውጊያ

ይህ ደግሞ ዲያቢሎስ መንፈሳዊነታችንን ለማዳከምና በቀላሉ ግዳይ ሊጥለን ሲፈልግ የሚሠራው ተንኮል ነው፡፡ በአእምሮአችን

ሁለት የሚቃረኑ ሐሳቦችን ያስነሣል፡፡ ሁለቱም ሐሳቦች መልካም ሐሳቦች ናቸው፡፡ ነገር ግን ያለማቋረጥ በአእምሮአችን ውስጥ ይፈራረቃሉ፡፡ ሁለቱም ሐሳቦቻችን የየራሳቸው አሳማኝነት ያላቸውና ተገቢ በሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተደገፉ ናቸው፡፡ የትኛው ሐሳብ ከፈጣሪ ዘንድ እንደሆነና የትኛው ደግሞ እንዳልሆነ ለመመርመር ስንጣጣር ብዙ ርቀት እንጓዛለን፡፡

እውነታው ግን ሁለቱም ሐሳቦች ከዲያቢሎስ መሆናቸው ነው፡፡ ይህንን የሚያደርገው ግን ፍሬቢስ ለሆኑ ነገሮች ትኩረት በመስጠት እንድንዳከምና በቀላሉ ለጥቃት እንድንጋለጥ ብሎ ነው፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ማመንታት ግን መፍትሔው የንስሐ አባትን ማማከር ነው፡፡

## ፲፩. የመንፈሳዊ እድገት ውጊያ

ዲያቢሎስ በመንፈሳዊ ሕይወት ለማደግ ከመጠን ያለፈ ጉጉት እንዲያድርብህ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በአእምሮህም ‹‹ምንም ዓይነት እድገት እያሳየህ አይደለም! የንስሐ አባት ብትለውጥ ይሻልሃል!!›› እያለ ሊያንሾካሹክ ይችላል፡፡

ሁላችንም አንድ የማናውቀው ነገር ግን አለ ፤ እግዚአብሔር የመንፈሳዊ ተጋድሎአችንን ፍሬ እስከ መጨረሻዋ የሕውታችን ፍጻሜ ድረስ ይደብቅብናል፡፡ ይህንን የሚያደርገው ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ነው፡፡ የትጋታችንን ውጤቶች ካየን ወዲያውኑ ይህንን ፍሬ ያገኘነው በእግዚአብሔር ቸርነት ሳይሆን በእኛ ቅድስና እንደሆነ እናስባለን፡፡ ከዚህም የተነሣ በተጋድሎ ያገኘነውን ሁሉ በትዕቢትና ራስን ጻድቅ አድርጎ በመመልከት እናጣዋለን፡፡

እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲያመጣቸው እንዲህ ብሎአቸው ነበር ፡- ‹‹አምላክህም እግዚአብሔር እነዚህን አሕዛብ በጥቂት በጥቂቱ ከፊትህ ያወጣቸዋል የምድረ በዳ አራዊት እንዳይበዙብህ አንድ ጊዜ ታጠፋቸው ዘንድ አይገባህም፡፡›› (ዘዳ.፯÷፳፪) አባቶቻችን ይህንን ሲያብራሩ ‹አሕዛብ› የኃጢአቶቻችን ምሳሌ ናቸው ይላሉ፡፡ እግዚአብሔር ኃጢአቶቻችንን በአንድ ጊዜ እንዲወገዱ አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም የምድረ በዳ አራዊት የተባሉ ትዕቢትና በራስ መመካት ይበዙብንና ይውጡናል፡፡

የትጋታችንን ውጤት ለማየት መጠበቅ እንደሌለብን የሚያስረዳ ሌላ ምሳሌም ጌታችን ነግሮናል፡፡ ‹‹እርሱም አለ፦ በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ናት ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም፥ እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማል፡፡›› (ማር.፬÷፳፮) በቤትህ ውስጥ አትክልት ከተከልህ በየዕለቱ ያድጋል፡፡ ሲያድግ ግን ልታይ ትችላለህ? በመንፈሳዊ ሕይወትህም እንዲሁ ነው ፤ ውጤትን ለማየት አትጠብቅ ምክንያቱም እግዚአብሔር ለጥቅማችን ሲል ዕድገታችንን ይሰውረዋል፡፡

## ፲፪. ተጨማሪ ኃጢአቶች

አባቶቻችን ዲያቢሎስ ሊዋጋን ሲመጣ በቀኝ እጁና በግራ እጁ ሁለት ረዳት አጋንንትን ይዞ ይመጣል ይላሉ፡፡ በቀኝ እጁ ይዞት የሚመጣው የሚያስታብይ ሰይጣን (ሰይጣነ ትዕቢት) ይባላል፡፡ በስተግራው የሚይዘው ደግሞ ተስፋ የሚያስቆርጥ ሰይጣን (ሰይጣነ ቀቢጸ ተስፋ) ይባላል፡፡

ዋናው ሰይጣን ፈትኖ በኃጢአት ከጣለህ ተስፋ የሚያስቆርጠው ሰይጣን ይረከብሃል፡፡ የመዳን ተስፋህ እንዲሟጠጥ እና ተስፋ እንድትቆርጥ በሚያስደነግጥ ሁኔታ ይወቅስሃል፡፡ ይህን ጊዜ ደጋግመህ በመውደቅህ ምክንያት እየወቀሰህ ያለው ኅሊናህ ወይም ፈጣሪህ ይመስልሃል ፤ ነገር ግን ታሳስተሃል፡፡ አባቶቻችን እግዚአብሔር በእርጋታና በፍቅር እንጂ በማስጨነቅ አይገሥጽም ሲሉ ተናግረዋልና፡፡

ፈተናውና ድል ካደረግህ ደግሞ የትዕቢት ሰይጣን በራስ የመመካትና የጻድቅነትን ስሜት በአእምሮህ ማመላለስ ይጀምራል፡፡ ‹‹በእውነቱ ከሆነ ይህንን ኃጢአት በመዋጋትኮ ልምድ እያካበትህ ነው!!›› ወይም ይህን የመሳሰለውን ነገር እየነገረ በእግዚአብሔር ቸርነት ያገኘሽውን ድል እንድታጣ ያደርግሃል፡፡

ተስፋ አስቆራጩ ሰይጣን አንዳንድ ጊዜ ሥጋ ወደሙ ለመቀበል በተሰለፍንበት ጊዜ እንኳን በአእምሮአችን እግዚአብሔርን እንድንሰድብ ወይም የዝሙት ሐሳብ እንድናስብ ሊያደርገን ይችላል፡፡ ከዚያም በድኅነታችን ተስፋ እንድንቆርጥ ለማድረግ ይገሥጸናል ፤ ይወቅሰናል፡፡

አንድ መነኩሴ በአእምሮው እግዚአብሔርን የመሳደብ ሐሳብ በተደጋጋሚ እየተዋጋው ስለነበር ተጨንቆ ወደ አበምኔቱ ሔደ፡፡ አበምኔቱ ግን እነዚህን ሐሳቦች ንቆ እንዲተዋቸውና ‹‹እነዚህ ሐሳቦች የራስህ ሐሳቦች ናቸው እንጂ የእኔ ሐሳቦች አይደሉም ፤ ስድብህም በገዛ ራስህ ላይ ይሁን!›› ብሎ ዲያቢሎስን እንዲቃወም ነገሩት፡፡

የእነዚህ ፈተናዎች መፍትሔው ፈተናዎቹን ለይቶ ማወቅ ፣ መግለጥና መዋጋት ነው። ወደ ንስሐ አባትህ ሒድና እነዚህን ሐሳቦችህን ሁሉ ገልጠህ ንገራቸው። ለንስሐ አባትህ እንደተናገርህ እነዚህ ክፉ ሐሳቦች ሁሉ ተንነው ይጠፋሉ ይላሉ አባቶች።

### ምዕራፍ ስድስት

# ጽድቅን መከተል

ጽድቅ እያንዳንዱ ሰው ወደ ክርስቲያናዊ ፍጹምነት በሚያደርገው ጉዞ ሊያፈራው የሚገባ ፍሬ ነው፡፡ ‹‹መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል ወደ እሳትም ይጣላል፡፡›› (ማቴ. ፫÷፲) ጌታችን ስለ እነዚህ ፍሬዎች ጥቅም የነገረንም ይህንኑ ነው፡፡ ከመቀጠላችንም በፊት ጌታችን የነገረንን ተጨማሪ ነገር እንስማ ፡- ‹‹በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ፡፡ ቅርንጫፍ በወይኑ ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም፡፡ እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ፡፡ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፡፡›› (ዮሐ. ፭÷፬–፭)

እናም ፍሬን ለማፍራት የመጀመሪያው መመሪያ ይህ ነው፡፡ ‹‹ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም፡፡›› ማንም ሰው በራሱ ጥረት ብቻ ሊያፈራ አይችልም፡፡ ፍሬያማዎች የሚያደርገን እርሱ እግዚአብሔር ነው፡፡

እግዚአብሔር መሬት እንዳለውና መሬቱን እንዲንከባከቡ አገልጋዮችን እንደቀጠረ ገበሬ ነው፡፡ መሬቱና ዘሩ የእግዚአብሔር ነው ፤ ማዳበሪያውም እንዲሁ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለእርሻ የሚያስፈልገውን ዝናምና ፀሐይም ያዘጋጃል፡፡ የተቀጠረው አገልጋይ ደግሞ በሚገባ ማረስ ፣ ዘርን መዝራት ፣ አረምን ማረም ፣

ማዳበሪያን ማድረግና የድካሙን ዋጋ ማጨድ ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን የቅጥረኛው ሠራተኛ ሥራውን ከመሥራት በስተቀር በሠራው ነገር ላይ መብት የለውም፡፡ በእኛም እንዲሁ ነው ‹‹እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፡፡ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ፡፡›› እንዳለን ጌታችን፡፡ (ሉቃ. ፲፯÷፲)

ቅድስና እንዲሁ አይከሰትም፡፡ አንድ ሰው በተገቢው መንገድ ቅድስናን ለማግኘት መለማመድ አለበት፡፡ አንዳንድ ጊዜ በጎነት ከምድር እስከ ሰማይ በሚደርስና ብዙ ደረጃዎች ባለው መሰላል ይመሰላል፡፡ አንዳንድ በጎነቶች በመሰላሉ ከሥር ሲገኙ ሌሎች ደግሞ ከመሰላሉ ጫፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ አባቶች እነዚህን መሰላሎች ዘልለን ልናልፋቸው አንችልም ነገር ግን ደረጃ በደረጃ ልንወጣቸው ይገባናል ይላሉ፡፡

በታችኛው የመሰላሉ መውጫ ላይ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ የጽድቅ ሥራዎች አሉ፡፡ እነዚህም መታዘዝና ትዕግሥት ናቸው፡፡ በመሰላሉ የላይኛው ጫፍ ላይ ደግሞ ትሕትናና ፍቅር አሉ፡፡ ፍቅር ከሁሉም የበጎነት ደረጃዎች ከፍተኛው ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ‹ሁሉን የሚያጠቃልል በጎነት› ተብሎ ይጠራል፡፡ ፍቅር ያለው ሁሉም በጎነቶች ይኖሩታል፡፡

በጎነትን ስንለማመድ አንድ በአንድ ልንለምዳቸው እንደሚገባን ይመከራል፡፡ አንዱን የበጎነት ደረጃ ተለማምደን ስንጨርስ የመሰላሉን ቀጣይ ደረጃ ደግሞ እንወጣለን፡፡

በጎነት በየጊዜው እየዳበረ የሚሔድ ነገር ነው፡፡ አንዱን በጎነት መልመድ የሚቀጥለውን በጎነት በቀላሉ ለማግኘት ያስችላል፡፡ ለምሳሌ ራስህን ትዕግሥትንና መታዘዝን ካስለመድኸው የዋህነትም የአንተ ይሆናል፡፡ የዋህነትን ስትይዝ ደግሞ በትሕትና ደጃፍ ላይ ነህ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፡፡

አንድ ልምምድ አለማማጅ ወይም አሰልጣኝ ይፈልጋል፡፡ ማንም ሰው ያለ አሰልጣኝ በአትሌቲክስ ሊሳካለት አይችልም፡፡ እንዲሁም አንድ ክርስቲያን ያለ አሰልጣኝ ‹የክርስቶስ /መንፈሳዊ/ ሯጭ› ሊሆን አይችልም፡፡ አሰልጣኝህ ደግሞ የንስሐ አባትህ ናቸው፡፡ በልምምድህ ወቅትም ትእዛዝ ሊሰጡህ የሚገባው እርሳቸው ናቸው፡፡ ያለፈውን ምእራፍ አንብበኸውና ተረድተኸው ከሆነ በእርግጠኝነት ይህን ልምምድ በራስህ የማድረግህን አደጋ ትረዳዋለህ፡፡

ታዛዥነትና ትዕግሥት ሌሎች በጎነቶችን ለማግኘት እንደ ቅድመ ሁኔታ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ እነዚህን መሠረታዊ በጎነቶች ካልያዝህ ሌሎች የበጎነት ፍሬዎችን ልታፈራ አትችልም፡፡ የዚህም ምክንያቱ ታዛዥ ካልሆንህ በአሰልጣኝህ /በንስሐ አባትህ/ የሚሰጥህን ትእዛዝ ልትፈጽም አትችልም፡፡ በእርግጥም ምንም ዓይነት ዕድገት አይኖርህም፡፡ እንዲሁም ትዕግሥት ሳይኖርህ ልምምድህን በጽናት ለማካሔድና ፍሬ ለማፍራት አትችልም፡፡

በዘር ዘሪው ምሳሌ ላይ ጌታችን እንዲህ ሲል ነግሮናል ፦ ‹‹በመልካም መሬት ላይም የወደቀ እነርሱ በመልካምና በበጎ ልብ

ቃሉን ሰምተው የሚጠብቁት በመጽናትም ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው፡፡›› (ሉቃ. ፰÷፲፭)

በቀሪው የዚህ መጽሐፍ ክፍል ትዕግሥትንና ታዛዥነትን ልምምድን በተመለከተ አንዳንድ ተግባራዊ ‹‹ዘዴዎችን›› እንመለከታለን፡፡

## መታዘዝ

መታዘዝ የአንተን ፍላጎት ወይም ፈቃድ ለሌላው ፍላጎት ተገዢ ማድረግ ነው፡፡ አባቶች ይህንን ጠቃሚና መሠረታዊ የሆነ በጎነት ለጀማሪ ደቀመዛሙርቶቻቸው ለማስተማር ብዙ ታላላቅ መከራዎችን ተቀብለዋል፡፡ መቼም ሁላችንም ቅዱስ ዮሐንስ ኮሎቦስን (ሐጺርን) እናውቀዋለን፡፡ እሱን ያስተምሩት የነበሩት አባት ደረቅ እንጨት አምጥቶ እንዲተክለውና በየዕለቱ ውኃ እያመጣ እንዲተክለው አዝዘውት ነበር፡፡

ሌላ አባት ደግሞ ጀማሪ ተማሪያቸውን በገዳሙ ደጃፍ እንዲቆምና ወደ ገዳሙ የሚገቡትን ሰዎች ሁሉ በፊታቸው እየሰገደ ‹‹የሥጋ ደዌ ተጠቂ ነኝና ጸልዩልኝ!›› እንዲል አዘዙት፡፡ ይህ ምናልባት ለእኔና ለእናንተ ማላገጥ ሊመስለን ይችላል፡፡ ነገር ግን እነዚያ አባቶች እንዴት ባለ መንገድ ታዛዥነትን እንደሚለማመዱ የሚያሳይ ነው፡፡ እናም በሚከተሉት ስልት ላይ ውሳኔ ከማሳለፍህ በፊት እባክህን ወደሚያገኙት ውጤትና ወደሚያፈሩት ፍሬም ተመልከት፡፡ ዓመታትን ከፈጀ ደረቅ በትርን ውኃ ማጠጣት በኋላ እንጨቱ ለምልሞ አፈራ፡፡ እኚያም መምህር ፍሬውን ወደ ሌሎች መነኮሳት ወስደው ‹‹ኑ የመታዘዝን ፍሬ ብሉ!›› አሏቸው፡፡

እውነተኛ ታዛዥ ለመሆን ከፈለግህ የታዘዝኸው ነገር የሚስማማህ ነገር መሆን የለበትም፡፡ የታዘዝኸው ነገር ተቀባይነት የሌለው ነገር በሆነ መጠን በመታዘዝህ የበለጠ ዋጋ ታገኛለህ፡፡ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን ይስሐቅን ይሠዋለት ዘንድ ይስሐቅን በጠየቀው ጊዜ አብርሃም ስለታዘዘው ትእዛዝ ተገቢነት ለመጠየቅ ለአፍታ እንኳን ቆም ብሎ አላሰበም፡፡ የተባለው ብቻ አደረገ፡፡ አዎን እግዚአብሔር ልጁን እንዲያርድ አላደረገውም፡፡ እግዚአብሔር ለአብርሃም ይህንን ‹ተገቢ ያልሆነ› የሚመስል ትእዛዝ ያዘዘው ታዛዥነቱን ሊፈትን ነበር፡፡ ስለዚህም ስለዚህ ታዛዥነቱ በበረከት መትረፍረፍን ተሸልሟል፡፡

በተመሳሳይ ለምትወደው ወይም ለሚስማማህ ነገር ብትታዘዝ ነጥብ ልታስቆጥር አትችልም፡፡ የማትወድደውን ወይም የማይስማማህን ነገር ለማድረግ እሺ ስትል ግን ያን ጊዜ ነጥብ ልታስቆጥር ትችላለህ፡፡ ለምሳሌ አባትህ ‹‹ተነሥ ልብስህን ለባብስ! አንተ የምትወድደው ምግብ ቤት ራት ልጋብዝህ!›› ቢልህ እና ‹‹እሺ ጌታዬ!›› ብትል በዚህ የተነሣ ከእግዚአብሔር የታዛዥነትን ዋጋ ታገኛለህ ብዬ አላስብም፡፡ ነገር ግን አባትህ እንድትቆፍርና እንድታጭድ ወይም እናትህ ምግብ ሲያበስሉ እንድትረዳቸው ሲጠይቁህ ‹‹እሺ አባዬ!›› ‹‹እሺ እማዬ!›› ካልህ ያን ጊዜ ዋጋ ታገኛለህ፡፡

ሌላው የመታዘዝ ጠቃሚ መመዘኛ ነጥብ ‹‹በጌታ መሆኑ›› ነው፡፡ ‹‹ልጆች ሆይ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ ይህ የሚገባ ነውና!›› (ኤፌ. ፮፥፩) የምንፈጽመው ትእዛዝ ከመጽሐፍ ቅዱስ

አንጻር መመዘን አለበት ፤ ምክንያቱም ‹‹ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር መታዘዝ ይገባናል፡፡›› (ሐዋ. ፭÷፳፱)

## የመታዘዝ ልምምድ

ለንስሐ አባትህ ካማከርህ እንዲያነቃህና በተተጋድሎ እንዲያጸናህ ወደ እግዚአብሔር ልባዊ ጸሎት ካደረግህ አሁን ልምምድህን መጀመር ትችላለህ፡፡ በማለዳ ተነሣና እግዚአብሔር ይህንን ድንቅ የሆነ የጽድቅ ሥራ እንድትሠራ የሰጠህን ዕድሎች ሁሉ በማስታወስ ጀምር፡፡ ከዚያም ለወላጆችህ ፣ ለመምህርህ ፣ ለትዳር አጋርህ ወዘተ ታዛዥ ሆነህ ለመዋል ወስን፡፡ ለራስህም እንዲህ በል ‹‹ይህንን የማደርገው ስለ እግዚአብሔር ስል ነው እንጂ ስለሰዎቹ አይደለም፡፡›› አንድ ጊዜ ይህንን ውሳኔ ከወሰንህ በኋላ ያለማመንታት አድርገው፡፡ በመጀመሪያ ላይ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ በተለይ የምትወድደውን የቴሌቪዥን ዝግጅት እያየህ እያለ እናትህ ወይም አባትህ እንላክህ ሲሉህ! ይህንን ድንቅ የሆነ የመታዘዝ ሕይወት በነፍስህ ላይ ለመትከል ስትል ይህን ለማድረግ ራስህን አስገድድ፡፡

መላክህ ቢያማርርህ እንኳን ‹‹ወላጆቼ ለእነርሱ የታዘዝሁ ይመስላቸዋል፡፡ ይህን የማደርገው ለራሴ ስል እንደሆነ ግን አያውቁም፡፡›› ብለህ አስብ፡፡

መላላኩ የማይቀበሉት ዓይነት እየሆነ ከመጣ ደግሞ ለራስህ ‹‹ይህን የማደርገው ከእግዚአብሔር ዋጋ ለማግኘት ነው እንጂ ከቤተሰቦቼ አይደለም፡፡›› ብለህ ራስህን አጽናና፡፡

የታዘዝሁት ትእዛዝ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም እያልህ ራስህን አትጠይቅ፡፡ የመታዘዝን በጎነት እንድታገኝ ስትል ዝም ብለህ ፈጽመው፡፡ እንደ እውነታው ከሆነ የታዘዝኸው ትእዛዝ ተገቢ ባልሆነ መጠን በቶሎ የመታዘዝን ጸጋ ታገኛለህ፡፡ ‹‹የብሕትውና መንገዶች›› በተሰኘው መጽሐፍ ላይ ለዚህ የሚሆን ዓይነተኛ ምሳሌ እነሆ ፡-

ባለቤትህ ‹‹ዛሬ ሊዘንብ ስለሚችል ጃንጥላ ያዝ!›› ትልሃለች፡፡ ወደ ውጪ ስታይ ግን ፀሐይ ወጥቷል አንድም ደመና በሰማዩ ላይ አይታይም፡፡ ለራስህም ‹‹ምንም የሚዘንብበት ሁኔታ የለም፡፡›› ትላለህ፡፡ ደህና ልክ ልትሆን ትችላለህ ፤ ሆኖም ይህ ለመታዘዝ ብቻ ስትል መታዘዝን የምለማመድበት ዕድል ነው፡፡ እናም በእንዲህ ዓይነቱ ቀን ጃንጥላ በመያዝህ ሰዎች አተኩረው ካዩህ ለራስህ ‹‹ይህንን ለምን እንደማደርግ ምንም አያውቁም!›› ብለህ ሳቅ፡፡

መታዘዝ ማለት የታዘዝኸውን ነገር የማድረግ ችሎታህን ማሳደግ ማለት ነው፡፡ ወጣቶች ሲታዘዙ የሚመልሷቸው ሁለት ዓይነተኛ መልሶች አሉ፡፡ ‹‹እንደዚያ ማድረግ አለብኝ እንዴ?›› እና ‹‹እሺ ቆይ!›› የሚሉ፡፡ አዎን ይህ ቆይታ ለዘላለም ሊሆን ይችላል፡፡ የመታዘዝን በጎነት ለመለማመድ ቁርጠኛ ከሆንህ ራስህን ለማሳደግ ልታስገድደው ይገባል፡፡

ይህንን የሚያብራራልን ከሌሎች መነኮሳት ጋር በገዳም ይኖር የነበረው ‹ማርቆስ ጸሐፊው› የተባለው መነኩሴ ነው፡፡ የገዳሙ መነኮሳት ‹‹አበምኔቱ ከሌሎቻችን ይልቅ ማርቆስን ይወደዋል›› ብለው ለጳጳሱ ቅሬታ አቀረቡ፡፡ ጳጳሱ ነገሩን ለማጣራት

ወደ ገዳሙ መጡና አበምኔቱን ጠየቁት፡፡ አበምኔቱም ይምጡና ላሳይዎት አላቸው፡፡ አበምኔቱ የእያንዳንዳቸውን መነኮሳት የበአታቸው በር ማንኳኳት ጀመረ፡፡ ሁሉም ‹‹መጣሁ!›› በማለት ከደቂቃዎች በኂላ እንደሚከፍቱ አሳዩ፡፡ የማርቆስን በአት ሲያንኳኩ ግን ወዲያውኑ ተከፈተ፡፡ አበምኔቱ ጳጳሱን ይዞ ወደ ማርቆስ በአት ገባ፡፡ በበአቱ ውስጥ ማርቆስ መጽሐፉን እየጻፈ ነበር፡፡ በሩ ተንኳኩቶ ለመክፈት ሲመጣም የጀመረውን ቃል አናባቢ ፊደላት እንኳን ልጨርስ አላለም፡፡ ጳጳሱ ይህንን ሲያዩ ‹‹ለምን እንደወደድኸው የገባኝ ብቻ እንዳይመስልህ እኔም ወደድሁት!›› አሉ፡፡

እስከመቼ ይህን ላድርግ? በተገለጸው መንገድ ይህንን ልምምድ የማድረግ ልባዊ ፍላጎት ካለህ ይህንን ድንቅ የሆነ በጎነት ለነፍስህ ለማስተዋወቅ ምናልባትም ሁለት ሳምንታትን ቢወስድብህ ነው፡፡

## ትዕግሥት

የትዕግሥት ጥቅም በራሱ በጌታችን የተነገረን ነገር ነው፡፡ ከዳግም ምጽአቱ ፊት ስለሚመጣው ታላላቅ መከራ ጌታችን እንዲህ አለ ‹‹እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል፡፡›› (ማቴ. ፲÷፳፪) እንደገናም ፦ ‹‹በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ፡፡›› (ሉቃ. ፳፩÷፲፱)

ከምጽአቱ በፊት ስላሉት የመጨረሻዎቹ ቀናት ጌታችን ሲናገር ‹‹ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኝ

ይሆንን?›› ብሏል፡፡ (ሉቃ. ፲፰÷፰) እንደገናም አለ ‹‹ዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች፡፡›› (ማቴ. ፳፬÷፲፪) ይህም ማለት በእነዚያ የጥፋት ቀናት ፍቅርና እምነት ይዳከማል ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ‹‹እስከ መጨረሻው የሚጸና (የሚታገሥ) እርሱ ይድናል›› በትዕግሥትም ሰው ነፍሱን ማግኘት ይችላል፡፡ ምናልባትም ትዕግሥት ሰው በመጨረሻዎቹ ቀናት ራሱን የሚያድንበት የጽድቅ መንገድ ነው፡፡

ስለ መጨረሻዎቹ ዘመናት የሚነግረን የዮሐንስ ራእይ መጽሐፍም የእነዚያን ቀናት መከራ ለማለፍ የትዕግሥትን ጠቀሜታ አጽንዖት ሰጥቶ ይናገራል፡፡ ‹‹የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁት ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትዕግሥታቸው በዚህ ነው፡፡›› (ራእ. ፲፬÷፲፪)

ይህም ቢሆን ትዕግሥት የሚያስፈልገው ለመጨረሻው ቀን ብቻ አይደለም፡፡ ለዛሬው መንፈሳዊ ህልውናችን እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ‹‹የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋልና፡፡›› (ዕብ. ፲÷፴፮) ሌላው ቀርቶ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከፈጸምን በኋላ እንኳን የገባለልን ቃል እስኪፈጸም ድረስም መታገሥ ይገባናል፡፡ ‹‹እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ፡፡ እነሆ፥ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል፡፡›› (ያዕ. ፭÷፯) ትዕግሥት ወደ ፍጹምነት እንድንሔድና  መልካሙን ፍሬ ተስፋ በማድረግ እንድንጋደል የሚያደርገን ነው፡፡ እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ

‹‹በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ›› ብሎናል፡፡ (ዕብ. ፲፪÷፩)

## ታጋሽ ለመሆን የሚደረግ ልምምድ

እንደሌላው የጽድቅ ሥራ ሁሉ የንስሐ አባትህን ምክርና መመሪያ ጠይቅ፡፡ ከዚያም በየዕለቱ የሚሰጥህን ትዕግሥትን ለመለማመድ የሚረዱ አጋጣሚዎችን መጠቀም እንድትችል ይመራህ ዘንድ ወደ አምላክህ ጸልይ፡፡ ነገር ግን ‹‹እግዚአብሔር ሆይ እባክህ ትዕግሥትን ስጠኝ አሁኑኑ እፈልገዋለሁ!›› እንደሚል ሰው አትሁን፡፡

እግዚአብሔር ለእኛ ካለው ፍቅር የተነሣ ይህንን ጠቃሚ የሆነ ትዕግሥትን እንድንለምድና የእኛ እንድናደርግ ብዙ ዕድሎችን ይሰጠናል፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታ ግን እኛ ወደ አምላካችን ዘንበል ብለን አናውቅም ፤ ስለዚህም እነዚህን ዕድሎች አናውቃቸውም ፤ ብዙ ጊዜም ሳንጠቀምባቸው እናልፋለን፡፡

ለምሳሌ ሥራ ከፈታህ ሁለት ወር ሆኖሃል፡፡ በመቶ የሚቆጠሩ ቦታዎች የትምህርት ማስረጃህን አስገብሃል፡፡ ያለ ማቋረጥም እየጸለይህ ነው፤ ምን ዋጋ አለው አንድም መልስ እንኳ አላገኘህም፡፡ ፈጣሪን ማማረር ትጀምራለህ! ‹‹አምላኬ ለምን እንዲህ ያደርገኛል?›› ትላለህ፡፡ መልሱ ግን ይህ ነው ፤ እግዚአብሔር ትዕግሥትን የምትለማመድበት ወርቃማ ዕድል እየሰጠህ ነው፡፡ ለአንተ ወዲያውኑ ሥራ መስጠት ለእርሱ ቀላል ነገር ነው፡፡ ሆኖም በቅጽበት ሥራን ማግኘት ወደ መንግሥተ ሰማያት ሊመራህ

አይችልም ፤ ትዕግሥት ግን ይችላል። እናም እግዚአብሔር ትዕግሥትን የምትማርበትና ታጋሽ የምትሆንበትን ዕድል ሰጥቶሃል። እናም ታጋሽ መሆን እንደቻልህ ሥራውን ይሰጥሃል!

አብዛኛውን ጊዜ በችግር እንዘፈቅና እግዚአብሔር ለምን ይህን እንዳደረገ ለማወቅ እንዳክራለን። እግዚአብሔር በቸርነቱ ይህንን ችግር በእኛ ላይ እንዳመጣ ሳንረዳ በራሳችን መንገድ ለመፍታት እንራወጣለን። ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ፰፥፳፰ ላይ እንዲህ ይለናል ፦ ‹‹እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።›› ይህም ማለት እግዚአብሔርን የምንወድ ከሆንን በእኛ ላይ የሚሆነው ነገር ሁሉ ለእኛ ጥቅም ነው። አስተዋይ የሆነ ሰው አንድ የተለየ ነገር ሲያጋጥመው እግዚአብሔር ምን መልእክት እየነገረኝ ነው? የትኛውን የቅድስና ደረጃ ሊሰጠኝ ይሆን? ብሎ ራሱን ይጠይቃል።

ቅዱስ ጳውሎስ እንደገና በዕብራውያን ፲፪፥፲፩ ላይ ፦ ‹‹ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም፥ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።›› እዚህ ጋርስ ምን ማለት ይሆን? ምንም ችግሩ ደስታን የሚያመጣ ነገር ባይሆንም ትዕግሥትን መለማመጃ ካደረግነው ፍሬው ሰላምንና ደስታን ሊሰጠን ይችላል።

አንዲት እናት ‹‹ልጆቼ ሊያሳብዱኝ ነው!›› አለችኝ። እኔም ‹‹ዕድለኛ ነሽ! ልጆችሽ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራሽ በጎ ሥራ ትምህርት ቤት ናቸውና ስለ እነርሱ እግዚአብሔርን ልታመሰግኚ ይገባሻል!›› አልኳት።

መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ መከራዎች ትዕግሥትን ስለሚያስተምሩን ለእኛ ጠቃሚ እንደሆኑ ይነግረናል፡፡ ‹‹ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት ፤ ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም፡፡›› (ያዕ. ፩÷፫–፬) ይህም ማለት ፈተናዎችና መከራዎች በእኛ ውስጥ ትዕግሥትን ይፈጥራሉ ሆኖም ይህ የመታገሥ ተግባር ወደ ክርስቲያናዊ ፍጹምነት መዓርግ ከመድረሳችን በፊት (በመለማመድ) መፈጸም አለበት፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ ተመሳሳይ ሐሳብ ይነግረናል ‹‹ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን መከራ ትዕግሥትን እንዲያደርግ፥ ትዕግሥትም ፈተናን ፈተናም ተስፋን እንዲያደርግ እያወቅን፥ በመከራችን ደግሞ እንመካለን፡፡›› (ሮሜ ፭÷፫–፬)

ወደ እኛ የሚመጡት ፈተናዎች ሁሉ ለእኛ ጥቅም ናቸው የሚል ሃሳብ በኅሊናችን ካለ በፈተናዎቹ ውስጥ ትዕግሥትን መለማመድ እንችላለን ፤ ታጋሽነትን እንለምዳለን ፤ ይህንን መዳኛ የሚሆን በጎነትንም ለማግኘት አንቸገርም፡፡

መከራን ትዕግሥትን እንደመማሪያ ዕድል አድርጌ ከተረዳሁት የዚህን ዕድል ሙሉ አቅም ለመጠቀም ኅሊናዬን ማዘጋጀት ይኖርብኛል፡፡ ቅዱስ ያዕቆብ እንዳለው ‹‹ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም፡፡›› ማለት አለብኝ፡፡

ለሥራ ቃለ መጠይቅ ሳልጠራ ሁለት ወር ሲሆነኝ ለራሴ

‹‹ያለ ሥራ ሁለት ዓመት እንኳን ብቆይ ፍጹም ትዕግሥትን ለማግኘት ስል በጽናት እቋቋመዋለሁ፡፡›› ብዬ መወሰን አለብኝ፡፡ ራስህን እንዲህ በማለት አጽና ‹‹አምላኬ ይወደኛል! በሚጠፋው ፈንታ የማይጠፋውን ፣ በምድራዊው ፈንታ ሰማያዊውን ፣ በጊዜያዊው ፈንታ ዘላለማዊውን ሊሰጠኝ የወደደውም ለዚህ ነው፡፡››

እንዲህ በማለት ራስህን አበርታ ‹‹እስከ መጨረሻው ለመጽናት ልክ እንደወሰንሁ እግዚአብሔር ችግሬን ይፈታልኛል፡፡››

ከቅዱሳን አንዱ በአንድ ወቅት እንዲህ አለ ‹‹ራሱ መቅመስ አለበት እንጂ ለአንድ ሰው የማርን ጣዕም ልትገልጽለት አትችልም›› ይህም ማለት ይህንን ነገር ራስህ መሞከር አለብህ፡፡ የዚህን ልምምድ ጣፋጭ ውጤት ከማጣጣምህ በፊት በዚህ በጎ ሥራ በእምነት ራስህን ማለማመድ አለብህ፡፡ ውጤቶቹም ተገቢ በመሆናቸው ከአንተ ጋር ጸንተው ይቆያሉ፡፡ አንድ ጊዜ ይህንን ልምምድ በተገቢው መንገድ ከፈጸምህ ይህ የትዕግሥት ጠባይ እስከ ሕይወትህ ፍጻሜ ድረስ አብሮህ ይቆያል፡፡ እግዚአብሔር እንዴት በመከራህ ጊዜ የትዕግሥትን ጸጋ እንደሰጠህና ችግርህን እንዴት እንዳሳለፈልህ ያልጠየቅኸውንና ያልተመኘኸውንም እንደሰጠህ እያሰብህ የቀደመ ውሳኔህን ጣፋጭ ፍሬ እያስታወስህ ሌላ ቁርጠኛ ውሳኔዎችንም ትወስናለህ፡፡ እናም አሁን በጥሩ የትዕግሥት መሠረት ላይ ነህና ወደ ቀጣዩ ወደ ክርስቲያናዊ ፍጹምነት የሚያደርሰው መሰላል ደረጃ ለመውጣት ዝግጁ ነህ፡፡

### ምእራፍ ሰባት

# የዋህነት

የዋህነት ‹‹የመንፈስ ፍሬ ነው›› (ገላ. ፭÷፳፫) ጌታችን ራሱ ስለ የዋህነት እንዲህ ሲል አሳስቦናል ‹‹ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና፡፡›› (ማቴ. ፲፩÷፳፱–፴)

የጌታችንን የዋህነት እንዴት ልንመስለው እንችላለን? እስቲ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጌታችን ጠባይ የሚለውን እንመልከት ‹‹አይጮኽም ቃሉንም አያነሣም፥ ድምፁንም በሜዳ አያሰማም፡፡ የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም፥ የሚጤስንም ክር አያጠፋም በእውነት ፍርድን ያወጣል፡፡ ›› (ኢሳ. ፵፪÷፪–፫) ይህ እንግዲህ ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢታዊ መንገድ ጌታን የገለጸበት ነው፡፡ በዚህ የሚከሰትልን ምስል የጸጥተኛ ፣ በዝግታ የሚናገርና ከሌሎች ጋር በስምምነት የሚቀርብ ሰው ምስል ነው፡፡ በሌላ መንገድ ሲገለጽ ቁጣን ማብረድ የሚቻለው ማለት ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ፲፪÷፲፰ ላይ ፡- ‹‹ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ፡፡›› ሲል አሳስቦናል፡፡

ዛሬ ዛሬ በሁሉም የዕድሜ ክልል ባሉ ሰዎች ዘንድ ቁጣ ትልቅ ችግር ሆኗል፡፡ መኪና ስንነዳ በረራ ስናደርግ ወይም ያለ ምክንያት በንዴት እንጦፋለን፡፡ ፊልሞችና ቴሌቪዥን ፣

የኮምፒውተር ጨዋታዎችና ካርቱኖች ጭምር የሚመለከቷቸውን ሰዎች ለንዴትና ቁጣ ይገፋፋሉ፡፡ ‹ንዴትን መቆጣጠር› (“Anger Management”) የሚሉ ሥልጠናዎች ትልቅ የሥራ መስክ እየሆኑ መምጣታቸውም የሚደንቅ አይደለም፡፡

## የየዋህነት ደረጃዎች

የበረሃ አባቶች የየዋህነት ደረጃዎችን አስቀምጠውልናል፡፡ እነርሱ የየዋህነትን ደረጃዎች ጌታችን በዘር ዘሪው ምሳሌ ላይ ካስቀመጣቸው የፍሬያማነት ደረጃዎች ጋር ያመሳስሉታል፡፡ ‹‹ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ስድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ፡፡›› (ማቴ. ፲፫÷፰)

የመጀመሪያው ደረጃ ክፉን በክፉ አለመመለስ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ እንዲህ ብሎናል ‹‹ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ›› (ሮሜ ፲፪÷፲፯)

ቅዱስ ጴጥሮስም ተመሳሳይ ነገር ይነግረናል ‹‹ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩ እንጂ፥ በረከትን ልትወርሱ ለዚህ ተጠርታችኋልና፡፡›› (፩ጴጥ. ፫÷፱)

ጌታችን የዚህ ተግባር ፍጹም ምሳሌ ነው፡፡ ‹‹ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤›› (፩ጴጥ. ፪÷፳፫)

ሁለተኛው ደረጃ ውስጣዊ ሰላምህን ሳታጣ ስድብን መቀበል ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ክፉን በክፉ ከመመለስ ራሳቸውን ይገታሉ ነገር ግን በውስጣቸው በንዴት ይነፍራሉ፡፡ ውስጣቸው በቁጣ ሃሳብ

እና በበቀል ፍላጎት የተሞላ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ወደ ሁለተኛው የየዋህነት ደረጃ ያልደረሱ ናቸው፡፡ ይህ የየዋህነት ሁለተኛ ደረጃ ላይ መድረስ እንደሚቻል የሚያሳዩ ምሳሌዎችን ከበረሃ አባቶች መካከል እናገኛለን፡፡

ቅዱስ ዮሐንስ ኮሎቦስ (ሐጺር) እጅግ የገነነ አባት ስለነበር ሰዎች ሊሰሙት ወደ እርሱ ይመጡ ነበር፡፡ ሌላ መነኩሴ ደግሞ በዮሐንስ ሐጺር ክብርና ዝና ይቀናት ነበርና በእሱ ዙሪያ በተሰበሰቡ ሰዎች ፊት መጥቶ ‹‹ዮሐንስ በአፍቃሪዎቿ ፊት ገላዋን እንደምታሳይ ጋለሞታ ነህ!›› አለው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስም ‹‹ወንድሜ ከላይ ተመልክተሸኝ ይህንን ካልከኝ ውስጤን ብታይማ ምን ትለኝ ይሆን?› ብሎ መለሰለት፡፡ በዙሪያው የነበሩት ሰዎች በመሰደብህ ውስጥህ አልተረበሸም? አሉት፡፡ እሱም ‹‹ዮሐንስ ላዩ የተሰማው ነው በውስጡ የተሰማው›› አላቸው፡፡

ጥቂት የሶርያ መነኮሳት የግብፃውያንን መነኮሳት ዝና ሰምተው እንዴት እንደሚኖሩ ለማየት ወደ ግብፅ ገዳማት መጡ፡፡ ግብፃውያን መነኮሳት ደግሞ እንግዳ ሲመጣ የእነርሱን የምናኔ ኑሮ በሌላው ላይ ላለመጫን ሲሉ በጊዜ የመብላት ልማድ ነበራቸው፡፡ እናም ከሶርያ የመጡት እንግዶች ገበታ ሲቀርብላቸው በልባቸው ‹‹እነዚህ የግብፅ መነኮሳት ለካ ቸልተኞች ናቸው፡፡ እኛ እስከ ምሽት ድረስ እንጾማለን እነርሱ ግን ገና በሦስት ሰዓት ይበላሉ!!›› ብለው አጉረመረሙ፡፡ አበምኔቱ የሚያስቡትን በመረዳት ትምህርት ሊሰጣቸው ወሰነ፡፡ አንድ አረጋዊ መነኩሴ ዳቦ እያደለ በመካከላቸው ይዞር ነበር፡፡ እናም ወደ አበምኔቱ ደርሶ ዳቦ ሲሰጠው አበምኔቱ

ፊቱን በኃይል መታው፡፡ አረጋዊው መነኩሴ ከመመታቱ በፊት የነበረው የፊቱ ገጽታ ሳይቀየር ዳቡውን ማደል ቀጠለ፡፡ ሶርያውያኑ መነኮሳት ከአበምኔቱ እግር ሥር ተደፍተው ‹‹አባታችን ይቅር በለን! ረዥም ሰዓት ያለ ምግብ መቆየት እንችላለን ነገር ግን እናንተ እንደምታደርጉት ግን ስሜታችንን መግታት አንችልም፡፡›› አሉት፡፡

ሦስተኛው የየዋህነት ደረጃ ላይ ያለው ደግሞ ከተሰደበ በኋላ ‹‹ወንድሜን እኔን በመስደብ ኃጢአት ውስጥ ከተትኩት›› ብሎ ስለ ሰደበው ወንድሙ የሚያዝን ነው፡፡

## የዋህነትን መለማመድ

አሁንም ከንስሐ አባትህ ፈቃድ ካገኘህ በኋላ ወደ ጸሎትህ ተመለስ፡፡

ጌታ እንዴት እንደ እርሱ የዋህ መሆን እንደሚቻል ያስተምርህ ዘንድ ለምን፡፡ ‹‹ጌታዬ ከእኔ ተማሩ እኔ የዋህ ነኝና ብለሃል ፤ ይህንን የዋህነት ለእኔ አስተምረኝ ያን ጊዜም የነፍሴን ዕረፍት አገኛለሁ፡፡›› ብለህ ለምን፡፡

ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ በዚህ ጉዳይ ራስህን በዚህ መንገድ ማሳመን ነው፡፡ ሰላም ከእግዚአብሔር የተሰጠን ስጦታ ነው፡፡ እርሱም እንዲህ ብሎናል ‹‹ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤›› (ዮሐ. ፲፬÷፳፯) በተናደድክ ቁጥር ጌታችን ለአንተነትህ የሰጠህን ውድ ሥጦታ ሰላምህን እያጣህ ነው፡፡ ይህም የጌታችንን ሥጦታ ተቀብሎ እንደመወርወር ነው፡፡ እስቲ አስበው አንድ ጳጳስ ሥጦታ ቢሰጡህ ያንን ሥጦታ ጎዳና ላይ ትወረውረዋለህ? መልስህ ‹‹በፍጹም አልወረውረውም›› ከሆነ

በተቆጣህ ቁጥር እየወረወርኸው ያለው የክርስቶስ ስጦታ ምን ያህል ይበልጥ ይሆን?

ይህንን ጠባይ አንድ ጊዜ በአእምሮህ ውስጥ በሚገባ ካኖርኸው የሚከተለውን ባሕታዊው ቴዎፋን የሚመክርህን ልምምድ አድርግ፡- በማለዳ ጸሎት ካደረግህ በኋላ ሰላምህን ሊነሱህ የሚችሉትን ሁኔታዎች በሙሉ በአእምሮህ አስባቸው። ይመጣ ይሆናል የምትለውን የከፋ ነገር አስብና ‹ይህ እንኳን ቢከሰት የክርስቶስን ውድ ሥጦታ ወርውሮ ለመጣል የሚያበቃ ነው?› ብለህ ራስህን ጠይቅ። ቀደም ሲል ያየነውን ደረጃ በትክክል ተወጥተኸው ከሆነ መልስህ ‹‹በፍጹም አይደለም!›› የሚል ይሆናል። ከዚያም በአእምሮህ የተመላለሱትን ነገሮች ሁሉ መሆን እንደሌለባቸውና ሰላምህን ሊያሳጡህ እንደማይገባ ወስን።

ወዳጄ ልንገርህ ይህ አካሔድ በትክክል ይሠራል! ከዓመታት በፊት ይህንን ልምምድ ‹‹የማይታይ ውጊያ›› ከሚለው መጽሐፍ ላይ አንብቤ ልሞክረው ወሰንሁ። ውጤቱም እንደጠበቅሁት ሆነልኝ። ይህንን ልምምድ ለብዙ ምእመናን እንዲለማመዱት ነግሬያቸው ነበር። በሚገባ የሞከሩት ሰዎች በውጤቱ ተደንቀዋል።

ይህንን የየዋህነትና ንዴትን የመግታት ልምምድ በሚገባ የሞከረችና በእምነት የተገበረች የአራት ልጆች እናት ነበረች። በኋላ መጥታ ስትነግረኝ ልጆችዋ ‹‹እማዬ አሞሻል? ወይስ ምን ሆነሽ ነው?›› ብለው ይጠይቋት ጀመር። እርስዋ ግን አልታመመችም። ጌታችን ለእያንዳንዳችን የሰጠንንና አለመታደል ሆኖ እንደዋዛ እየወረወርነው ያለነውን የሰላም ሥጦታ እያጣጣመች ነው።

ይህ ሆኖ እያለ ውስጣዊ ሰላምን ማረጋገጥ የሚቻለው በቀጣዩ ደረጃ ላይ ሲደረስ ብቻ ነው፡፡ ‹‹ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤›› (ማቴ. ፭÷፵፬) ለሚያጠቁህና ለሚጠሉህ ሰዎች እንደመጸለይ ከክርስቶስ የሆነውን ሰላም የሚሰጥ ነገር የለም፡፡ እናም የተባልከውን አድርግ በትክክል ይሠራል፡፡ ይህንን በመንፈሳዊ ቅንዓት ካደረግህ ጌታችን በዚሁ ምእራፍ ላይ ወዳዘዘው ‹‹ጠላትን ወደ መውደድ›› ደረጃ ትደርሳለህ፡፡

ይህንን ተግሣጽ በቁም ነገር የሚቀበሉ ሰዎች ከእርሱ ማንም ሊወስደው የማይቻለውን የመጨረሻ ሰላም ያገኛሉ፡፡ ከብዙ ዓመታት በፊት በግብፅ በአንድ ትልቅ ድርጅት ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ሥልጣን የነበረው አንድ ወጣት አውቅ ነበር፡፡ ይህ ወጣት ኦርቶዶክሳዊ ነበረ፡፡ በግብፅ ደግሞ ክርስቲያን መሆን በተለይም በእንዲህ ዓይነት ተፈላጊ ሥልጣን ላይ ተቀምጦ ክርስቲያን መሆን ደህንነትን ለአደጋ የሚያጋልጥ ነበር፡፡

ይህ በግብፅ ጠረፍ አካባቢ ይሠራ የነበረ ወጣት ታዲያ እጅግ አክራሪ የነበረ (የድርጅቱ ምክትል ፕሬዚዳንት የሆነ) አለቃ ነበረው፡፡ ይህንን ወጣት አሽቀንጥሮ ጥሎ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ሰው በቦታው መተካትን የሕይወቱ ትልቅ ግብ አድርጎት ነበር፡፡ ለዓመት በሆነ ወንጀል ውስጥ ሊያስገባው ያሴር ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ባልታወቀ ምክንያት ፖሊስ እየመጣ ምርመራ ያደርግበት ነበር፡፡ አንድ ቀን (ክርስቲያን ያልሆነ) የፖሊሶቹ አዛዥ ‹‹በእውነት እዚህ አካባቢ አንድ ሰው ጠምዶ ይዞሃል!›› ብሎ ነገረው፡፡

ይህንን ወጣት ወህኒ ለማውረድ ያደረጋቸው ሙከራዎች አልሳካ ሲሉ አለቃው ሊገድለው ማሴር ጀመረ፡፡ ወጣቱ ኦርቶዶክሳዊ አንድ ሰው ሊገድለው ገንዘብ እንደተከፈለውና በጨለማ እንዳይወጣና እንዲጠነቀቅ ሩኅሩኅ የፖሊስ አዛዥ በእርግጠኝነት ነገረው፡፡

በዚህ ሁሉ ሥቃይ ውስጥ ወጣቱ ልጅ ይጸልይና መጽሐፍ ቅዱስ ያነብ ነበር፡፡ ሁልጊዜም መጽሐፍ ቅዱስን ሲገልጥ ማቴ. ፭÷፵፬ በፊቱ ያገኝ ነበር፡፡ እሱም ‹‹ጌታዬ በእርግጥ ሕይወቴን አሰቃቂ ላደረገውና ሊገድለኝ ለሚፈገው ለእዚህ ሰው እውነት እንድጸልይለት ትፈልጋለህ?›› ይል ነበር፡፡አሁንም አሁንም በልቡ የሚደውለው መልስ ግን ‹‹አዎ ጸልይለት!›› የሚል ነበር፡፡

ከሐሳቡ ጋር ሲጋጭ ከቆየ በኂላ በመጨረሻ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለውን በጭፍን ለመቀበል ወሰነ፡፡ እናም ለአለቃው መጸለይ ጀመረ፡፡ በመጀመሪያ ላይ የሚጸልይለት በከንፈሩ እንጂ በልቡ አልነበረም፡፡ ይህንን ልምምድ ሳያቋርጥ ሲሞክረው ግን አንዳች አስደናቂ ነገር መከሰት ጀመረ፡፡ ራሱንም ስለዚያ ሰው በእውነት ከልቡ ሲጸልይ አገኘው፡፡

በዚያ ሰው ላይ የነበረው የጥላቻ ስሜትም በኀዘኔታ ስሜት ተለወጠ፡፡ ስለራሱም ማሰብ ጀመረ ‹‹እኔ እኮ ክርስቲያን ሆኜ ባልወለድ ኖሮ ይህ ሰው የሚያደርገውን ላደርግ እችል ነበር፡፡›› ይል ጀመር፡፡ ጌታችን ለተናገረው ቃል አዲስ ትርጓሜ! ‹‹ከዚህ በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል፡፡›› (ዮሐ. ፲፮÷፪)

‹‹ይህ ምስኪን ሰው እኮ እኔን በማስቃየቱ የአምላክን ፈቃድ እየፈጸመ ይመስለዋል፡፡ ልክ ቤተ ክርስቲያንን በማጥፋት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘ እንደመሰለው እንደ ጠርሴሱ ጳውሎስ!›› እያለ ያዝንለት ጀመር፡፡ ወጣቱ ለራሱም እንዲህ ይላል፡- ‹‹የእርሱ እንድሆን ጌታ በምሕረቱ ብዛት ባይመርጠኝ ኖሮ ይህንን የማደርገው እኮ እኔ ነበርኩ!›› እግዚአብሔርንም አሳዳጅ በመሆን ፈንታ ተሳዳጅ ስላደረገው ያመሰግን ጀመር፡፡

ለአሳዳጁም መልካም ነገሮችን ማድረግ ጀመረ ፤ በቅን ልብም እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው ይጸልይለት ጀመረ፡፡

አንድ ቀን የድርጅቱ ፕሬዚዳንት ወጣቱን ወደ ቢሮው አስጠራውና ‹‹በአንተ ላይ እየደረሰ ያለውን ነገርና ምክትል ፕሬዚዳንቱ ሊጎዳህ እንደሚፈልግና ለምን እንዲህ እንደሚያደርግም ደርሼበታለሁ፡፡ እናም ላባርረው መሆኑን በመጀመሪያ ለአንተ ላሳውቅህ ፈልጌ ነው፡፡›› አለው፡፡ በዚህ ወጣት ልብ ውስጥ ግን ደስታ አልተፈጠረም፡፡ ከእንቅልፋቸው ሲነቁ አባታቸውን ሥራ አጥ ሆኖ ስለሚያገኙት ሕጻናት አዘነ እንጂ፡፡

አንተም ወዳጄ መጽሐፍ ቅዱስን በቁም ነገር ብትይዘውና እነዚህን ልምምዶች በደስታ ብትፈጽም የማይታወቅ የልብ ሰላም ይኖርሃል!

ምዕራፍ ስምንት

# ንጽሕና

እግዚአብሔር ጾታዊ ፍላጎትን ለምን በሰው ልጅ ላይ ፈጠረ? ለመባዛት ብቻ ይሆን? አቡነ ሙሴ በቆየ ኤልኬሬዛ ጎትም ላይ በጻፉት ጽሑፍ የሚከተለውን ጽፈዋል፡፡ በእንስሳት ዘንድ እግዚአብሔር ጾታዊ ፍላጎትን የፈጠረው የእንሳትን ዘር ለማቆየት ሲል ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ነው እንስሳት በዓመት ውስጥ ለጥቂት ቀናት ወይም ለጥቂት ሳምንታት ብቻ በጾታዊ ተራክቦ ንቁ የሚሆኑት፡፡ ይህ የተራክቦ ጊዜ ‹‹የግለት ጊዜ›› ተብሎ ይጠራል፡፡ በእነዚህ ወራት ሴቲቱ ወንዱን እንስሳ ለተራክቦ የሚጋብዝ አንዳች ድምጽ ፣ መዓዛ ወይም ምልክት ታሳያለች፡፡ እንስሳት በእነዚህ ወራት ብቻ ተራክቦን የሚፈጽሙ ሲሆን እነዚህ ወራት ካለፉ በኋላ ግን የጾታ ፍላጎት አይኖራቸውም፡፡ በሰዎች ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም ፤ [5]ከእንስሳት ወገን ሆነው ሳለ ሁልጊዜም ሙቀት የማይለያቸው ሰዎች ብቻ ናቸው፡፡ ይህ ለምን ሆነ?

አቡነ ሙሴ መልሱን ይሰጡናል፡፡ ይህ የሆነው እግዚአብሔር የሰው ልጅ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ፍቅር የሚመስልን የተቀደሰ ፍቅር እንዲያዩና ደስ እንዲሰኙ ስለወደደ ነው፡፡ ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን

---

[5] ሰው መልአካዊም እንስሳዊም ባሕርይ ስላለው፡፡ ሰው ከእንስሳት ወገን ተብሎ መጠራቱ እንግዳ ነገር አይደለም፡፡ ከአርባዕቱ እንስሳ አንዱ ገጸ ሰብእ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።›› ብሏል። (ኤፌ. ፭፥፴፪) ቅዱስ ጳውሎስ ምሥጢረ ተክሊልን በዚህ መልኩ ነው የሚገልጸው። ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው። ታላቅነቱም በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ትስስር ስለሚያንጸባርቅ ብቻ ነው። በቅዱስ ጋብቻ ውስጥ ሩካቤ የተቀደሰና ታላቅ እንደሆነ ሁሉ ከጋብቻ ውጪ ሲሆን ደግሞ የተወገዘ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ አክሎ ‹‹የወንድማማች መዋደድ ይኑር። እንግዶችን መቀበል አትርሱ፤ በዚህ አንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግድነት ተቀብለዋልና።›› ብሏል። (ዕብ. ፲፫፥፪) እንዲሁም ‹‹ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።›› (፩ቆሮ. ፮፥፲፰)

በጋብቻ ውስጥ የሚፈጸም ሩካቤ በክርስቶስና በሙሽራይቱ በቤተ ክርስቲያን መካከል ላለው ፍቅር ምሳሌ የሚሆን ሲሆን ከጋብቻ ውጪ የሚፈጸም ሩካቤ ደግሞ ከሌሎች ኃጢአቶች ሁሉ የተለየ ኃጢአት ነው። ምክንያቱም በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን ፍቅር በጎ ምስል የሚያሳድፍ ነው። ‹‹ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም።›› (፩ቆሮ. ፮፥፲፭)

ታላቁ ቅዱስ አትናቴዎስ በጋብቻ ውስጥ እና ከጋብቻ ውጪ የሚፈጸምን ሩካቤ አስመልክቶ አስደናቂ ንጽጽር አቅርቧል። እንዲህ ይለናል ፦ አንድ ወታደር ወደ ጦርነት ሔዶ ሃያ የጠላት ወታደሮችን ቢገድል የክብር ሜዳይ ይሸለማል። ነገር ግን በሰላም

ጊዜ ወደ ጎዳና ወጥቶ አንድ ሰው ቢገድል ይወገዛል፡፡ ድርጊቱ ተመሳሳይ ቢሆንም የተፈጸመበት ሁኔታ የተለያየ በመሆኑ ፍጹም ተቃራኒ የሆኑ ውጤቶችንም ያስከትላል፡፡

እግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያንን ፍቅር በዚህ ከመግለጹ በላይ የጋብቻ ፍቅር የተባረከ ለመሆኑ ሌላ ማስረጃ የለም፡፡ ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ ካሉ መጻሕፍት አንዱ በሆነው በመኃልየ መኃልይ ገልጾታል፡፡ ይህ መጽሐፍ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች የማይረዱትና ለዝሙት እንደሚያነሣሣ መጽሐፍ አድርገው የሚተቹት መጽሐፍ ነው፡፡ ነገር ግን በጋብቻ ትስስር ውስጥ አንዳች ኃጢአትና ለዝሙት የሚገፋፋ አንዳች ነገር የለበትም ፤ ለክርስቶስና ለቤተ ክርስቲያን አንድነት ምሳሌ ነው እንጂ፡፡ ‹‹ባሎች ሆይ፥ ክርስቶስ ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ … ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ ሰጠ›› (ኤፌ. ፭፥፳፭) በጋብቻ የሚፈጸም ሩካቤ ከዝሙት የሚለየውም በዚህ ነው፡፡ በኃጢአት የሚፈጸም ጾታዊ ግንኙነት የሚያተኩረው በመውሰድ ፣ በማግበስበስ ፣ በመበዝበዝ ፣ ራስን በማርካት ላይ ብቻ ሲሆን በጋብቻ የሚፈጸም ግንኙነት ግን ትኩረቱ በመስጠት ላይ ነው፡፡

በጋብቻ ውስጥ ያለው ፍቅር ‹‹ስለ እርስዋ ራሱን አሳልፎ የሰጠ›› ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን ባሳየው ፍቅር መመዘን አለበት፡፡ በጋብቻ ውስጥ ያለ ፍቅር ራስን መስጠት ነው እንጂ ማግበስበስና መውሰድ አይደለም፡፡ ይህም ነው የተቀደሰ የሚያደርገው፡፡ ምክንያቱም ይህ ክርስቶስን መምሰል ነው፡፡

ቅዱስ ጳውሎስ ‹‹ከዝሙት ሽሹ!›› ብሏል፡፡ ነገር ግን አንድ ሰው ‹‹ይህን ከማድረግ ይልቅ መናገሩ ቀላል ነው!›› ሊል ይችላል፡፡ እስማማለሁ! ድንግልና በቀላሉ የማይገኝ ቅድስና ነው፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ ደረስሁ ልትል የምትችለው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በዚህ ሕይወት ውስጥ በጥልቀት ስትገባ ብቻ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዝሙት አጥፊነት ይነግረናል፡- ‹‹ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ ፤ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም፡፡›› (፩ቆሮ. ፯÷፱–፲)

በዚህ ሁሉን የሚያጠቃልል ዐረፍተ ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉንም ዓይነቶች ያልተገቡ ጾታዊ ድርጊቶችን ሁሉ ያወግዛል፡፡ ዝሙት ከጋብቻ በፊት የሚፈጸም ሩካቤ ሲሆን ሴሰኝነት ደግሞ ከጋብቻ ላይ ተደርቦ የሚፈጸም ሩካቤ ነው፡፡ እነዚህ የአንድ ኃጢአት ሁለት ደረጃዎች ሲሆኑ ቅጣታቸው ግን የተለያየ ነው፡፡ ዘማዊ ሰው በራሱ ሰውነትና በዝሙት አቻው ሰውነት ላይ ኃጢአትን ይሠራል፡፡ ሴሰኛ ግን በራሱ ሰውነት ፣ በኃጢአት ተባባሪው ሰውነትና በትዳር አጋሩም ሰውነት ላይ ኃጢአትን ይሠራል፡፡ ግብረ ሰዶማዊነትም የተወገዘ መሆኑ የማይዘነጋ ነው፡፡ ወንዶች ሆነው ሳለ እንደ ሴት የሚሆኑም ሆነ ራሳቸውን በጾታ በሚመስላቸው ጥቃት

እንዲደርስባቸው የሚያመቻቹ ሁሉ በዚህ ግብረ ሰዶማዊነት ተሳታፊዎች ናቸው፡፡

የሴቶች ግብረ ሰዶማዊነትም በመጽሐፍ ቅዱስ የተወገዘ ነው፡፡ ‹‹ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤›› (ሮሜ. ፩፥፳፮)

ጌታችንም ስለዚህ ፍትወታዊ ድርጊትና ተገቢ ስላልሆነ ጾታዊ ተራክቦ እንዲህ ሲል ተናግሮአል፡፡ ‹‹እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል፡፡›› (ማቴ. ፭፥፳፰) ይህ ቃል ሴት ወደ ወንድ አይታ ስለ መመኘትዋም ሆነ ወንድ በጾታ የሚመስለውን ሌላ ወንድ መመኘቱ ጥፋተኝነት ስለመሆኑ ምንም አይልም፡፡

ዛሬ ዛሬ ዝርዝሩ ብዙ ሆኗል፡፡ ለዝሙት የሚያነሣሡ እይታዎች ሌላው ቀርቶ ለትናንሽ ሕጻናት እንኳን ፈተና ሆነዋል፡፡ ይህ ዓይነቱ ዝሙት ቀስቃሽ ትርዒት ደግሞ ዝሙትን እየፈጸሙ ያለ ያህል እንዲሰማቸው የሚያደርግና [6]ግብረ አውናን /masturbation/ እንዲፈጽሙ የሚያደርጋቸው ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህን የርኩሰት ተግባራት የሚያወግዝ ቢሆንም እንዴት እንደምንዋጋቸው ግን በዝርዝር አላስቀመጠም፡፡ ለዚህ ጉዳይ ደግሞ ወደ በረሃ አባቶች የሕይወት ልምድ መለስ እንላለን፡፡ እነርሱ በጉዳዩ ላይ ተጠያቂዎች ናቸው፡፡

---

[6] ስለ ግብረ አውናን ምንነትና መፍትሔዎቹ ሕይወተ ወራዙት ቁጥር አንድ በዲያቆን ኅብረት የሺጥላ ይመልከቱ፡፡

## መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን መፈጸም

የበረሃ አባቶች እንደሚሉት ከሆነ አንድ ሰው ንጽሕናን ከመፈለጉ በፊት ሊሔድባቸው የሚገቡ የመጀመሪያ ተግባራት አሉ፡፡ ቀዳሚ ያሉዋቸው ተግባራትን እነሆ!

### ሆድህን ተቆጣጠር

በሆዳምነት ለተሸነፈ ሰው ንጽሕናን ማግኘት እጅግ የማይመስል ነገር ነው፡፡ ይህም የአባቶች ሐሳብ የሚስማማበት ነው፡፡ የሆድ መሙላት የሥጋን ምኞት ያቀጣጥላል፡፡ አንድ ሰው ለምግብ ያለውን ፍላጎት መግታት ካልቻለ የበለጠ አስቸጋሪ የሆነውን ጾታዊ ፍላጎት ሊገታ አይችልም ብንለው የበለጠ ይገልጸዋል፡፡

### እንቅልፍህን ተቆጣጠር

እንቅልፍን ማብዛትም የጾታዊ ዝንባሌን በመጨመር በኩል አስተዋጽኦ ያደርጋል ይላሉ አባቶች፡፡ አንድ ሰው በፍትወት ኃጢአት እንዳይወድቅ አብዝቶ ላለመተኛት መዋጋት አለበት፡፡ መጽሐፍ ቅዱስም በግልጽ አብዝቶ መተኛትን እየተቃወመ ይነግረናል፡- ‹‹አንተ ታካች፥ እስከ መቼ ትተኛለህ? ከእንቅልፍህስ መቼ ትነሣለህ?›› ‹‹ድሀ እንዳትሆን እንቅልፍን አትውደድ ዓይንህን ክፈት፥ እንጀራም ትጠግባለህ፡፡›› ሲል ያሳስበናል፡፡ (ምሳ. ፮፥፲፫ / ፳፥፱)

## ንዴትህን ተቆጣጠር

አባቶቻችን ቁጣችንን መቆጣጠር ካልቻልን ሥጋዊ ምኞቶቻችንንም መቆጣጠር እንደማንችል በአጽንዖት ይመክሩናል፡፡ አባቶች የኃጢአትን ዓይነቶች ሲዘረዝሩ ቁጣና ዝሙትን በአንድ ምድብ ‹‹ስሜት ቀስቃሽ ከሆኑ ኃጢአቶች›› ጋር ይመድቧቸዋል፡፡ አንድ አባት እንዲያውም የቁጣ ሰይጣንና የዝሙት ሰይጣን አንድ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ በቀላሉ ለቁጣ የሚነሣሣ ሰው በቀላሉ የሥጋው ፍላጎትም የሚነሣሣ ነው፡፡ አባቶች ስለዚህ የሚነግሩን እነሆ ፡-

አንድ ሰው በእርጋታና በልብ ጽናት እያደገ ከመጣ በሰውነቱ ንጽሕናም ላይ ይህ ለውጥ ይታያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቁጣን ስሜት ማስወገድ ከቻለ የበለጠ በጠበቀ መንገድ ንጽሕናን ማግኘት ይችላል፡፡

ከወጣቶች ጋር በነበረኝ ቆይታ በተነሣ ልጨምራቸው የሚገቡ ሁለት መሠረታዊ ነገሮችም አሉ፡፡

### መጠጣት

አልኮል የሥጋን ስሜት እጅግ የሚያነቃቃ ነው፡፡ አንድ ሰው መጥኖ ቢጠጣ እንኳን የፍትወት ስሜቱን ለመግታት ያለው ኃይል ይፈረካከሳል፡፡ ታላቁ ሼክስፒር ወይን በጾታዊ ጠባይ ላይ የሚያመጣውን ለውጥ አስመልክቶ በጻፈበት ተውኔቱ ‹‹መጠጥ ምኞትን ይጨምርና ዓቅመ ቢስ ያደርጋል!›› ብሏል፡፡ በክህነት ባገለገልኩባቸው በርካታ ዓመታት ስለ መጠጥና ዝሙት በርካታ

የሚያስጨንቁ ታሪኮችን የሰማሁኝ ቢሆንም የሚከተለው ታሪክ ግን ከኅሊናዬ አይጠፋም፡፡

ታሪኩ ከጀርመን የዘር ሐረግ ስለተወለደችና በጣም ሃይማኖተኛ ስለነበረች የ0ሥራ ስድስት ዓመት ልጃገረድ ነው፡፡ ልጆቼ ትናንሽ እያሉ እቤቴ ትመጣና ልጆቼን ትጠብቅ ነበር፡፡ ለልጆቻችን መጽሐፍ ቅዱስ ታነብላቸው ስለነበርና ይህም በዚያን ጊዜ የማይገኝ ብርቅ ነገር ነውና እንወዳት ነበር፡፡ አንድ ቀን እናቷ ‹‹አንቺ እኮ ምንም ዓይነት ሕይወት እያሳለፍሽ አይደለም! ለምን የጎረቤቶቻችንን የአዲስ ዓመት ድግስ ላይ አትሔጂም?›› ትላትና ልጅቷም ትስማማለች፡፡ በድግሱ ላይ አንዱ ለየት ያለ ጣዕም ያለው የቡርቱካን ጭማቂ ይሰጣትና ትጠጣለች፡፡ በዚያች የአዲስ ዓመት ድንግልናዋን ያጣች ብቻ እንዳይመስላችሁ በኋላም ማርገዟን አወቀች፡፡ ይህንን የፈጸመባት ሰው ደግሞ ያገባና ልጆች ያሉት ሰው ነበረ፡፡ እናትዋ ጽንስ እንድታስወርድ አልለቀቀቻትም፡፡ ጡረታ የወጣች ነርስ ብትሆንም ልጅዋ ጽንሱን እንድትወልድ ብላ /ዓቅም እንዳያንሳቸው/ ወደ ሥራዋ ተመለሰች፡፡ ከስድስት ወራት በኋላ ግን ልጅቷ በልብ ድካም ሞተች፡፡

### ጭፈራ

ጭፈራ ጾታዊ ግንኙነቶች ከሚጀመሩባቸው ከተለመዱ መንገዶች አንዱ ነው፡፡ አሁንም በአእምሮዬ ተቀርጾው ከቀሩ በርካታ አሰቃቂ ታሪኮች አንዱን ብናገር ይበቃል፡፡ በሰማኒያዎቹ ውስጥ ነው፡፡ ዕረፍት በወጡ ካህን ፈንታ ለማገልገል ወደ አሜሪካን ሀገር እየሔድኩ ነበር፡፡ ከቅዳሴ በኋላ ለመናዘዝ የምትፈልግ የ0ሥራ

ሦስት ዓመት ልጅ ወደ እኔ መጣች፡፡ ወደ ተካጊቸው ካህን ጽሕፈት ቤት ይዤያት ሔድኩ ፤ እያለቀሰችና ሳግ እየተናነቃት ተከተለችኝ፡፡ ላረጋጋት ከሞከርኩ በኂላ ለምን እንደምታለቅስ ጠየቅኂት፡፡ በመጨረሻም ‹‹ዝሙት ፈጽሜያለሁ›› ብላ ትነግረኝ ጀመር፡፡ ነገሩ የሆነው (በቤተሰቦቿ ገፋፊነት) ለጭፈራ ሔዳ ነው፡፡ ከዐሥራ አምስት ዓመት ታዳጊ ጋር ስትጨፍር ከመንጋቱ በፊት ድንግልናዋን አጣች፡፡ ‹‹አስገድዶ ከክብር አሳነሰሽ?›› ብዬ ጠየቅኂት፡፡ ‹‹አይደለም አባታችን የእሱን ያህል እኔም ፍላጎቱ ነበረኝ፡፡ ከዘፈኑና ከመብራቶቹ ጋር የእኛ አካልም ከመቀራረቡ ጋር የመቃወም አዝማሚያ አልነበረኝም፡፡›› ነበረ ምላሿ፡፡

እስቲ ደግሞ ወደ አባቶች እንመለስ፡፡ ምንም እንኳን አብዝቶ መብላትን አብዝቶ መተኛትንና ቁጣን መግታት ብንችል እንኳን ንጽሕናን ለማግኘታችን ከመቻላችን በፊት አንድ የሚያስፈልገን አንዳች በጎነት አለ ይሉናል፡፡ ‹‹ንጽሕናን የምትመኝ ከሆነ ትሕትናንም ተመኝ፡፡ ምክንያቱም ያለ ትሕትና ንጽሕናን ለማግኘት አትችልም፡፡›› የሥጋ ፍላጎትን በመዋጋት ውስጥ ትልቁ ችግር በራስ መመካት ነው፡፡ ‹‹ይህንንና ይህንን ላደርግ ነው ፤ ድሉም የእኔ ይሆናል!››

መንፈሳዊ ተጋድሎን በተመለከተ አንድ አስተተያየት ልስጣችሁ፡፡ ‹‹እኔ›› በሚለው ቃል የሚጀምር ማንኛውም ነገር መፍረሱ አይቀሬ ነው፡፡ በራሳችን መተማመንን ካልተውን በቀር አሁንም አሁንም መላልሰን እንወድቃለን፡፡ ራስን በመቆጣጠር

ሥጋዊ ምኞቱን መቆጣጠር የቻለ ማንም የለም፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ከአባቶች አንዱ የሚነግረንን እነሆ፡-

> በራሳችን ጥረት ንጽሕናን ማግኘት አይቻለንም ፤ ያለማቋረጥ እየተጋን እንኳን ከልምድ ትምህርት ቤት የተማርነው ከመለኮታዊው የጸጋ ሥጦታ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህ የተነሣ አንድ ሰው ያለ መታከት በጥረቱ መቀጠል አለበት፡፡ ለአምላካዊው ሥጦታው ምስጋና ይድረሰውና ያን ጊዜ ከሥጋዊ ውጊያ ነጻ ለመሆን የተገባ ይሆናል፡፡ የሚፈልገውን የሰውነት ንጽሕና በራሱ ማግኘት እንደሚችል አድርጎ ማመን የለበትም፡፡

ይህንን ጽንሰ ሐሳብ ለወጣቶች ለማስረዳት በምሞክርበት ጊዜ የሚከተለውን ንጽጽሮሽ እጠቀማለሁ፡፡ በጠረጴዛ ላይ የተቀመጠ አሻንጉሊት ላይ ለመድረስ የሚሞክርን ትንሽ ሕጻን አስቡ፡፡ ጠረጴዛው ከእርሱ ቁመት በጣም ስለሚረዝም ለመድረስ አያስችለውም፡፡ በእግሮቹ ጥፍር ለመቆም ሞከረ ነገር ግን አልቻለም፡፡ ወደ ላይ ለመዝለልም ሞከረ ነገር ግን ሊደርስ አልቻለም፡፡ በሌላ ዕቃ ላይ ለመወጣጣትም ሞከረ ትርፉ ግን ወድቆ ራሱ መጉዳት ብቻ ነበር፡፡ ሙሉ በሙሉ ሲዳከም ማልቀስ ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ ሲያየው የነበረው አባቱ ደርሶ ጠረጴዛው ላይ ያለውን መጫወቻ ሰጠው፡፡ ትንሹ ሕጻን በራሱ ጥረት መጫወቻዎቹን አላገኘም፡፡ ሆኖም ጥረቶቹ የአባቱን ልብ ለመርዳት አነሣሣው፡፡

ችግሩ እኛም እንዲሁ መሆናችን ላይ ነው፡፡ እንሞክራለን ፣ እንሞክራለን ፣ እንወድቃለን፡፡ ስንደክምም እንጮኻለን፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር ከውጊያው እንድናርፍ ያደርገናል፡፡ ነገር ግን ዲያቢሎስ ወዲያውኑ ወይም ቆይቶ ይህንን ያደርግነው በራሳችን

ጥረት እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ይህንን ሐሳብ በልብ እንዳመንህ ሁሉን ነገር ታጣና ወደነበርህበት ሥፍራ ትመለሳለህ፡፡ የሚያስደንቀው ነገር ይህ ነገር መደጋገሙ ሲሆን እንዴት በድጋሚ እንደወደቅን እንኳን ሳንረዳ ያንኑ ስኅተት መደጋገማችን ነው፡፡ አበምኔቱ ሼይርሞንም ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ብሎአል ፡-

> አንድ ሰው ለረዥም ጊዜ በንጽሕና ለመኖር በመቻሉ ከእንግዲህ ቅድስናዬን አላጣም እያለ መደሰት ከጀመረ በራሱ መመካት ይጀምራል፡፡ እግዚአብሔር ልርሱ ጥቅም ሲል ቸርነቱን ሲያርቅበት ግን የተማመነበት የንጽሕና ደረጃው እየተወው እንደመጣ ይረዳል፡፡ የመጽናቱ ምንጭ ወደ ሆነው አምላክም ይመልሰዋል፡፡ አንድ ሰው የሚፈልገውን ንጽሕና የሚያገኘው በእግዚአብሔር ቸርነት መሆኑን እስኪያረጋግጥ ድረስ በእነዚህ መነዋወጾች ከአምላኩ መማር አለበት፡፡

እነዚህ ‹መነዋወጾች› ወደ እውነተኛ ንጽሕና እስከሚደርስ ድረስ ብዙ ዓመታትን ሊወስዱ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የሚያጋጥሙን መታወኮች ልምድን የሚሰጡን ዝሙትን በመዋጋት ብቻ ሳይሆን ትዕቢትንና መመጻደቅንም ስለሚዋጉልን ነው፡፡

በዚህ ፈተና በተደጋጋሚ ስትወድቅ አትደናገጥ፡፡ ምክንያቱም አበምኔቱ ሼይርሞን እንደሚነግረን ከሆነ ብዙ ልምድ ላለውም እንኳን አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡ ከታላላቆች ሴት የበረሃ መናኞች አንድዋ የሆነችው እማ ሣራ እግዚአብሔር ከዚህ ስሜት ነጻ እስካደረጋት ድረስ ለዐሥራ አራት ዓመታት ከዝሙት ሐሳት ጋር ተዋግታለች፡፡ ቅዱስ ሙሴ ጸሊምም እንዲሁ፡፡

በመጨረሻም በተደጋጋሚ ጊዜያት ስንወድቅ ድል የተነሳነው ምን ማድረግ እንዳልቻልን እንድናውቅ ነው ብለን እናስባለን፡፡ ከዚያም ወደ ልብ ትሕትና እንደርስና ድል መነሳታችንና ይህንን ውጊያ ለማሸነፍ ፈጽሞ እንደማንችል እንረዳለን፡፡ በዚህ ጊዜ ነው እግዚአብሔር ከመካከል የሚገባውና ከአሳዛኝ ሁኔታ ነጻ እንድንወጣ የሚያደርገን፡፡ ይኼን ጊዜ በደካማ አቅማችን ራሳችንን ዝቅ ዝቅ እናደርጋለን ፣ ቸርነቱንንም እናደንቃለን፡፡ ከዚህም በኋላ ውጊያው ድል አይነሳንም ፣ ፈተናውም አያውከንም፡፡ በሥጋችን የሚመጣብን ድንገተኛ ድቀትና ኃጢአትም በእርግጥ ከእግዚአብሔር ቸርነት የሚመጣ መሆኑንና ከእኛ ጥረት ጋር ያልተገናኘ መሆኑን ስለምንረዳም በልባችን ድንቅ የሆነ ደስታ ይሰማናል፡፡

## ስንጽሕና የሚደረግ ተጋድሎ

እንደሌላው የጽድቅ ሥራ ሁሉ ንጽሕናን ለማግኘት በሚደረገው ተጋድሎ ውስጥም ጸሎት ቀዳሚው ሒደት ነው፡፡ በከንፈርህ ብቻ ልታገለግለው እንደማትሻና በእውነት ንጽሕናን እንደምትፈልግ ለእግዚአብሔር አሳየው፡፡ ርኵሰትን መጥላት አለብህ፡፡ ምክንያቱም በውስጥህ ኃጢአትን እየወደድህ ንጽሕናን እንዲሰጥህ በመለመን እግዚአብሔርን ልታታልል አትችልም፡፡

ነገር ግን እዚህ ደረጃ ላይ ያልደረስህ ከሆንክስ? አንዳንድ ወጣቶች ወደ እኔ ይመጡና ‹‹ንስሐ መግባት እፈልጋለሁ ኃጢአትን ለመጥላት ግን አልቻልሁም›› ይሉኛል፡፡ ደህና ፣ በታማኝነት ወደ አምላክህ ሒድና ስለገባህበት አጣብቂኝ ንገረው፡፡ ከመዝሙረኛው ጋር ‹‹አቤቱ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ›› በል፡፡

ጠዋት በማዕጠንት ላይ መባዕ ለሚያስገቡ ሰዎች እግዚአብሔር ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ እጅግ ያማረ የመስተብቍዕ ጸሎት ይደረግላቸዋል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር [7]‹‹የመስጠት ፍላጎት ያላቸውንና የሚሰጡት የሌላቸውን›› ዋጋ እንዲሰጥ ይጸለያል፡፡ አንተም ከዚህ ጸሎት ወስደህ ራስህን በመድኃኔዓለም እግር ሥር ደፍተህ እንዲህ በል፡፡ ‹‹ጌታ ሆይ ሊሰጡ እየወደዱ የሚሰጡት ከሌላቸው ሰዎች አንዱ ነኝ፡፡ አልተቻለኝም እንጂ እውነተኛ የሆነ ንጽሕናን የመፈለግ ምኞትን ላቀርብልህ እወድድ ነበር፡፡››

ቅዱስ አውግስጢኖስ በአንድ ወቅት ስለዚህ ደረጃ እንዲህ እያለ ይጸልይ ነበር ‹‹አምላኬ ሆይ! መጸጸትን እፈልጋለሁ! ገና የሚቀሩኝ (የኃጢአትን) ደስታዎች አሉብኝና አሁን ግን አልችልም፡፡›› እግዚአብሔርም ከቅዱስ አውግስጢኖስ ጋር ሆነ ለሠላሳ ዓመታት በኃጢአት የኖረው ሰውም ጻጻስ ለመሆን በቃ!

በንጽሕና ለመኖር ለእግዚአብሔር ስእለት መሳልንና አንዳች ነገርንም ቃል ከመግባት ተጠንቀቅ፡፡ ምክንያቱም እንዲሁ ቃል የምትገባው ነገር ወዲያውኑ ልትቆጣጠረው የማትችለው ዓይነት ነገር ሊሆን ይችላልና፡፡

ከጸሎት በኋላ ከልብህ ኃጢአትን ለመቃወም መነሣት አለብህ፡፡ ክፉ ሐሳቦችን ያለ አንዳች የማስቆም ሙከራ እያሰብሃቸው ወይም ለዝሙት የሚያነሣሡ ሥዕላትንና ምስሎችን እየተመለከትህ

---

[7] ‹‹ወለእለሂ ይፈቅዱ የሀቡ አልቦሙ ዘይሁቡ ይትወከፍ ፍትወቶሙ ዘበሰማያት መንግሥተ ይጸጉ›› ‹‹ሊሰጡ ወደው ሳሉ የሚሰጡት ያጡትን የሐሳባቸውን እንደ ሥራ ቆጥሮ መንግሥተ ሰማያትን ይሰጣቸው ዘንድ›› (ጸሎተ መባዕ ዘሐዋርያት)

እግዚአብሔር ንጽሕናን እንዲሰጥህ ብትለምን የማይመስል ነገር ነው።

በምታደርጋቸው ጥረቶች ወዲያውኑ ውጤቶችን አገኛለሁ ብለህ አትጠብቅ ይህ በራስ መታመን ነው። የአንተን ዕድገት የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነው። የመጨረሻውን ውጤት ሳትጠብቅ ባለህ ኃይል ሁሉ ተጋደል። እግዚአብሔር ከዲያቢሎስ ጋር እንደማትገዳደር ያውቃልና ሁልጊዜ ድል እንድታደርግ አይጠብቅብህም። ነገር ግን በመጨረሻው ብትሸነፍም እንኳን እግዚአብሔር ያለ መታከት እንድትዋጋ ይፈልጋል።

ባሕታዊው አባ ቴዎፋን ለዚህ ጉዳይ ጥሩ ንጽጽር አቅርቦአል። ‹‹በጠላቶቹ ተከብቦ በውጊያው ክፉኛ እስከሚቆስል ድረስ ሳያቋርጥ የተዋጋ ሰው ጀግና ተብሎ ሜዳይ ይሸለማል። ጠላቶቹ ሲከብቡት ነጭ ሰንደቅ አሳይቶ ከተማረከ ግን እንደ ከዳተኛ ተቆጥሮ ይቀጣል።›› ብሏል።

በእርግጥ አንተ እንደ ጠፋህ ትቆጥረው ይሆናል ፤ እግዚአብሔር ግን እንደ ድል ይቆጥረዋል። በቅዱስ አትናቴዎስ በተጻፈው ‹‹የቅዱስ እንጦንዮስ ሕይወት›› ይህንን የሚያሳይ ጥሩ ታሪክ አለ። ቅዱስ እንጦኒን በብዙ ዓይነት መንገዶች በዲያቢሎስ ተፈትኖአል። ሊያስደነግጠው ሲፈልግ በአራዊት እየተመሰለ ይታየዋል ፣ በሴትና በወርቅ ሊፈታተነው ይሞክራል ሆኖም ቅዱስ እንጦኒ ተቋቋመው። በመጨረሻም በሚያስፈራ ገጽ ኀሊናውን እስከሚስት ድረስ ደበደበው። በዚህ ሁኔታ ላይ ሆኖ ያገኘው ደቀ መዝሙሩም ተሸክሞ በአቅራቢያው ባለች መንደር በምትገኝ ቤተ

ክርስቲያን አስቀመጠው፡፡ ቅዱስ እንጦኒ ራሱን ሲያውቅ የቤተ ክርስቲያኑ ጣሪያ ተከፍቶ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብሩ ዙፋን ላይ ተቀምጦ ታየው፡፡ ቅዱስ እንጦኒም ለራሱ አዝኖ ‹‹ጌታ ሆይ ዲያቢሎስ ሲደበድበኝ ወዴት ነበርህ?›› ብሎ ጠየቀ፡፡ ‹‹እንጦንዮስ ሆይ በስተቀኝህ ነበርሁ፡፡ ብርቱ ሆነህ ነበርና የምታገኘውን ክብር እንዳታጣ ስል እጄን አላስገባሁም!›› አለው፡፡

አየህ ቅዱስ እንጦኒ ዲያቢሎስ በድብደባ ያደረሰበትን ጥቃት ተመለከተ እግዚአብሔር ግን ለሽልማት የሚያበቃውን ድል ተመለከተ፡፡ ከዚህ ታሪክ የሚገኘው ትምህርትም ስለ ውጊያው ውጤት ሳትጨነቅ ዝም ብህ ተዋጋ! የሚል ነው፡፡

## የጠላት ማታለያዎች

ዲያቢሎስ ውጊያውን እንድናቆም ሲል ሊያታልለንና በመንገዳችን ላይ በርካታ እንቅፋቶችን ሊያኖር ይችላል፡፡ ጥቂቶቹ ማታለያዎች እነዚህ ናቸው፡፡

ለረዥም ጊዜ ከታገልኸው በኋላ በመጨረሻ ድል ታደርጋለህ፡፡ ይሄን ጊዜ ‹‹ሁሉም ነገር እስከጠፋልህ ድረስ ለምን ትንሽ ዘና ብለህ ደግሞ ቆይተህ ውጊያውን አትቀጥልም?›› ይልሃል፡፡ ስኅተት ነው! ያለ መታከት እስከተዋጋህ ድረስ ሁሉም ነገር አልጠፋም ፤ በውጊያው ቆሰልህ እንጂ አልተሸነፍህም፡፡ መልሰህ ለኃጢአት እጅ አትስጥ ይህ ክህደት ነው፡፡ በውጊያ መካከል ብትወድቅ እንኳን ሽልማት ግን ይገባሃል፡፡ ‹‹ሁሉም ነገር ጠፍቶልሃል!›› ‹‹ከዚህ በኋላ መዋጋትህ ምንም ለውጥ አያመጣም!›› የሚሉትን ምክሮች መስማት ደግሞ ሽልማትህን እንዲቀማህ

መፍቀድ ነው፡፡ እናም ተነሥተህ ውጊያህን ቀጥል ለሚያጠቁህ ሐሳቦችም አትረታ፡፡ የዲያቢሎስን ፈተናዎች ተቋቁሞ ድል ያደረገ ጌታ ያዝንልሃል ፣ ይረዳህማል፡፡

ሌላው ማታለያ ይህ ነው፡፡ በመጨረሻ መሸነፍህ ለማይቀረው ለምን በውጊያ ራስህን ታደክማለህ? እያለ ይነግርሃል፡፡ ይህንን ለአንድ መነኩሴ ነግሮት ነበር ፣ መነኩሴውም ‹‹አንድ ቡጢ ለአንተ አንድ ቡጢ ደግሞ ለእኔ!›› አለው፡፡ ይህ ልክ እንደ ቦክስ ውድድር ነው፡፡ የቱንም ያህል ብትመታም ተጋጣሚህን የቻልኸውን ምት ትሰነዝርበታለህ፡፡ ውጤቱን ግን የምታውቀው በውድድሩ ፍጻሜ ላይ ብቻ ነው፡፡

ሌላው የታወቀ ማታለያ ደግሞ ይህ ነው፡፡ በኃጢአት ትወድቃለህ ፣ ጥፋተኝነት ይሰማህና ወደ አምላክህ መመለስና ይቅርታን መለመን ትፈልጋለህ፡፡ ዲያቢሎስ ግን ‹‹ይህንን ሁሉ ካደረግህ በኋላ የእግዚአብሔርን ፊት ለማየትና ከእርሱ ጋር ለመነጋገር የምትነሣው እንዴት ብትደፍር ነው?›› ይልሃል፡፡ ከዚያም እንዲህ ሲል ይመክርሃል፡፡ ‹‹ግዴለህም ንጹሕ እስከምትሆን ድረስ ለጥቂት ሰዓታት ወይም ለጥቂት ቀናት ቆይና ጸልይ!›› ይልሃል፡፡ ትልቅ ስኅተት! እንዲሁ እንዳለህ ወደ አምላክህ ና! የጠፋው ልጅ ወደ አባቱ ለመመለስ ሲወስን ወዲያውኑ መጣ፡፡ አብሮአቸው ይኖር ስለነበር የዐሣማዎቹ ክርፋት በላዩ ላይ ነበር፡፡ ንጹሕ ልብስ እስከሚለብስ ድረስ ግን አልቆየም፡፡ ያደፈ ልብሱን ያወለቀለትና ንጹሕ ልብስን ያለበሰው አባቱ ነበር፡፡ አባቱ ሞቶ በነበረውና አሁን ግን ሕያው በሆነው በልጁ ፍቅር ተሸንፎ ነበር፡፡

የኃጢአት ሽታ በመላ ሰውነቱ ላይ ቢኖርም ወደ እርሱ ሮጠና አቀፈና ሳመው፡፡

ኦርቶዶክሳዊው መነኩሴ አባ ሌቭ ጊሌት በመንፈሳዊ ጽሑፎቹ ላይ አንድ ጊዜ እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ ‹‹አንተም ኃጢአት በምትሠራ ጊዜ እግዚአብሔር እንደሚወድህ እርግጠኛ መሆን አለብህ፡፡›› ዲያቢሎስ በተቃራኒው ሊነገርህ ይችላል ፤ እርሱ ግን ሐሰተኛ ነው፡፡

እናም እንደወደቅህ ወዲያውኑ በተወደደው አባትህ ፊት ተንርክከህ ‹‹አባት ሆይ በሰማይና በፊትህ በደልሁ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅህ ልባል አይገባኝም›› በለው፡፡ ወዲያውኑ አባትህ በደስታ ሲያቅፍህና በፍቅር ሲስምህ ታገኘዋለህ፡፡ ዳግመኛም በቁርጠኝነት ወደ ውጊያው ተመልሰሃል ማለት ነው፡፡ ይህ የጸጸት መጀመሪያ ተግባር ግን ለንስሐ አባትህ የምታደርገውን ኑዛዜ የሚተካ ነው ማለት አይቻልም፡፡

ከዚህ በኋላ የሚሞክረው ሌላው ማታለያ ደግሞ ይህ ነው፡፡ ይመጣና እንዲህ ይልሃል ፣ ‹‹ይህ ኃጢአት ስትሠራ አሁን ለስንተኛ ጊዜ ነው? ወደ እርሱ በመጣህ ቁጥር እግዚአብሔር የሚቀበልህ ይመስልሃል?›› መልሱ ግን አዎ ነው! ቅዱስ ጴጥሮስ ለጌታችን ምን ያህል ጊዜ ወንድሙን ይቅር ማለት እንደሚገባው በጠየቀው ጊዜ ጌታችን ሰባት ጊዜ ሰባ ብሎ መልሶለታል፡፡ እኛ እርስ በእርሳችን ሰባት ጊዜ ሰባ ይቅር እንድንባባል የሚጠብቅብን አምላክ እሱ ራሱ ይህንን ዓይነቱን ዕድል የማይሰጠን ይመስላኗል?

በወደቅህበት መጠን ወደ እግዚአብሔር ተመለስ፡፡ መቼም ጀርባውን አይሰጥህም፡፡

አንድ ምእመን ወደ ገዳም ሔዶ ከመነኮሳት አንዱን ‹‹እናንተ መነኮሳትን በዓለም ከምንኖረው ሰዎች የሚለያችሁ ምንድር ነው?›› ብሎ ጠየቀው፡፡ መነኩሴውም መለሰ ‹‹እንወድቃለን ከዚያም እንነሣለን ፣ ከዚያም እንወድቃለን ደግሞ እንነሣለን ፣ እንወድቃለን ደግሞ እንነሣለን…›› አለው፡፡ አያችሁ! በአንድ ጀልባ ላይ ነን እኮ!

በተደጋጋሚ ስትወድቅ ከመጠን በላይ አትዘን ባሕታዊው ቴዎፋን እንደተናገረው ይህ የትዕቢት ምልክት ነው፡፡ እግዚአብሔር ትሕትናን ሊያስተምርህ የላከልህ መፍትሔ አድርገህ ውሰደው፡፡ ከበረሃ አባቶች እንዲህ አለ ፦ ‹‹በትሕትና ሆኖ መሸነፍ በትዕቢት ሆኖ ድል ከማድረግ ይሻላል፡፡›› ቅዱስ ይስሐቅ ሶርያዊም ‹‹አንዳንዶች እግዚአብሔርን በጽድቃቸው ያስደስቱታል ፤ ሌሎች ደግሞ በተጸጸተና በተሰበረ ልብ›› ብሏል፡፡ እናም በኃጢአት ብትወድቅ እንኳን የተሰበረና የተጸጸተ ልብ ይኑርህ ፤ ይህ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል፡፡

አንዳንድ ሰዎች ለብዙ ጊዜ ሞክረው ሳይሳካላቸው ሲቀር ተስፋ ይቆርጣሉ፡፡ አንዱ አበምኔቱ ሻይርሞንን ‹‹ንጽሕናን ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?›› ብሎ ጠየቀው፡፡ እሱም መለሰለት ፦

> ከማይጠቅሙ ወሬዎች ሁሉ ራሱን የሚያርቅ ሰው ፣ ቁጣንና ዓለማዊ ጭንቀትና ሐሳብን ሁሉ መግደል የቻለ ሰው ፣ ከልክ በላይ የማይበላና የማይተኛ ሰው ፣ እንዲሁም ንጽሕናን የሚያገኘው በራሱ ጥረት ሳይሆን

በእግዚአብሔር ምሕረት እንደሆነ ለሚያምን ሰው ንጽሕናን በስድስት ወራት ውስጥ ማግኘት አያቅተውም፡፡

ገና የመንፈሳዊነት ደረጃ ላይ ላልደረሰ ሰው ወደ ንጽሕና ደረጃ ለመድረስ ምን ያህ ጊዜ የሚፈጅበት ይመስላኋል? ስድስት ወራት? አስተማማኝ የሆነ ድልን እስከምታገኝ ድረስ ለዐሥራ አራት ዓመታት የተጋደለችውን እማ ሣራን አስቧት፡፡

አንዳንድ ጊዜ እኛ ራሳችን ዲያቢሎስን ልናታልለው እንችላለን፡፡ ልክ እንደ አንድ መነኩሴ፡፡ ይህ መነኩሴ በጣም እየራበው ቁርስ የመብላት ፈተና ይመጣበታል፡፡ እሱም ‹‹አንድ ሁለት መዝሙራትን እንጸልይና እንበላለን!›› ይላል ፤ ከዚያም ‹‹በቃ ሁለት መዝሙራት ብቻ ልጨምርና ከዚያ በእርግጠኝነት እበላለሁ!›› ይላል እንዲህ እያለም ይቀጥላል፡፡ ወዲያውኑ ረሃብ ይጠፋለታል ምክንያቱም ዲያቢሎስ ስለተሰላቸ ነው፡፡ እኛም ለኃጢአት የሚገፋፋንን ስሜት ለመዋጋት ተመሳሳይ ዘዴ መጠቀም እንችላለን፡፡ አንተም ‹‹እስቲ የዛሬን አርፌ ልተኛና ነገ የሚሆነውን እናያለን!›› ልትል ትችላለህ፡፡ በዚህ መንገድ እስክንደክም ድረስ እንኳን የምንወድቅበትን ጊዜ ማራዘም እንችላለን፡፡ ቀስ በቀስም የመቆየት ኃይላችን ሲጨምር በዚያው ልክ መውደቃችን እየቀነሰ ይመጣል፡፡

በመጨረሻም እግዚአብሔር ንጽሕናን ሲሰጠን ምን ማድረግ አለብን? እስቲ አበምኔቱ ሼይርማን በዚህ ጉዳይ ላይ የሚለንን እንስማ ፡-

ንጽሕናን ያገኘ ሰው በተቀዳጀው ቅድስና ሲደሰት በእሱ ጥረትና ንቃት ሳይሆን በእግዚአብሔር ጥበቃ እንዳገኘው ማወቅ አለበት፡፡ ሰውነቱንም በዚህ ንጽሕና ማቆየት የሚችለው መሐሪው ጌታ እስከፈቀደ ጊዜ ድረስ መሆኑንም መረዳት አለበት፡፡ በቅድስናውም መተማመን የለበትም፡፡ አምላካዊ ጥበቃ ለጥቂት ጊዜ ቢለየው መልሶ ሊቆሽሽ እንደሚችል በማወቅ አንዳች አይነካኝም በሚል የደህንነት ስሜትም መሸንገል የለበትም፡፡ ስለዚህ በፍጹም ጸጸትና የልብ ትሕትና አንድ ሰው በንጽሕናው ጸንቶ ለመቆየት ያለ መታከት መጸለይ አለበት፡፡

ምእራፍ ዘጠኝ

# [8]መለየት

መናፍስትን መለየት በ፩ቆሮ. ፲፪÷፲ ላይ ከተዘረዘሩት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ መናፍስትን እንድንለይ ያስጠነቅቀናል። ‹‹ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤›› (፩ዮሐ. ፲÷፩) ንጉሥ ሰሎሞን ይሰጠው ዘንድ ከአምላኩ የጠየቀው ጸጋም ይኸው ነበር። ‹‹ስለዚህም በሕዝብህ ላይ መፍረድ ይችል ዘንድ፥ መልካሙንና ክፉውንም ይለይ ዘንድ ለባሪያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው›› (፩ነገሥ. ፫÷፱)

ቅዱስ እንጦኒ መለየትን ከሌሎች በጎነቶች ሁሉ በበለጠ መመኘት እንደሚገባ ተናግሯል። ምክንያቱም ያለ መለየት በሌሎቹ የጽድቅ ሥራዎች እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም።

## ሐሳቦችን መለየት

በሰው ነፍስ ውስጥ የሚመላለሱ ብዙ ዓይነት ሐሳቦች አሉ። እነዚህ ሐሳቦች ከሦስቱ ምንጮች ከአንዱ ናቸው፡-

፩. ከራሱ ከሰውዬው ‹‹የሰዎች አሳብ ከንቱ እንደ ሆነ እግዚአብሔር ያውቃል።›› ተብሎ እንደተነገረን። (መዝ. ፺፬÷፲፩)

፪. ከእግዚአብሔር (በእኛ ዘንድ ከሚኖር ከመንፈስ ቅዱስ) ‹‹አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ፥ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና

[8] ለ ላልቶ ይነበብ። ምሳሌ፡- ክፉን ከደግ ‹መለየት›

እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ፤ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፥ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።›› ተብሎ እንደተነገረን። (ማቴ. ፲÷፲፱–፳)

፫. ከዲያቢሎስ ፡ ‹‹እራትም ሲበሉ ዲያብሎስ በስምዖን ልጅ በአስቆሮቱ በይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኋላ፥›› ይላል። (ዮሐ. ፲፫÷፪) እንዲሁም በሐዋ.፭÷፫ ፡- ‹‹ጴጥሮስም፦ ሐናንያ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሽያጭ ታስቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ስለ ምን ሞላ?›› ይላል።

ከእግዚአብሔር የሆነው ሐሳብ ተከትሎ ከዲያቢሎስ የሆነ ሐሳብ ሊመጣ ስለሚችል የሐሳቦችን ምንጭ መለየት በጣም አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ለዚህ የሚሆነን ምሳሌ በማቴዎስ ወንጌል ላይ ተቀምጦልናል።

‹‹ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ፦ አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ። ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።›› (ማቴ. ፲፮÷፲፮–፲፯)

‹‹ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሎችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር። ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ። አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ። እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን። ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ

ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።›› (ማቴ. ፲፮÷፳፩–፳፫)

እንደምትመለከቱት በቅዱስ ጴጥሮስ ልብ ውስጥ የእግዚአብሔርን ሐሳብ ተከትሎ የዲያቢሎስ ሐሳብ መጥቷል። ቅዱስ ጴጥሮስ የሐሳቦቹን ምንጮች መለየት አልቻለም። ምክንያቱም ያን ጊዜ መንፈስ ቅዱስን አልተቀበለም ነበር።

ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ‹‹መናፍስት ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነው እንደሆነ እወቁ›› ብሎ ቢያስጠነቅቀንም እነዚህን ሐሳቦች የምንለይበትን ዝርዝር አካሔድ ግን አላስቀመጠልንም።

እናም በዚህ ጉዳይ ላይ ያላቸውን ልምድ በመፈለግ ወደ በረሃ አባቶች እንሔዳለን። እነሱ የሚሉት በጠቅላላው ይህንን ይመስላል ፡-

፩. ሐሳብህ እግዚአብሔርን በመፍራት የተሞላ መሆኑን መዝን

፪. በእርግጥ ለሁሉም ሰው መልካምነት ያዘለ ነው?

፫. ጌታችን ካደረጋቸውና ሐዋርያቱም ካስተማሩት ጋር የሚስማማ ነው?

፬. ያሰብኸው ሐሳብ ሰላምንና መረጋጋትን የሚያመጣ ነው? ወይስ ቁጣ ፣ መራርነትና ሁከት የከበበው ሐሳብ ነው? እጅግ የተቀደሱ ሐሳቦች እንኳን ሰላማችንን የሚነጥቁን ከሆነ ልንጠራጠራቸው ይገባል።

ብዙ ጊዜ ወደ መወጋገዝ ወደ መለያየትና ቁጣ እያመራን እንኳን ለእግዚአብሔር በቅናት እያገለገልን እንደሆነ እንዲሰማን እንሆናለን። ይህ በተደጋጋሚ የሚከሰትብን

የሚከብቡንን ሐሳቦች የመመርመርን ጠቃሚ ሒደት ስላላለፍን ነው፡፡

እግዚአብሔር እንዴት እንደሚናገረን በመጽሐፈ ነገሥት ላይ ተጽፎልናል፡፡ እግዚአብሔር ነቢዩ ኤልያስን ሊያናግረው ወደደ እናም አለ ፦

‹‹እርሱም፦ ውጣ፥ በተራራውም ላይ በእግዚአብሔር ፊት ቁም አለ፡፡ እነሆም፥ እግዚአብሔር አለፈ፥ በእግዚአብሔርም ፊት ትልቅና ብርቱ ነፋስ ተራሮቹን ሰነጠቀ ዓለቶቹንም ሰባበረ፥ እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም፡፡ ከነፋሱም በኋላ የምድር መናወጥ ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም፡፡ ከምድር መናወጥ በኋላ እሳት ሆነ፥ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም፡፡ ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምፅ ሆነ፡፡›› (፩ነገሥ. ፲፱÷፲፩–፲፪)

የእግዚአብሔር ድምፅ ተራሮች የሚሰባብር ነፋስ ፣ ወይም የመሬት መንቀጥቀጥ ወይም እሳት አይደለም የዝምታ ድምፅ ነው እንጂ፡፡ በትዕቢት ፣ በራስ ወዳድነት ፣ በማወክ ፣ በጭንቀት ፣ በተቃውሞ ፣ በቅናትና በመለያየት የተከበበ ሐሳብ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆኑ ሐሳቦች በእርጋታ ፣ በደስታና በትሕትና የሚሞሉን ናቸው፡፡

፫. የመጣብህ ሐሳብ እያጣደፈህ ነው? አሁን የግድ መፈጸም እንዳለብህስ ይሰማሃል? እንደዚያ ከሆነ ተጠንቀቅ ፤ ምክንያቱም

ይህ ከፈታኙ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ዕድገት ቀስ በቀስና በእርጋታ እንጂ በስሜታዊነት አይመጣም፡፡

ታላቁ ቅዱስ መቃርዮስ በአንድ ወቅት በአካባቢው ያሉትን መነኮሳት ዞሮ የመጎብኘት ሐሳብ መጣበት፡፡ ሐሳቡን በውስጡ ይዞ ሲመረምረው ለሁለት ዓመታት ቆየ ፤ ሐሳቡም ከዲያቢሎስ ሆኖ ተገኘ!

እነዚህን ሁሉ ሒደቶች ካለፍህ በኋላም ዲያቢሎስ ሊያታልልህ ይችላል፡፡ ሐሳቦችህ ከወዴት እንደመጡ ለመፈተን እጅግ ጠቃሚው መንገድ ሐሳቦችህን ለንስሐ አባትህ መግለጥ ነው፡፡ አባቶች ሐሳቦችን በመለየት ሒደት ውስጥ ትልቅ ቦታ ይሰጡታል፡፡ ቅዱስ መቃርዮስ ሐሳቦቹን ከበረሃ እናቶች አንዷ ለነበረችው ለእማ ሣራ ይነግራት ነበር፡፡ ቅዱስ ሙሴ ጸሊምም ሐሳቦቹን የዐሥራ ስምንት ዓመት ወጣት ለነበረውና ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ለተሞላው ለአባ ዘካርያስ ሐሳቦቹን ይነግረው ነበር፡፡

በተለይም በወሳኝ ጉዳዮች ላይ የራስህን ውሳኔዎች አትተማመንባቸው፡፡ እኔ በግሌ ይህ ነገር አስቸጋሪ መሆኑን ተምሬያለሁ፡፡ ነገሩ እንዲህ ነው፡-

ጊዜው ረዥም ነው ፤ ቅስና በተቀበልኩ ጥቂት ዓመታት ውስጥ አንድ ከፍተኛ ውዝግብ ያስነሣና ከምእመናን መካከል መለያየትን የፈጠረ አንድ ፕሮጀክት ጀምረን ነበር፡፡ ፕሮጀክቱ ሊጀመር ሁለት ሳምንታት ሲቀሩ ከፕሮጀክቱ ይልቅ ፍቅርና መተባበር ይበልጣል የሚል ሐሳብ በአእምሮዬ መመላለስ ጀመረ፡፡ እግዚአብሔር ፕሮጀክቱን እንዳቆምና የተቃወሙትን ሰዎች ጋር

እንድታረቅ የነገረኝ መሰለኝ፡፡ ውሳኔዬን ለቦርዱ አባላት ነገርኳቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ከአባላቱ አንዱ ‹‹አባታችን ሁልጊዜ ምንም ነገር ከመወሰናችን በፊት ሐሳቦቻችንን ለንስሐ አባቶቻችን እንድናማክር ያስተምሩናል፡፡ እርስዎ ስለዚህ ሐሳብዎ የንስሐ አባትዎን አማክረዋል?›› ብሎ ጠየቀኝ፡፡ ይህንን ጠቃሚ ሒደት በመርሳቴ አፈርሁ፡፡ ለንስሐ አባቴ ደውዬ ሐሳቦቼን ነገርኳቸው፡፡ እሳቸውም ‹‹ይህ ሐሳብ ከዲያቢሎስ ነው!›› አሉኝ፡፡ እንዲሁም አንድ ጳጳስ ወደ እኛ እንደሚመጡና ማንኛውንም ውሳኔ ከመወሰኔ በፊት እሳቸውን እንዳማክር ነገሩኝ፡፡ ብፁዕነታቸው ጋርም ሔጄ ስለ መጡብኝ ሐሳቦች አማከርኳቸው፡፡ እሳቸውም ‹‹ይህ ሐሳብ ከዲያቦሎስ ነው!›› አሉኝ፡፡ በእውነት ታናሽነት ተሰማኝ፡፡ ‹‹እንዴት እኔ ሳልችል ብፁዕነትዎና የንስሐ አባቴ ሐሳቦቼን ልትለዩ ቻላችሁ?›› ብፁዕነታቸው ፈገግ ብለው ‹‹ትንሽ ተጨማሪ ልምድ ስላለን ነው!›› አሉኝ፡፡

‹‹ዲያቢሎስ ፕሮጀክቱን ማስተጓጎል ይፈልጋል፡፡ እናም ውዝግብ ካስነሣ በኋላ ወደ አንተ መጥቶ በፍቅርና አንድነት ስም ፕሮጀክቱን እንድታቆም ሊያሳምንህ ይሞክራል፡፡ ማድረግ ያለብህ እንዲህ ነው፡፡ ሒድና ፕሮጀክቱን ቀጥል ፤ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፕሮጀክቱ ወደ መሳካት ሲያመራ ውዝግቡ ያበቃል፡፡›› አሉኝ ብፁዕነታቸው፡፡ ያ አጋጣሚ ሳላማክር በራሴ ውሳኔ ላይ እንዳልተማመን ትልቅ ትምህርት ሰጠኝ፡፡ ለእናንተም ይህንኑ እንደሚያስተምራችሁ ተስፋዬ ነው፡፡

# የእግዚአብሔርን ፈቃድ መለየት

አንዳንድ ጊዜ አንድ ሰው በቀላሉ ሊወስንበት በማይችለው ሁኔታ ውስጥ ሊገባ ይችላል። ለምሳሌ በአንድ ጊዜ ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች ሊቀበሉህ ይችላሉ። አንደኛው ዩኒቨርሲቲ በምትኖርበት ከተማ ሲሆን ሌላኛው ዩኒቨርሲቲ ደግሞ ከከተማ ውጪ ሆኖ የበለጠ ዝነኛ ዩኒቨርሲቲ ይሆናል። ወይም ደግሞ ሥራ እያለህ በሌላ ከተማ ሌላ ሥራ የመቀጠር ዕድል አገኘህና ሃሳብህን አንዱ ነገር ላይ ማርጋት አልቻልህም። በእንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ላይ ነው እንግዲህ ‹‹እግዚአብሔር ለእኔ ያለው የሚፈቅደው ታዲያ የትኛውን ነው?›› የሚል ጥያቄ የምናነሣው። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ በእርግጥ አስቸጋሪ ነው። የአባቶቻችንን መንገድ ከተከተልን ግን አያስቸግርም።

ወደዚህ ጉዳይ ከመግባታችን በፊት ግን እስቲ ራሳችንን እንጠይቅ ‹‹የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ለእኔ ምን ይጠቅመኛል?››

ቅዱስ ጳውሎስ በሮሜ ፲፪፥፪ ላይ የእግዚአብሔር ፈቃድ በጎ ፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም እንደሆነ ነግሮናል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ፍጹም ነው ፤ ምንም ነገር አይጎድለውም ፣ መንፈሳዊ ፣ ሥነ ልቡናዊና ስሜታዊ ፍላጎቶችን ሁሉ ለማሟላት የሚችል ነው። እግዚአብሔር ወደፊት የሚሆነውን ያውቃል ፣ የትኛው ነገር ለዘለቄታው እንደሚጠቅመኝ ያውቃል።

በሌላ በኩል የእኔ ፍላጎት ፍጹም የሆነ ነገርም ሊሆን ይችላል። ሆኖም እኔ የዘለቄታውን ጥቅም ሳላስብ የቅርቡን ጥቅም

ብቻ ልመለከት እችላለሁ፡፡ የዘለቄታውን ከግምት ውስጥ ሳስገባ ብፈልግ እንኳን በሚመጣው ሳምንት እንኳን የሚያጋጥመኝን ነገር መተንበይ የማልችል እስከሆንኩኝ ድረስ ይህንን የማደርግበት ዓቅም የለኝም፡፡

ጠቢብ ሰው ምንም ነገር ሲያደርግ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚጠይቀው ለዚህ ነው፡፡

ሆኖም እግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት ላውቅ እችላለሁ? ባሕታዊው ቴዎፋን እንደነገረን ከሆነ እግዚአብሔር በጎ ፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነ ፈቃዱን እንዲገልጽልኝ የምፈልግ ከሆነ የራሴን ፈቃድ መተው አለብኝ፡፡ ይህም ማለት በእውነት የእርሱን ፈቃድ እንደምፈልግ ለእግዚአብሔር ማረጋገጥ አለብኝ ማለት ነው፡፡

አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ፈቃዱን እንዲያስታውቀን እንጸልያለን በውስጣችን ግን የራሳችንን አቋም ከያዝን ቆይተናል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እየምንፈልገው ከእኛ ፈቃድ ጋር እስከተስማማ ድረስ ብቻ ነው፡፡ በዚህ መንገድ የምንመራ ከሆነ እግዚአብሔር ፈቃዱን አይገልጥልንም፡፡

ባሕታዊው ቴዎፋን ይህንን ምሳሌ ሰጥቶናል፡፡ የወይን ጭማቂ ያለበት ብርጭቆ ቢኖርህና በዚያው ብርጭቆ ውስጥ ማር ልታደርግበት ብትፈልግ በመጨመሪያ የወይኑን ጭማቂ መድፋት ፣ ብርጭቆውን ማጠብና የወይኑ መዓዛ እስኪጠፋ ድረስ ለጥቂት ሰዓታት በፀሐይ ላይ ማድረቅ አለብህ፡፡ ከዚያ በኋላ ማሩን ታደርግበታለህ፡፡ የወይን ጭማቂ የተባለው ግለኛ ፣ የቅርቡን ብቻ ተመልካች ፣ ከእግዚአብሔር ፈቃድ በተለየ ፍጹምነት የሚጎድለው

፣ በጎ ያልሆነና ደስ የማያሰኝ የሆነው የእኛ ፈቃድ ነው፡፡ ማሩ ደግሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ የራሳችንን ፈቃድ ካላስወገድን እግዚአብሔር ፈቃዱን አይገልጥልንም፡፡ ምክንያቱም  የራሳችንን ፈቃድ ወስነን እያለ እግዚአብሔርን ፈቃድህን ግለጥልን ማለት በእርግጥ እንደ መዘበት ነው፡፡

እንዴት ላድርገው ይሆን? መልካም ለዚህ መፍትሔው ፈቃድን ገለልተኛ የማድረግ ልምምድ ነው፡፡ ጽንሰ ሐሳቡ ይሔ ነው፡፡ በአንድ ነገር ላይ በአወንታዊም ይሁን በአሉታዊ መንገድ ላዘነብል እችላለሁ፡፡ ለምሳሌ ተጨማሪ ደሞዝ የሚያስገኝልኝ ሥራ ካገኘሁ ለዚያ ሥራ ላደላ እችላለሁ ፤ ይህም የዚያን ሥራ መጥፎ ጎኖች ከመመልከት ሊከለክለኝ ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ የማልፈልገውን ነገር እንድቀበል የሚጋብዝ ሁኔታ ደግሞ ሊያጋጥመኛል ሆኖም ነገሩን ስለማልፈልገው ያሉትን በጎ ጎኖች ለመመልከት አልፈልግም፡፡ እነዚህ መውደድና መጥላቶች ብዙውን ጊዜ ከመጀመሪያ እይታ የሚመነጩ ናቸው፡፡ እናም ብዙ ጊዜ የምንወስደው እርምጃ የገንዘቡን ሌላ ጎን በመዘንጋት ነው፡፡ መፍትሔው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡

እስቲ ምሳሌ እንውሰድ፡፡ አንድ በከተማችን የሚገኝ ዩኒቨርሲቲ ተቀበለኝ እንበል፡፡ ሆኖም ከከተማ ውጪ ያለ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ ጥሪ አደረገልኝ፡፡ ‹ነጻ የመሆን› ፍላጎቴ ከከተማ ወጥቶ በመማር የሚመጡብኝን የጎንዮሽ ጉዳቶች እንድዘነጋቸው አደረገኝ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ፍጹም ፣ በጎና ደስ የሚያሰኝ የሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ የቱ እንደሆነ ለማወቅ ትፈልጋላችሁ?

በመጀመሪያ ሆን ብዬ በሩቅ ከተማው ዩኒቨርስቲ ጉዞዬ ምክንያት የሚመጡ ጥሩ ያልሆኑ ነገሮችን ነቅሶ በማውጣትና ቢቻል በማጉላት ለአንዱ ጉዳይ ማድላቴን ትቼ ገለልተኛ /ሚዛናዊ/ መሆን አለብኝ፡፡

አንደኛ ከቤተሰቦቼና ከጓደኞቼ ልርቅ ነው፡፡ ልነጋገር የምችለው ከማላውቃቸው ሰዎች ጋር ስለሆነ ብቸኝነት ይሰማኛል፡፡ በዩኒቨርሲቲው አካባቢ ቤተ ክርስቲያን ስለሌለ ለመሳለም ለሰዓታት ያህል መጓዝ ይኖርብኛል፡፡ እንዲረዱኝ ሁልጊዜ የምቀርባቸውን የንስሐ አባቴንም ከእኔ በመራቃቸው ምክንያት ላጣቸው ነው ወዘተርፈ

በእርግጥም እነዚህ ሁሉ አሉታዊ ጎኖች እውነት ሆነው ሳለ ከቤተሰብ ቁጥጥርና ከቤት ውጪ በመሆን ስለምታገኘው ‹ነጻነት› ስትል ንቀህ ትተኸዋል፡፡ ቁርጠኛ የሆነ ሰው ግን ይህንን ልምምድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ያደርጋል፡፡ በውጤቱም ራስህን ለሁለቱም ምክረ ሐሳቦች ያላደላ ገለልተኛ ሆኖ ታገኘዋለህ፡፡ እያንዳንዱም ሐሳብ የየራሱ አወንታዊና አሉታ ጎን አለው፡፡

በሺህ የሚቆጠሩ ዶላሮችን የምታገኝበት ነገር ግን ልጆችህን ከትምህርት ቤታቸው ፣ ከጓደኞቻቸውና ከሰንበት ትምህርት ቤታቸው እንድትለያቸው የሚያደርግህና አንተንም ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎትህ እና ከንስሐ አባትህ የሚነጥልህ ሥራ ስታገኝም ይህንኑ መተግበር አለብህ፡፡

የመጀመሪያው ሒደት ስለምታገኘው ነገር መልካም ጎን በምትሰጠው ክብደት መጠን መጥፎ ጎኑንም በትኩረት በመለየት

ሚዛናዊ መሆን ነው። ይህን ጊዜና ይህን ጊዜ ብቻ ነው ወደ እግዚአብሔር ቀርበህ በጎ ፍጹምና ደስ የሚያሰኝ ፈቃዱን እንዲገልጽልህ መለመን የምትችለው።

ቀጣዩ ሒደት ወደ ንስሐ አባትህ መሔድና እንዲጸልዩልህ መጠየቅ ነው። ይህ ሲሆን ፈቃዱን ይገልጥልሃል። ይህ ራስህን ለንስሐ አባትህ የማስገዛት ተግባር የትሕትና ሲሆን እግዚአብሔር ፈቃዱን ይገልጽልህ ዘንድ ትልቁ ቅድመ ሁኔታ ነው።

እግዚአብሔር ለአንተ የማይስማማህን ነገር ይፈቅድ ይሆን ብለህ ፍርሃት ፍርሃት የሚልህ ከሆነ የቤት ሥራህን በሚገባ አልሠራህም ፣ ለአንዱ ነገር ማድላትህ አሁንም ድረስ አለ። ወደ ንስሐ አባትህ ሔደህ እንዲጸልዩልህ ነግረሃቸው እግዚአብሔር ከአንዱ አማራጭ ይልቅ ሌላኛውን እንዲመርጥ የምትመኝ ከሆነ አሁንም የቤት ሥራህን በሚገባ አልሠራህም።

በሚከተለው ምሳሌ እንደምነግርህ አንተ ራስህን ገለልተኛ ከማድረግህ በፊት እግዚአብሔር አንተ ትፈልገው የነበረውን አማራጭ መርጦት ሲሆን ደግሞ መልካም ይሆናል።

ወደ ካናዳ ከመምጣቱ በፊት ግብፅ እያለ የማውቀው አንድ ወጣት ወላጆቹና ወንድም እኅቶቹ ሁሉ ካናዳ የሚኖሩ ቢሆንም እርሱ ግን ወደ ካናዳ ለመምጣት ፈቃድ ለማግኘት በካናዳ ኤምባሲ በኩል ያደረገው ተደጋጋሚ ጥረት እንዳልተሳካለት በማማረር ደብዳቤ ጻፈልኝ።

እኔም ወደ ካናዳ እንድትሰደድ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይሆን ይሆናል አልሁት። ከዚያም የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት

ለማወቅ መፈለግ እንዳለበትና ራሱን ሚዛናዊ ለማድረግ ምን ማድረግ እንዳለበት አስከትዬ ነገርሁት፡፡ እሱም ምክሬን ተቀብሎ ወደ ካናዳ ባለመሔዱ ውስጥ ስለሚያገኛቸው መልካም ነገሮችም ማሰብ ጀመረ፡፡

ለሚስቱም ‹‹በግብፅ ከቆየን ወላጆቼና ቤተሰቦቼ ግብፅን ለመጎብኘት ቢፈልጉ እንኳን የእኛ ቤት ማረፊያቸው ይሆናል፡፡ እንዲሁም እዚህ ሁለታችንም ጥሩ ሥራ እስካለን ድረስ ወደ ካናዳ ሔደን ሀ ብለን መጀመር አይኖርብንም፡፡ ማመልከቻዎችም የምንጽፈው ካናዳ አልሔዱም ለመባል ብቻ ነው፡፡ በማንኛውም ጊዜ ወደ ካናዳ መሔድና ከቤተሰቦቻችን ጋር ማሳለፍ በሁለቱም ዓለማት ፈለግነውን ማድረግ እንችላለን፡፡›› ብሎም ለሚስቱ ነገራት፡፡ ሁለቱም ይህንን ይህንን አቋም በግብፅ መኖር መጥፎ እንዳልሆነ እስኪያምኑ ድረስ ተከተሉት፡፡ (በተለይም ነገሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ እስከሆነ ድረስ)

በቀጣዩ ደብዳቤ እንዲህ ብሎ ጻፈልኝ ‹‹ከሀገር ብንወጣም ግብፅ ውስጥ ብንቆይም ምንም ለውጥ አያመጣም ብለን ማሰብ ስንጀምርና ለአንዱ ነገር ብቻ ከነበረን ዝንባሌ ነጻ በሆንበት ዕለት ከካናዳ ኤምባሲ ተደውሎ እንደተቀበሉንና ቪዛችንን ለመቀበል የህክምና ምርመራ እንድናደርግ ተነገረን፡፡››

ይህንን መንፈሳዊ ልምምድ የማድረግ ውበቱ ሁልጊዜ እንዲህ ዓይነት ነገር ሲገጥምህ ወደ ተመሳሳይ ሒደት ትመጣለህ፡፡ ማድረግ ስለሚገባህ ነገር ከመጠን በላይ አለማሰብ ቀላል ይሆንልሃል፡፡ የራስህን ፍላጎት ቀብረህና ሚዛናዊ ሆነህ በመገኘትም

ፍጹም በጎና ደስ የሚያሰኘው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሊገለጥልህ ይችላል፡፡

አንዳንድ የማሳሰቢያ ቃላትን ልነግርህ እፈልጋለሁ! ለማታለል እንዳትሞክር! አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ እንፈልጋለን ሆኖም እግዚአብሔር ፈቃዱን ሲገልጥልን በፈቃዱ አንደሰትም፡፡ አንዳንድ ሰዎች የንስሐ አባትን መቀየር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ይቀይረው ይሆናል በሚል ተስፋ ሌላ ንስሐ አባት ይቀይራሉ፡፡

ሌላው ችግር የእግዚአብሔር ፈቃድ ፍጹም ዘንግተን እግዚአብሔር የምንፈልገውን ብቻ እንዲሰጠን በመጠየቅ የራሳችንን ፈቃድ ብቻ እንከተላለን፡፡ ይህ በተለይ በጋብቻ ጉዳይ ላይ እጅግ አደገኛ ነገር ነው፡፡

የተቀደሰ ትውስታ የነበራቸው የቀድሞው አቡነ ጴኤሜን ከሚስቱ ጋር ስላለበት የጋብቻ ችግር ለማማከር ሁልጊዜ ወደ እርሳቸው ስለሚመጣ አንድ ወጣት ታሪክ ነግረውኝ ነበር፡፡ ጳጳሱ አንድ ቀን በመታከት ‹‹ይህችን ሴት ከማግባትህ በፊት ጸልየህ ነበር?›› ብለው ጠየቁት፡፡ እሱም ‹‹አዎን ለስድስት ወራት በየቀኑ እጸልይ ነበር!›› አላቸው፡፡ ጳጳሱም ‹‹ምን እያልህ ነበር የምትጸልየው?›› ብለው ጠየቁት፡፡ ወጣቱም ‹‹እግዚአብሔር ሆይ እባክህ ይህችን ሴት እንዳገባት ፍቀድልኝ!›› እያልሁ እጸልይ ነበር አላቸው፡፡

እኔ እጅግ የተሻለ መንገድ የምለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ መቀበል ለብዙ ወጣቶች እጅግ አስቸጋሪ ነገር ነው፡፡ አንዲት ወጣት

‹‹ከጋብቻ በስተቀር በሁሉም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ እቀበላለሁ!›› አለችኝ፡፡ ለምን እንደሆነም ጠየቅኋት፡፡ መለሰች ‹‹ምክንያቱም እግዚአብሔር የሚፈቅደው አብሮ ለመኖር የሚከብደኝን በሰንበት ትምህርት ቤቶች የሚያስተምር ዲያቆን እንዳገባ ነው!›› አለችኝ፡፡ እኔም ‹‹እግዚአብሔር አብረሽው በመኖርሽ ሊያስደስትሽ የሚችል በሰንበት ትምህርት ቤት የሚያስተምር ዲያቆንንስ ሊመርጥልሽ አይችልም?›› አልኳት፡፡

‹የእግዚአብሔር ፈቃድ በጋብቻዬ ላይ› በሚል ርእስ በምናደርገው ውይይት ላይ ታዳሚ የነበረ ሌላ ወጣት ደግሞ ባቀረብኩት ነገር ላይ በቁጣ ተቃውሞ ተነሣ፡፡ ‹‹ጋብቻን በተመለከተ የዕጣ ፈንታዬ ጌታ እኔ ራሴ መሆን አለብኝ!›› እኔም መለስሁለት ‹‹እጮኛህ በመምረጥ ሒደት ላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ንቀህ ከተውህ የጥፋትህም ጌታ አንተው ትሆናለህ!››

ይህንን ምሳሌ ለወጣቶቻችን ሁሉ ለመስጠት እፈልጋለሁ! ሕይወታችሁ ሁለት ሰዎች እንደሚሠሩባት ጀልባ ናት የአንደኛው ሥራ መቅዘፍ ሲሆን የጀልባዋን አቅጣጫ መቆጣጠሪያ (መልሕቅ?) የሚይዝ ነው፡፡ ጠቢብ ሰው ‹‹ጌታ ሆይ አንተ አቅጣጫ መቆጣጠሪያውን ያዝ እኔ ደግሞ መቅዘፊያውን ልያዝ!›› ይላል፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ ብዙ ጊዜ እኛ አቅጣጫ ጠቋሚውን ለመያዝ የምንታገል ሲሆን እግዚአብሔር ግን ቀዛፊ እንዲሆን እንፈልጋለን!

የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደ ራስ ምርጫ አድርጎ የመቀበል ጥቅሙ ሕይወት ወዴትም አቅጣጫ ቢያመጣህ እግዚአብሔር እንደፈቀደው ስለምታውቅና እግዚአብሔር የፈቀደልኝ ነው

ስለምትል አትፈራም፡፡ በአጭር ቃል ‹‹አልወደውም!›› የሚባል ዓይነት ነገር ቢሆንም እንኳን በእርግጥ በጎ ፣ ፍጹምና ደስ የሚያሰኝ ነው፡፡

‹‹ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ ለሚያዞረን በእኛም በየስፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ ለሚገልጥ ለአምላክ ምስጋና ይሁን!››
***፪ቆሮ. ፪፥፲፬***